www.abyssinialaw.com



# አዋጅ ቁጥር ፸፭/፲፱፻፺፯ ዓ·ም
# የቤተሰብ ሕግ አዋጅ

## መግቢያ

ቤተሰብ የሕብረተሰብ መሠረት መሆኑን በማመን የመንግሥትና የሕብረተሰብ ጥበቃ ማግኘት እንዲችል የቤተሰብ ግንኙነት በሕግ መደን ገግና መገዛት ያለበት በመሆኑ ፤

በሥራ ላይ ያለው የኢትዮጵያ የቤተሰብ ሕግ ከክልላችን ተጨባጭ ሁኔታና በዋነኛነትም ከሕገ–መንግሥቱ ጋር እንዲጣጣም ማድረግ በማስፈ ለጉና በተለይም ጋብቻ በተጋቢዎች ነፃና ሙሉ ፈቃድ ላይ ብቻ መመሥረት ያለበት መሆኑንና በጋብቻ አፈፃፀም በጋብቻ ዘመንና በፍቺ ጊዜ የተጋቢዎችን የእኩልነት መብት የሚያስጠብቅ እንዲሁም የልጆችን ደህንነት አስተዳደግና አጠባበቅን ቀደምትነት በሚሰጥ መልኩ ሕግ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ፤

በቤተሰብ ውስጥ የሚነሱ ክርክሮችን ፍትሐዊ በሆነና በተቀላጠፈ ሁኔታ ብቃት ባለው አካል እንዲዳኙ ማድረግ በማስፈለጉ ፤

በክልላችን ተፈፃሚነት የሚኖረው የቤተሰብ ሕግ በክልሉ መንግሥት ምክር ቤት መውጣት ያለበት ስለሆነ ፤

በተሻሻለው የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፩ ንዑስ አንቀጽ ፫(ሀ) መሠረት ከዚህ የሚከተለው ታውጇል ።

፩· አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ “የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል መንግሥት የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር ፸፭/፲፱፻፺፯” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

www.abyssinialaw.com


## ምዕራፍ አንድ

## ስለመተጫጨት

**አንቀጽ ፩· ትርጓሜ**

፩· መተጫጨት ማለት እጮኛውና እጮኛይቱ ለወደፊት በመካከላቸው ጋብቻ ለመፈጸም የሚያደርጉት ስምምነት ነው ፡፡

፪· ስምምነታቸው በነፃ ፈቃድ ካልተመሠረተ ሕጋዊ ውጤት አይኖረውም ፡፡

፫· በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ /፩/ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ የተጋቢዎቹ ወላጆች ወይም ሌሎች ዘመዶች በመተጫጨቱ ላይ ስምምነታቸውን ሊሰጡ ይችላሉ ፡፡

**አንቀጽ ፪· የቤተዘመድ እንደራሴ**

፩· የቤተዘመድ እንደራሴ ሆነው የሚቆጠሩት በቅድሚያ አባትና እናት ሲሆኑ ፣ እነዚህ ከሌሉ ወይም ፈቃዳቸውን መስጠት የማይችሉ ከሆነ ሌሎች ወደ ላይ የሚቆጠሩ ወላጆች ወይም ወደጐን የሚቆጠሩ ዘመዶች ናቸው ፡፡

፪· የቤተዘመድ እንደራሴ ከሌለ ተጋቢዎች ሌላ ሰው ሊመርጡ ይችላሉ ፡፡

**አንቀጽ ፫· መተጫጨትን የሚከለክል ምክንያት**

በአንቀጽ ፩ ንዑስ አንቀጽ /፫/ የተመለከተው ቢኖርም ጋብቻ የሚከለክል ሕጋዊ ምክንያት ሳይኖር የተጋቢዎቹ ዘመዶች ለመተጫጨቱ ስምምነታቸውን አለመስጠት ምንም ለውጥ አያስከትልም፡፡

**አንቀጽ ፬· የመተጫጨት ውል አቀራረጽ /ፎርም**

የመተጫጨቱ ሥርዓት መተጫጨቱ በሚደረግበት ቦታ ልማድ መሠረት ወይም በጽሑፍ ይፈጸማል ፡፡

www.abyssinialaw.com



### አንቀጽ ፫· የመተጫጨት ማስረጃ

፩· መተጫጨቱ የተደረገው በጽሑፍ በሆነ ጊዜ የመተጫጨት ስምምነት መኖሩን ማስረዳት የሚቻለው ይህንኑ ጽሑፍ በማቅረብ ነው ።

፪· ጽሑፉ በጠፋ ጊዜ ወይም በሌለ ጊዜ በሦስት ምስክሮች ወይም ማናቸውም ማስረጃ በማቅረብ ይሆናል ።

### አንቀጽ ፬· መተጫጨት የሚቆይበት ጊዜ

በመተጫጨቱ ስምምነት ውስጥ ጋብቻ የሚፈጸምበት ጊዜ ካልተወሰነ የመተጫጨቱ ስምምነት በተደረገ በአንድ ዓመት ውስጥ ጋብቻ መፈጸም አለበት ።

### አንቀጽ ፭· የመተጫጨት መፍረስ

ከተጋቢዎች አንዱ ጋብቻ ለመፈጸም እንቢ ካለ ወይም በሁኔታ ወይም በጠባይ ጋብቻ እንዳይፈጸም የሚያደርግ ሁኔታ ካሳየ የመተጫጨት ስምምነት ይፈርሳል ።

### አንቀጽ ፮· የመተጫጨት መፍረስ የሚያስከትለው ውጤት

፩· ለመተጫጨት መፍረስ ኃላፊ የሆነው ወገን በመተጫጨቱ ምክንያት የተደረጉ ወጭዎችን ሁሉ የመክፈልና የተቀበለውን ስጦታ ለሌላው ወገን የመመለስ ግዴታ አለበት ።

፪· ኃላፊ የሆነው ወገን በተጨማሪ ሊተጉጂው ወገን የሕሊና ጉዳት ካሣ እንዲከፍል ፍ/ቤቶች ሊወስኑበት ይችላሉ ።

፫· ፍ/ቤት የካሣውን መጠን ለመወሰን ርትዕንና የአካባቢውን ልማድ መሠረት ያደርጋል ።

፬· ሆኖም የሕሊና ጉዳት ካሣ መጠን ከ፲ሺ /አሥር ሺ/ የኢትዮጵያ ብር የበለጠ ሊሆን አይችልም ።

### አንቀጽ ፯· የመተጫጨት መቅረት

መተጫጨቱ የቀረው ከተጋቢዎቹ በአንደኛው ሞት ወይም በሁለቱም ስምምነት ከሆነ ከላይ በአንቀጽ ፮ የተደነገገው ተፈፃሚ አይሆንም ።

www.abyssinialaw.com



አንቀጽ ፲· ስለይርጋ

በመተጫጨት መፍረስ ምክንያት የሚቀርቡ ክሶች ሁሉ መተጫጨቱ ከፈረሰበት ቀን አንስቶ በሁለት ዓመት ውስጥ ካልቀረቡ በይርጋ ይታገዳሉ ።

## ምዕራፍ ሁለት
## ስለጋብቻ አፈፃፀም
### ክፍል ፩
### ጠቅላላ

አንቀጽ ፲፩· ልዩ ልዩ የጋብቻ ሥርዓቶች

፩· ጋብቻ በአንድ የክብር መዝገብ ሹም ፊት ሊፈጸም ይችላል።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ ላይ የተጠቀሰው ቢኖርም፣ ጋብቻ በተጋቢዎች ኃይማኖት ወይም ባህል መሠረት ሊፈጸም ይችላል ።

አንቀጽ ፲፪· በክብር መዝገቡ ሹም ፊት የሚፈጸም ጋብቻ

ጋብቻ በክብር መዝገብ ሹም ፊት ተፈጸመ የሚባለው አንድ ወንድ እና አንዲት ሴት ጋብቻ ለመፈጸም ተስማምተው በክብር መዝገቡ ሹም ፊት በመቅረብ ፈቃዳቸውን ሲገልጹና የክብር መዝገቡ ሹሙም ይህንኑ ፈቃዳቸውን ሲቀበል ነው ።

አንቀጽ ፲፫· በኃይማኖት ሥርዓት መሠረት የሚፈጸም ጋብቻ

፩ ጋብቻ በኃይማኖት ሥርዓት መሠረት ተፈጸመ የሚባለው አንድ ወንድና አንዲት ሴት በኃይማኖታቸው ወይም ከሁለቱ በአንዳቸው ኃይማኖት መሠረት የሚፀና ጋብቻ ለማቋቋም የሚያስፈልገውን ሲፈጽሙ ነው ።

፪· በኃይማኖት ሥርዓት መሠረት ጋብቻ ሊፈጸም የሚችል በትና የአፈፃጸሙ ሥርዓት እንደየኃይማኖቱ ሥርዓት ይሆናል ።

አንቀጽ ፲፬· በባህል ሥርዓት መሠረት የሚፈጸም ጋብቻ

፩· ጋብቻ በባህል ሥርዓት መሠረት ተፈጸመ የሚባለው አንድ ወንድና አንዲት ሴት በሚኖሩበት አካባቢ ወይም

www.abyssinialaw.com



ጋብቻቸውን በሚፈጽሙበት ባህል ወይም በሁለቱ ተጋቢዎች ወይም ከሁለቱ ተጋቢዎች በአንዳቸው ባህል መሠረት የሚፀና ጋብቻ ለማቋቋም የሚያስፈልገውን ሥርዓት ሲፈጽሙ ነው ፡፡

፪· በባህል ሥርዓት መሠረት ጋብቻ ሊፈጸም የሚችልበትና የአፈፃፀሙ ሥርዓት እንደ አካባቢው ባህል ሥርዓት ይሆናል ፡፡

አንቀጽ ፲፫· ከክልሉ ውጭ ስለሚፈጸም ጋብቻ

፩· በተፈጸመበት አገር የጋብቻ አፈፃፀም ሕግ መሠረት ከኢትዮጵያ ውጭ የተፈጸመ ጋብቻ የሕዝብን ሞራል እስካልተቃረነ ድረስ በዚህ ሕግ ተቀባይነት ይኖረዋል ፡፡

፪· ጋብቻው በተፈጸመበት ክልል የጋብቻ አፈፃፀም ሕግ መሠረት ከክልሉ ውጭ የተፈጸመ ጋብቻ የሕዝብን ሞራል እስካልተቃረነ ድረስ በዚህ ሕግ ተቀባይነት ይኖረዋል ፡፡

## ክፍል ፪
## ሁሉንም ዓይነት ጋብቻ ለመፈጸም መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች

አንቀጽ ፲፬· ፈቃድ

የሚፀና ጋብቻ ተፈጸመ የሚባለው ተጋቢዎቹ ለመጋባት ነፃና ሙሉ ፈቃዳቸውን ሲሰጡ ብቻ ነው፡፡

አንቀጽ ፲፭· ዕድሜ

፩· ወንዱም ሆነ ሴቷ አሥራ ስምንት ዓመት ሳይሞላቸው ጋብቻ ለመፈጸም አይችሉም ፡፡

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ የተደነገገው ቢኖርም ከባድ ምክንያት ሲያጋጥም የተጋቢዎቹ ወይም ከተጋ ቢዎቹ የአንዳቸው ወላጆች ወይም አሳዳሪ በሚያቀርቡት ጥያቄ መሠረት የፍትሕ ቢሮ ኃላፊው ከመደበኛው የጋብቻ ዕድሜ ከሁለት ዓመት ያልበለጠ ጊዜ በመቀነስ እንዲጋቡ ሊፈቅድ ይችላል ፡፡

www.abyssinialaw.com


አንቀጽ ፲፰· የሥጋ ዝምድና

፩· በቀጥታ የሥጋ ዘመዶች መካከል ጋብቻ መፈጸም ክልክል ነው ።

፪· ወደ ጐን በሚቆጠር የሥጋ ዝምድና ባላቸው ዘመዳሞች መካከል ክልከላው እስከ ሰባተኛ ደረጃ ድረስ ነው ።

፫· የዝምድና ደረጃ አቆጣጠር የጋራ ከሆነው የግንድ ወላጅ ጀምሮ ግራና ቀኝ ያለውን ትውልድ መስመር በመቁጠር የሚገኝ ድምር ነው ።

አንቀጽ ፲፱· የጋብቻ ዝምድና

፩· በቀጥታ የጋብቻ ዘመዳሞች መካከል ጋብቻ መፈጸም ክልክል ነው ።

፪· ወደ ጐን በሚቆጠር የጋብቻ ዝምድና ባላቸው ዘመዳሞች መካከል ክልከላው እስከ ሦስተኛ ደረጃ ነው ።

አንቀጽ ፳· በሕግ ያልተረጋገጠ ልጅነት

የአንድ ሰው ተወላጅነት በሕግ መሠረት ያልተረጋገጠ ቢሆንም እንኳን በማህበረሰቡ ዘንድ በተወላጅነት የሚታወቅ ከሆነ በዚህ ሕግ በአንቀጽ ፲፰ እና ፲፱ መሠረት ለጋብቻ ክልከላ በቂ ነው ።

አንቀጽ ፳፩· በጋብቻ ላይ ጋብቻ

ማንኛውም ሰው አስቀድሞ በጋብቻ የተሳሰረ ከሆነ ጋብቻው ፀንቶ ባለበት ጊዜ ሌላ ጋብቻ ወይም ጋብቻ ሳይፈጸም እንደባልና ሚስት አብሮ የመኖር ግንኙነት መፈጸም የተከለከለ ነው ።

አንቀጽ ፳፪ /፩/ ጋብቻን በውክልና ለመፈጸም የማይቻል ስለመሆኑ

፩· ጋብቻ ሲፈጸም ሁለቱም ተጋቢዎች ጋብቻውን በሚፈጸምበት ጊዜ በግንባር ተገኝተው ፈቃዳቸውን መስጠት አለባቸው ።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ የተደነገገው ቢኖርም ከባድ ምክንያት መኖሩን እና በተወካይ አማካይነት ጋብቻውን ለመፈጸም የሚፈልገው ተጋቢ ፈቃዱን በማያሻማ ሁኔታ የገለጸ መሆኑን የፍትሕ ቢሮ ኃላፊው

www.abyssinialaw.com



ሲያረጋግጥ ጋብቻው በውክልና ሊፈጸም ይችላል ።

አንቀጽ ፳፫ /፪/· መሠረታዊ ስህተት

፩· በስህተት በተገኘ ፈቃድ ምክንያት የተፈጸመ ጋብቻ አይፀናም ።

፪· በስህተት ምክንያት ፈቃድ ተጓደለ የሚባለው ስህተቱ መሠረታዊ ሆኖ ሲገኝ ነው ።

፫· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፪/ የተገለጸው አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ መሠረታዊ ስህተት እንዳለ ይቆጠራል ፤

(ሀ) በሚያገባው ሰው ማንነት ላይ በመሳሳት ምክንያት አገባዋለሁ ብሎ ያላሰበውን ሰው ያገባ ሲሆን ፤

(ለ) የሚያገባው ሰው ሊድን የማይችል ከባድ በሽታ ወይም ለተወላጆች ሊተላለፍ የሚችል ነዋሪ በሽታ ያለበት መሆኑን ሳያውቅ ያገባው ሲሆን ፤

(ሐ) ከተጋቢዎቹ አንዱ የግብረ ሥጋ ግንኙነት መፈጸም የማይችል መሆኑን ባለማወቁ ምክንያት ያገባው ሲሆን ፤

(መ) ከተጋቢዎቹ አንዱ ከተመሳሳይ ፆታ ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት የመፈጸም ልማድ ያለው መሆኑን ባለማወቅ ምክንያት ያገባው ሲሆን።

አንቀጽ ፳፬ /፫/· በኃይል ሥራ የተገኘ ፈቃድ

፩· በኃይል ሥራ በተገኘ ፈቃድ ምክንያት የተፈጸመ ጋብቻ አይፀናም ።

፪· ፈቃድ በኃይል የተገኘ ነው የሚባለው ፈቃዱን የሰጠው ተጋቢ ራሱን ወይም ከወላጆቹ ወይም ከተወ ላጆቹ አንዱን ወይም ሌላ ለእርሱ የቅርብ ዘመድ የሆነውን ሰው ሊፈጸምበት ከተቃረበ ከባድ አደጋ ለማዳን ሲል ፍቃዱን የሰጠ ሲሆን ነው።

አንቀጽ ፳፭· በፍርድ የተከለከለ ሰው ጋብቻ

፩· በፍርድ የተከለከለ ማንኛውም ሰው ፍርድ ቤት ካልፈቀደለት በስተቀር ጋብቻ መፈጸም አይችልም።

www.abyssinialaw.com


፪· ስለዚህ ጉዳይ ፍርድቤትን ለማስፈቀድ ለፍርድ ቤት የሚቀርበውን ጥያቄ የተከለከለው ሰው ራሱን ወይም አሳዳሪው ሊያቀርበው ይችላል ።

አንቀጽ ፳፮· በብቸኝነት ለመኖር የተወሰነ ጊዜ

፩· አንዲት ሴት አስቀድሞ የነበራት ጋብቻ ከቀረ በኋላ አንድ መቶ ሰማንያ ቀን ካላለፈ በስተቀር እንደገና ከሌላ ሰው ጋር ጋብቻ መፈጸም አትችልም ።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ የተደነገገው ቢኖርም ሴቲቱ አስቀድሞ የነበራት ጋብቻ ከቀረ በኋላ አንድ መቶ ሰማንያ ቀን ሳይሞላ ፤

(ሀ) የወለደች እንደሆነ ፤ ወይም

(ለ) ጋብቻ የምትፈጽመው ከቀድሞ ባሏ ጋር የሆነ እንደሆነ ወይም

(ሐ) እርጉዝ አለመሆኗ በሕክምና የተረጋገጠ እንደሆነ ወይም

(መ) በብቸኝነት ለመኖር የተወሰነውን ጊዜ እንዳትጠብቅ ፍርድ ቤት የወሰነ እንደሆነ ፤ በብቸኝነት ለመኖር ስለተወሰነው ጊዜ የተደነገገው ተፈፃሚ አይሆንም ።

## ክፍል ፫
## ጋብቻ እንዳይፈጸም ስለመቃወም

አንቀጽ ፳፯· ስለመቃወም

ጋብቻ ለመፈጸም አስፈላጊ የሆነ ሁኔታ አልተሟላም በማለት ሊፈጸም የታሰበ ጋብቻ እንዳይፈጸም ተቃውሞ ማቅረብ ይቻላል ።

አንቀጽ ፳፰· መቃወም ስለሚችሉ ወገኖች

ጋብቻ እንዳይፈፀም መቃወም የሚችሉት ወገኖች የሚከተሉት ብቻ ናቸው ፤

ሀ) በዕድሜ ምክንያት ሲሆን ፤ ወላጆች ፤ ዐቃቤ ሕግ ወይም ሌላ ማንኛውም ያገባኛል የሚል ሰው ፤

ለ) በሥጋ ወይም በጋብቻ ዝምድና ምክንያት ሲሆን የተጋቢዎቹ ወይም የአንደኛው ተጋቢ ወደ ላይ የሚቆጠሩ ወላጆች ፤ ፲፰ ዓመት የሞላቸው ወንድሞች

www.abyssinialaw.com



ወይም እህቶች ወይም ዐቃቤ ሕግ፤

ሐ) በጋብቻ ላይ ጋብቻ ሊፈጸም ሲሆን ሌላ ጋብቻ ከሚፈጽመው ሰው ጋር የቀደመ ጋብቻ አለኝ የሚለው ተጋቢ ወይም ዐቃቤ ሕግ ።

መ) በፍርድ በመከልከል ምክንያት ሲሆን አሳዳሪው ወይም ዐቃቤ ሕግ።

አንቀጽ ፳፱· መቃወሚያ ስለሚቀርብበት ሥርዓትና ጊዜ

፩· ጋብቻ እንዳይፈጸም የሚቀርበው መቃወሚያ በጽሑፍ ሆኖ እጅግ ቢዘገይ ጋብቻው ከሚፈጸምበት ከ፲፫ ቀን በፊት ለጋብቻ አስፈፃሚው ባለሥልጣን መቅረብ አለበት።

፪· ጋብቻ አስፈፃሚው ባለሥልጣን በመቃወሚያው ላይ ውሣኔ ከመስጠቱ በፊት የተጋቢዎቹን አስተያየት መቀበል ይኖርበታል ።

አንቀጽ ፴· በመቃወሚያው ላይ ስለሚሰጠው ውሣኔ

፩· ጋብቻ የሚያስፈጽመው ባለሥልጣን በሚቀርብለት መቃወሚያ ላይ በአምስት ቀን ውስጥ ውሣኔ መስጠት አለበት።

፪· ጋብቻ አስፈፃሚው ባለሥልጣን መቃወሚያውን ባለመቀበል ጋብቻው እንዲፈጸም የሚሰጠው ውሣኔ የመጨረሻ ይሆናል ።

፫· ጋብቻ አስፈፃሚው ባለሥልጣን መቃወሚያውን የተቀበለው እንደሆነ ጋብቻው እንዳይፈጸም ማድረግ አለበት።

፬· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፫/ የተመለከተው ውሣኔ የተሰጠ እንደሆነ ባለሥልጣኑ ለውሣኔው ምክንያት ያደረገውን ጉዳይ ተጋቢዎቹ ወዲያውኑ እንዲያውቁት ማድረግ አለበት ።

አንቀጽ ፴፩· ስለይግባኝ

፩· በዚህ ሕግ አንቀጽ ፴ ንዑስ አንቀጽ /፫/ በተመለከተው ሁኔታ በሚሰጠው ውሣኔ ላይ ተጋቢዎቹ ወይም ከተጋቢዎቹ አንዱ ለፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላሉ ።

፪· ይግባኝ የቀረበለት ፍርድ ቤት የጋብቻ አስፈፃሚውን

www.abyssinialaw.com


ባለሥልጣን ውሣኔ የሻረው እንደሆነ ባለሥልጣኑ ጋብቻውን ያስፈጽማል።

## ክፍል ፬
## የጋብቻ አፈፃፀም ሥርዓቶች

**አንቀጽ ፴፪ /፩/ ሥልጣን ያለው የክብር መዝገብ ሹም**

ጋብቻ ከተጋቢዎቹ አንዱ ወይም ከተጋቢዎቹ ወላጆች ወይም የቅርብ ዘመዶች አንዱ ጋብቻው ከሚፈጸምበት ጊዜ በፊት ቢያንስ ለስድስት ወራት ያህል ሳያቋርጥ በሚኖርበት ቦታ በሚገኘው የክብር መዝገብ ሹም ፊት ይፈጸማል።

**አንቀጽ ፴፫ /፪/ ጋብቻ ለመፈጸም ጥያቄ ስለማቅረብ እና ስለሚቀርብበት ጊዜ**

ተጋቢዎቹ ጋብቻ ለመፈጸም ማሰባቸውን እጅግ ቢዘገይ ጋብቻቸውን ለመፈጸም ከወሰኑበት ቀን ከአንድ ወር በፊት ለክብር መዝገብ ሹሙ ማስታወቅ አለባቸው ።

**አንቀጽ ፴፬ /፫/ ጋብቻ የሚፈጸምበት ቀን ስለመወሰንና ስለማስታወቅ**

የክብር መዝገብ ሹሙ ጥያቄው እንደቀረበለት ከተጋቢዎቹ ጋር በመነጋገር ከወሰነ በኋላ ጋብቻው የሚፈጸምበትን ቀን በመግለጽ አመቺ በሆነው መንገድ ማስታወቂያ ያወጣል ።

**አንቀጽ ፴፭ /፬/ የጋብቻ አፈፃፀም ሥርዓት እና ጋብቻው መፈጸሙን ስለማስታወቅ**

፩· ጋብቻው ሁለቱ ተጋቢዎች እና ከእያንዳንዱ ተጋቢ በኩል ሁለት፣ ሁለት ምስክሮች በተገኙበት በግልጽ ይፈጸማል ።

፪· ተጋቢዎቹና ምስክሮቹ ጋብቻ ለመፈጸም አስፈላጊ የሆኑትን ሁኔታዎች አለመጣሳቸውን በቃለ መሐላ ያረጋግጣሉ ።

፫· ተጋቢዎቹና ምስክሮቹ የመሐላ ቃል ከመስጠታቸው በፊት የሚሰጡት ቃል ስለሚያስከትለው ኃላፊነት የክብር መዝገብ ሹሙ በግልጽ ማስረዳት አለበት ።

www.abyssinialaw.com



፬· ሁለቱም ተጋቢዎች ጋብቻ ለመፈጸም መፍቀዳቸውን ለክብር መዝገብ ሹሙ በግልጽ ያረጋግጣሉ ።

፭· ሁለቱም ተጋቢዎችና ምስክሮቻቸው በክብር መዝገብ ላይ መፈረም አለባቸው ።

፮· ከዚህ በላይ የተገለጹት ሥርዓቶች የተፈጸሙ መሆናቸውን ሲያረጋግጥ የክብር መዝገብ ሹሙ ተጋቢዎቹ በሕጋዊ ጋብቻ የተሳሰሩ መሆናቸውን አስታውቆ ለተጋቢዎቹ የምስክር ወረቀት ይሰጣቸዋል።

አንቀጽ ፴፮· በኃይማኖትና በባህል ሥርዓት የሚፈጸም ጋብቻ

፩· በኃይማኖት ሥርዓት መሠረት ጋብቻ ሊፈጸም የሚችል በትና የአፈፃፀሙ ሥርዓት እንደየኃይማኖቱ ይወሰናል ።

፪· በባህል ሥርዓት መሠረት ጋብቻ ሊፈጸም የሚችልበትና የአፈፃፀሙ ሥርዓት በአካባቢው ባህል ይወሰናል ።

፫· በዚህ ሕግ ለማንኛውም የጋብቻ አፈፃፀም መሟላት አለባቸው የተባሉት ሁኔታዎች በኃይማኖትና በባህል ሥርዓት ለሚፈጸም ጋብቻም መሟላት አለባቸው ።

## ክፍል ፫
## ስለጋብቻ ምዝገባ

አንቀጽ ፴፯· ጋብቻን ስለማስመዝገብ

፩· ጋብቻው የተፈጸመው በማንኛውም የጋብቻ አፈፃፀም ሥርዓት ቢሆንም አግባብ ባለው የክብር መዝገብ ሹም ወይም አግባብ ባለው አካል መመዝገብ አለበት ።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ መሠረት ምዝገባውን ያከናወነ የክብር መዝገብ ሹም ለተጋቢዎቹ የጋብቻ ምስክር ወረቀት ይሰጣል ።

፫· ማንኛውም ጋብቻ ከተፈጸመበት ቀን ጀምሮ ውጤት ይኖረዋል ።

አንቀጽ ፴፰· የጋብቻ መዝገብ ስለማደራጀት

፩· በዚህ ሕግ አንቀጽ ፴፯ ንዑስ አንቀጽ /፩/ መሠረት ተጋቢዎቹ ጋብቻቸውን ያላስመዘገቡ ቢሆንም እንኳን የክብር መዝገብ ሹሙ አግባብ ባለው አካል ጋብቻ

www.abyssinialaw.com



፪· ይህ በሚሆንበት ጊዜ የክብር መዝገብ ሹሙ ተጋቢዎቹና እንደነገሩ ሁኔታ ምስክሮች ቀርበው በጋብቻ መዝገቡ ላይ እንዲፈርሙ ያደርጋል ።

አንቀጽ ፴፱· <u>የጋብቻው መዝገብ ይዘት</u>

የጋብቻ መዝገብ የሚያመለክተው ፤

ሀ) የተጋቢዎቹን ሙሉ ስም ፣ የተወለዱበትን ቀንና ቦታ የመኖሪያ አድራሻቸውን ፤

ለ) የምስክሮቹን ሙሉ ስም ፣ የተወለዱበትን ቀንና ቦታ፣ የመኖሪያ አድራሻቸውን ፤

ሐ) ጋብቻው የተፈጸመበትን ሥርዓት ፣ ቀንና ቦታ እንዲሁም የተመዘገበበትን ቀን ይሆናል ።

## ምዕራፍ ሦስት
## የጋብቻ ሁኔታዎች አለመሟላት የሚያስከትለው ውጤት

አንቀጽ ፴· የዕድሜ ሁኔታ

፩· በዚህ ሕግ አንቀጽ ፲፯ ንዑስ አንቀጽ ፪ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ዕድሜአቸው ከአሥራ ስምንት ዓመት በታች በሆኑት ሰዎች መካከል የተፈጸመ ጋብቻ በማና ቸውም ሰው ወይም በዐቃቤ ሕግ ጥያቄ ፣ እንዲፈርስ ይደረጋል ።

፪· ሕጉ የሚጠይቀው የጋብቻ ዕድሜ ከተሟላ በኋላ ጋብቻው እንዲፈርስ ጥያቄ ማቅረብም ሆነ መወሰን አይቻልም ።

አንቀጽ ፴፩· <u>የሥጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና</u>

በሥጋ ወይም በጋብቻ ዝምድና ምክንያት ጋብቻ እንዳይ ፈጸም የተደነገገውን ክልከላ በመተላለፍ የተፈጸመ ጋብቻ በማናቸውም ባለጉዳይ ወይም በዐቃቤ ሕግ ጥያቄ እንዲ ፈርስ ይደረጋል ።

አንቀጽ ፴፪· <u>በጋብቻ ላይ ጋብቻ</u>

፩· በጋብቻ ላይ ጋብቻ ተፈጽሞ ከተገኘ በመጀመሪያው

www.abyssinialaw.com



ወይም በሁለተኛው ተጋቢ ወይም በዐቃቤ ሕግ ጥያቄ የኋለኛው ጋብቻ እንዲፈርስ ይደረጋል።

፪· ሆኖም ከተጋቢዎቹ አንዱ ከሞተ የጋብቻ ማፍረስ ጥያቄው ቀሪ ሆኖ ሁለቱም ጋብቻዎች ሕጋዊ ውጤት ይኖራቸዋል።

አንቀጽ ፴፫· በፍርድ ክልከላ ምክንያት ጋብቻን ስለማፍረስ

፩· በፍርድ የተከለከለ ሰው ፍ/ቤት ሳይፈቅድ ጋብቻ ፈጽሞ ከተገኘ የተከለከለው ሰው ራሱ ወይም አሳዳሪው ጋብቻው እንዲፈርስ ጥያቄውን ለፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል ።

፪· የተከለከለው ሰው ጋብቻው እንዲፈርስ የሚያቀርበው ጥያቄ ክልከላው ከቀረበት ቀን ጀምሮ ስድስት ወር ካለፈ በኋላ ሊቀርብ አይችልም ።

፫· ጋብቻው እንዲፈርስ በአሳዳሪው የሚቀርበው ጥያቄ ጋብቻው መፈጸሙን ካወቀበት ቀን ጀምሮ ከስድስት ወር በኋላ ወይም በማናቸውም ምክንያት ቢሆን ክልከላው ከቀረ በኋላ ሊቀርብ አይችልም ።

አንቀጽ ፴፬· በኃይል ተግባር የተፈጸመውን ጋብቻ ስለማፍረስ

፩· ማንኛውም ሰው ተገዶ ጋብቻ ከፈጸመ ፣ ጋብቻው እንዲፈርስ ጥያቄውን ለፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል ።

፪· ስለዚህ ጉዳይ የሚቀርበው ጥያቄ የኃይል ሥራው ከቀረበት ከስድስት ወር በኋላ እና በማናቸውም ምክንያት ቢሆን ጋብቻው ከተፈጸመ ከሁለት ዓመት በኋላ ሊቀርብ አይችልም ።

አንቀጽ ፴፭· በስህተት ምክንያት የተፈጸመ ጋብቻን ስለማፍረስ

፩· ማንኛውም ሰው ከመሠረታዊ ስህተት በመነሳት ጋብቻ ከፈጸመ ጋብቻው እንዲፈርስ ጥያቄውን ለፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል ።

፪· ስለዚህ ጉዳይ የሚቀርበው ጥያቄ መሳሳቱን ካወቀበት ቀን ጀምሮ ከስድስት ወር በኋላ እና በማናቸውም ምክንያት ቢሆን ጋብቻው ከተፈጸመ ከሁለት ዓመት በኋላ ሊቀርብ አይችልም ።

www.abyssinialaw.com



አንቀጽ ፴፮· በብቸኝነት ለመኖር የተወሰነውን ጊዜ ስላለመጠበቅ

በዚህ ሕግ በአንቀጽ ፳፮ ንዑስ አንቀጽ /፩/ የተመለከተው በብቸኝነት ለመኖር የተወሰነው ጊዜ አልተከበረም በሚል ምክንያት ብቻ ጋብቻ እንዲፈርስ ጥያቄ ለማቅረብ አይቻልም ።

አንቀጽ ፴፯· የጋብቻ አስፈፃሚ ባለሥልጣን ሥልጣን የሌለው ስለመሆኑ

ጋብቻውን ያስፈጸመው ባለሥልጣን ሥልጣን አልነበ ረውም በማለት ብቻ ጋብቻው እንዲፈርስ ለመወሰን አይቻልም ።

አንቀጽ ፴፰ የሥነ ሥርዓት አለመጠበቅ

ጋብቻ አስፈፃሚው ባለሥልጣን የጋብቻ አፈፃፀም ሥርዓ ቶችን አልጠበቀም በማለት ጋብቻ እንዲፈርስ ሊወሰን አይችልም ።

## ምዕራፍ አራት
## የጋብቻ ውጤት
### ክፍል ፩
### ጠቅላላ

አንቀጽ ፴፱ ሁሉም የጋብቻ አፈፃፀም ሥርዓቶች ተመሳሳይ ውጤት ያላቸው ስለመሆኑ ፤

፩· በማናቸውም ዓይነት የጋብቻ አፈፃፀም ሥርዓት መሠረት የተፈጸመ ጋብቻ ከተፈጸመበት ቀን ጀምሮ ተመሳሳይ ሕጋዊ ውጤት ይኖረዋል ።

፪· በዚህ ረገድ ጋብቻ በክብር መዝገብ ሹም ፊት ወይም በሃይማኖት ወይም በባህል በታዘዙት ሥርዓቶች መሠረት የተፈጸመም ቢሆን ልዩነት አይደረግበትም።

አንቀጽ ፵ የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት መፈጸም

የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት በእውነት መፈጸሙ ወይም ተፈጽሟል ተብሎ መገመቱ ጋብቻው ለሚያስከትለው ውጤት አስፈላጊ አይደለም ።

www.abyssinialaw.com



አንቀጽ ፶፩/፩/ የጋብቻ ውል

፩· ተጋቢዎች ጋብቻቸው ንብረታቸውን በተመለከተ ስለሚ ያስከትለው ውጤት ጋብቻቸውን ከመፈጸማቸው በፊት ወይም እጅግ ቢዘገይ ጋብቻው በሚፈጸምበት ዕለት በውል መወሰን ይችላሉ ።

፪· እንዲሁም ግላዊ ግንኙነታቸውን በሚመለከት የሚኖሯ ቸውን መብቶችና ግዴታዎች በዚህ ውል መወሰን ይችላሉ ።

፫· በዚህ አንቀጽ ንውስ አንቀጽ (፩) መሠረት ተጋቢዎቹ የሚያደርጓቸው ውሎች አስገዳጅ የሕግ ድንጋጌዎችን የሚቃረኑ ሊሆኑ አይችሉም ።

አንቀጽ ፶፪/፪/ የተጋቢዎቹ ችሎታ ማጣት

፩· በፍርድ የተከለከለ ሰው የሚያደርገውን የጋብቻ ውል እርሱ ራሱ ካልፈጸመውና ፍርድ ቤት ካላፀደቀው በስተቀር ውጤት አይኖረውም ።

፪· በሕግ የተከለከለ ሰው ፤ የጋብቻ ውል መዋዋልን በተመ ለከተ ችሎታ እንዳለው ይቆጠራል ።

አንቀጽ ፶፫/፫/ የውሉ ፎርም

የጋብቻ ውል በጽሑፍ ካልተደረገና አራት ምስክሮች ፤ ሁለት በባል ወገን ሁለት በሚስት ወገን የፈረሙበት ካልሆነ በስተቀር ውጤት አይኖረውም።

አንቀጽ ፶፬/፬/ የውሉ ሠነድ ስለሚቀመጥበት ቦታ

፩· የጋብቻ ውሉ አንድ ቅጅ በፍርድ ቤት ወይም በክብር መዝገብ ሹም ዘንድ ይቀመጣል ።

፪· ተጋቢዎቹ ወይም ከተጋቢዎቹ አንዱ ለማየት በፈለጉ ጊዜ እንዲሁም በፍርድ ቤት ወይም ከተጋቢዎቹ በአንዱ የተፈቀደላቸው ሰዎች የውሉን ሠነድ ለማየት ይችላሉ ።

አንቀጽ ፶፭/፭/ ውል ለመዋዋል ስላለው የነፃነት ወሰን

፩· ተጋቢዎች በጋብቻቸው ውል ውስጥ በሌሎች ሦስተኛ ወገኖች ላይ ግዴታን የሚያስከትሉ ስምምነቶችን ማድረግ አይችሉም ።

www.abyssinialaw.com



፪· እንዲሁም ተጋቢዎቹ ባህልን ወይም ሃይማኖትን ወይም የአንድን አገር ሕግ በጥቅሉ በመጥቀስ ብቻ ተስማምተናል በማለት የሚያደርጉት የጋብቻ ውል ውጤት አይኖረውም ።

አንቀጽ ፶፯/፯/ የጋብቻ ውልን ስለማሻሻል

፩· የጋብቻ ውል እንዲሻሻል የቤተሰብን ጥቅም የሚጠይቅ ሲሆንና ተጋቢዎቹ ሲስማሙ ውሉን በማሻሻል ፍርድ ቤት እንዲያፀድቅላቸው መጠየቅ ይችላሉ ።

፪· ፍርድ ቤቱ በተጋቢዎቹ ተሻሽሎ የቀረበው የጋብቻ ውል የቤተሰቡን ጥቅም የማይጐዳ መሆኑን ሲያረጋግጥ የተሻሻለውን ውል ተቀብሎ ያፀድቃል ።

፫· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፪/ በተመለከተው ሁኔታ ፍርድ ቤቱ ውሉን ካፀደቀው የተሻሻለው ውል በፍርድ ቤት ወይም በክብር መዝገብ ሹም ዘንድ ይቀመጣል ።

አንቀጽ ፶፯/፯/ የሕግ ተፈፃሚነት

የጋብቻ ውል በሌለ ጊዜ ወይም የጋብቻ ውል ቢኖርም በሕግ ሳይፀና የቀረ እንደሆን ከዚህ ቀጥሎ ክፍል ፪ እና ፫ (በዚህ ምዕራፍ) የተመለከቱት ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ ።

## ክፍል ፪
## ጋብቻ በተጋቢዎች ግላዊ ግንኙነት ላይ ስለሚኖረው ውጤት

አንቀጽ ፶፰ መከባበር መተጋገዝና መደጋገፍ

፩· ባልና ሚስት እርስ በርሳቸው መከባበር ፣ መተጋገዝና መደጋገፍ አለባቸው ።

፪· በጋብቻ ውል ውስጥ ይህንን የሚቃረን ስምምነት ማድረግ አይችሉም ።

አንቀጽ ፶፱ የቤተሰብ የጋራ አመራር /፩/ ጠቅላላ

፩· በቤተሰብ አመራር ረገድ ባልና ሚስት እኩል መብት አላቸው ።

፪· ባልና ሚስት በማናቸውም ረገድ የቤተሰቡን ደህንነትና ጥቅም ለማስጠበቅ ፣ ልጆቻቸው በመልካም ሥነ–ምግባር

www.abyssinialaw.com



እንዲታነፁ ተገቢ ትምህርት እንዲቀስሙና ኃላፊነት የሚሰማቸው ዜጎች ሆነው እንዲያድጉ መተባበር አለባቸው ፡፡

አንቀጽ ፰ /፪/ ከተጋቢዎቹ አንዱ ቤተሰቡን ለመምራት ስላለመቻሉ

፩· ከባልና ከሚስቱ አንደኛው ችሎታ ያጣ ፣ የጠፋ ወይም ቤተሰቡን ጥሎ የሄደ ወይም ከመኖሪያ ሥፍራው በመራቁም ሆነ በማናቸውም ሌላ ምክንያት ፈቃዱን ለመስጠት በማይችልበት ሁኔታ በሚገኝበት ጊዜ በአንቀጽ ፶፱ የተመለከተውን የቤተሰብ አመራር አንደኛው ተጋቢ ብቻውን ይፈጽማል ፡፡

፪· ባልና ሚስቱ በጋብቻ ውላቸው ውስጥ ይህንን የሚቃረን ስምምነት ማድረግ አይችሉም ፡፡

አንቀጽ ፷፩ ከጋብቻ በፊት ከሌላ ስለተወለዱ ልጆች

፩· ከባልና ከሚስቱ አንዱ ከጋብቻው በፊት ከሌላ ሰው የወለዷቸውን ልጆች መልካም አስተዳደግ በሚመለከት በራሱ አሳብና መሪነት የፈቀደውን ውሣኔ ለማድረግ ይችላል ፡፡

፪· ይህንን የሚቃረን ማናቸውም ስምምነት ውጤት አይኖረውም ፡፡

አንቀጽ ፷፪ አብሮ መኖር

፩· ባልና ሚስት አብረው እንዲኖሩ ይገደዳሉ ፡፡

፪· ለጤናቸው አደገኛ ካልሆነ በስተቀር ባልና ሚስት ከጋብቻ የሚጠበቀውን መደበኛውን የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት መፈጸም አለባቸው ፡፡

፫· ይህንን የሚቃረን ማናቸውም ስምምነት ውጤት አይኖረውም ፡፡

አንቀጽ ፷፫ የመኖሪያ ሥፍራን ስለመወሰን

ባልና ሚስት የሚኖሩበትን ሥፍራ በጋራ ይወስናሉ፡፡

አንቀጽ ፷፬ በስምምነት ተለያይቶ ስለመኖር

፩· በዚህ ሕግ በአንቀጽ ፷፪ ንዑስ አንቀጽ /፩/ የተመለከተው ቢኖርም ፣ ባልና ሚስቱ ለተወሰነ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ

www.abyssinialaw.com



ተለያይተው ለመኖር መስማማት ይችላሉ።

፪· ስለዚህ ጉዳይ የተደነገገውን ስምምነት መለወጡ የማይገባ ካልሆነ በስተቀር ከሁለቱ ተጋቢዎች አንደኛው አስቦ ሊሰርዘው ይችላል ።

አንቀጽ ፷፭ የመተማመን ግዴታ

ባል ለሚስቱ ሚስት ለባልዋ ታማኝ የመሆን ግዴታ አለባቸው ።

## ክፍል ፫
## ጋብቻ በንብረት በኩል ስለሚኖረው ውጤት

አንቀጽ ፷፯ የባልና ሚስት የግል ሀብት /፩/ ያለግብይት የተገኙ ንብረቶች

ባልና ሚስቱ ጋብቻቸውን በሚፈጽሙበት ጊዜ በግል የነበሯቸው ንብረቶች ወይም ከጋብቻ በኋላ በውርስ ወይም በስጦታ በየግላቸው ያገኙዋቸው ንብረቶች የግል ንብረቶቻቸው ሆነው ይቀራሉ ።

አንቀጽ ፷፯ /፪/ በግብይት የተገኙ ንብረቶች

፩· ባልና ሚስት ከተጋቡ በኋላ አንዱ የግል ሀብቱ በሆነ ንብረት ለውጥ ያገኘው ወይም በግል ገንዘቡ የገዛቸው ወይም የግል ንብረቱን ሸጦ የሚያገኘው ገንዘብ የግል ሀብቱ ይሆናል ።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ የተመለከተው ድንጋጌ ተፈፃሚ የሚሆነው በግብይት የተገኘው ንብረት የግል ይባልልኝ ብሎ አንደኛው ወገን ጥያቄ ሲያቀርብ እና ፍርድ ቤቱ ሲያፀድቀው ብቻ ነው ።

አንቀጽ ፷፰ የግል ሀብትን ስለማስተዳደር /፩/ መሠረቱ

፩· እያንዳንዱ ተጋቢ የግል ሀብትን ራሱ ለማስተዳደርና ገቢውንም ለመቀበል ይችላል ።

፪· እያንዳንዱ ተጋቢ የግል ሀብቱን ራሱ ሊያዝበት ነፃነት አለው ።

www.abyssinialaw.com



**አንቀጽ ፷፱ /፪/ የግል ሀብት አስተዳደርን በጋብቻ ውል ስለመወሰን**

፩· ባልና ሚስት አንደኛው የሌላውን ተጋቢ የግል ሀብት በሙሉ ወይም በከፊል እንዲያስተዳድርለት እና እንደአስ ፈላጊነቱ እንዲያዝበት በጋብቻ ውላቸው ሊወስኑ ይችላሉ ።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ በተመለከተው አኳኋን ንብረት የማስተዳደር ሥልጣን የተሰጠው ተጋቢ በሌላኛው ተጋቢ ሲጠየቅ ስለንብረቱ አስተዳደር ዓመታዊ የሂሣብ መግለጫ የመስጠት ግዴታ አለበት ።

**አንቀጽ ፸ /፫/ ስለውክልና ሥልጣን**

ከተጋቢዎቹ አንዱ የግል ሀብቱን በሙሉ ወይም በከፊል እንዲያስተዳድርለት ለሌላኛው ተጋቢ ውክልና መስጠት ይችላል ።

**አንቀጽ ፸፩ የባልና ሚስት የጋራ ሀብት**

፩· ባልና ሚስት ከግል ጥረታቸውና ከግል ወይም ከጋራ ንብረታቸው የሚያገኙዋቸው ገቢዎች ሁሉ የጋራ ሀብቶ ቻቸው ይሆናሉ ።

፪· በዚህ ሕግ አንቀጽ ፷፰ ንዑስ አንቀጽ /፪/ መሠረት የአንደኛው ተጋቢ የግል ሀብት ነው ካልተባለ በስተቀር ባልና ሚስት ከተጋቡ በኋላ በግብይት የሚያገኙት ንብረት ሁሉ የጋራ ሀብታቸው ይሆናል።

፫· በስጦታው ውል ወይም በኑዛዜው ቃል በሌላ አኳኋን ካልተመለከተ በስተቀር ፣ በስጦታ ወይም በኑዛዜ ለተጋ ቢዎቹ የተሰጧቸው ንብረቶች ሁሉ የጋራ ሀብቶቻቸው ይሆናሉ ።

**አንቀጽ ፸፪ የሕግ ግምት**

፩· አንደኛው ተጋቢ የግል ሀብቱ መሆኑን ካላስረዳ በስተቀር ማንኛውም ንብረት በአንደኛው ተጋቢ ስም ብቻ የተመ ዘገበ ቢሆንም እንኳን የጋራ ሀብት እንደሆነ ይቆጠራል ።

፪· የግል ንብረት መሆኑን ሦስተኛ ወገኖች የሚያውቁት ወይም ሊያውቁት የሚገባ ካልሆነ በስተቀር፣ ባልና

www.abyssinialaw.com



ሚስቱ ወይም ከሁለቱ አንዱ ይኸው ንብረት የግል ነው በማለት በሦስተኛ ወገን ላይ መቃወሚያ አድርገው ሊያቀርቡት አይችሉም።

አንቀጽ ፷፫ ስለባልና ሚስት ገቢ /፩/ መደበኛ የገቢ አስተዳደር

፩· ባልና ሚስት እያንዳንዳቸው ገቢያቸውን በየራሳቸው ይቀበላሉ ።

፪· ባልና ሚስት በየግላቸው የሚያገኙትን ገቢ ፣ የግል ወይም የጋራ የባንክ ሂሣብ በመክፈት ማስቀመጥ ይችላሉ ።

፫· ከባልና ከሚስት አንደኛው ሲጠይቅ ፤ ሌላኛው ተጋቢ ያገኘውን የገቢ መጠን የማስታወቅ ግዴታ አለበት ።

አንቀጽ ፷፬ /፪/ ልዩ ሁኔታ

፩· ከባልና ከሚስቱ አንዱ ገቢውን ሌላኛው ተጋቢ እንዲቀበ ልለት ሥልጣን ለመስጠት ይችላል ።

፪· ከባልና ከሚስቱ በአንደኛው ጠያቂነት የአንደኛውን ገቢ ሌላኛው ተጋቢ እንዲቀበልና ለመቀበሉም ደረሰኝ እንዲሰጥ ፍርድ ቤት ሊወስን ይችላል ።

፫· በሌላ ሕግ በተለየ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር ፣ ከባልና ከሚስት የአንደኛው ገቢ በሙሉ ወይም በከፊል እንዲ ከበር በፍርድ ቤት ሊታዘዝ ይችላል ።

አንቀጽ ፷፭ የጋራ ሀብትን ስለማስተዳደር

፩· ከባልና ከሚስት አንዱ የጋራ ሀብታቸውን በሙሉ ወይም በከፊል እንዲያስተዳድር ግልጽ የሆነ ስምምነት ከሌለ በስተቀር ባልና ሚስቱ የጋራ ሀብታቸውን በጋራ ያስተዳ ድራሉ ።

፪· ከባልና ከሚስት አንዱ ችሎታ የለውም ተብሎ ሲወሰን ወይም ንብረት የማስተዳደር መብቱን ሲገፋ ወይም በሌላ በማናቸውም ምክንያት የጋራ ሀብታቸውን ለማስተ ዳደር የማይችል ሆኖ ሲገኝ ሌላኛው ተጋቢ የጋራ ሀብቱን የማስተዳደሩን ተግባር ያከናውናል ።

አንቀጽ ፷፮ የማስታወቅ ግዴታ

ከተጋቢዎቹ አንዱ ብቻ የጋራ ሀብታቸውን በሚያስተዳድ

www.abyssinialaw.com



ርበት ጊዜ የሀብቱን አስተዳደር በተመለከተ ለሌላኛው ተጋቢ መረጃ የመስጠት ግዴታ አለበት ።

አንቀጽ ፸፯ /፩/ የተጋቢዎቹ ስምምነት አስፈላጊ ስለመሆኑ

በሌላ ሕግ በተለየ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር ፣ በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ የተጋቢዎቹ ስምምነት አስፈላጊ ነው ፣

ሀ) የጋራ የሆነውን የማይንቀሳቀስ ንብረት ለመሸጥ ፣ ለመለወጥ ፣ ለማከራየት ፣ በመያዣ ወይም በዋስትና ለመስጠት ወይም በሌላ በማናቸውም ሁኔታ በዚሁ ንብረት ላይ ሌሎች ሰዎች መብት እንዲያገኙ ለማድረግ፣

ለ) ዋጋቸው ከብር ፭፻ /አምስት መቶ/ በላይ የሆኑ የሚንቀሳቀሱ ንብረቶችን ወይም የገንዘብ ሠነዶችን ለመሸጥ ፣ ለመለወጥ በመያዣ ወይም በዋስትና ለመስጠት ወይም በሌላ በማናቸውም ሁኔታ ለማስተላለፍ ፣

ሐ) ከብር ፩፻ /አንድ መቶ/ በላይ ዋጋ ያለውን የጋራ ንብረት ወይም ገንዘብ ለሌላ ሰው በስጦታ ለማስተላለፍ ።

መ) ከብር ፭፻ /አምስት መቶ/ በላይ ለመበደር ወይም ለማበደር ወይም ለሌላ ሰው ዋስ ለመሆን ።

አንቀጽ ፸፯ /፪/ የስምምነት አለመኖር ስለሚያስከትለው ውጤት

፩· አንደኛው ተጋቢ ከዚህ በላይ የተመለከተውን ድንጋጌ ባለማክበር የውል ግዴታ ገብቶ ከተገኘ ፣ ሌላኛው ተጋቢ ለፍርድ ቤት በሚያቀርበው ጥያቄ ግዴታው ሊፈርስ ይችላል ።

፪· ግዴታው እንዲፈርስ የሚቀርበው ጥያቄ ጠያቂው ወገን ግዴታው መገባቱን ከአወቀበት ቀን ጀምሮ ከስድስት ወር በኋላ ወይም በሌላ በማናቸውም ሁኔታ ግዴታው ከተገባ ከሁለት ዓመት በኋላ ሊቀርብ አይችልም ።

አንቀጽ ፸፰ የባልና የሚስት ዕዳ

፩· ከባል ወይም ከሚስት በግል የሚጠየቅ ዕዳ ከባለዕዳው ተጋቢ የግል ሀብት ፣ የግል ሀብቱ ዕዳውን ለመሸፈን በቂ በማይሆንበት ጊዜ ከጋራ ሀብታቸው ይከፈላል ።

፪· ዕዳው የመጣው ለትዳራቸው ጥቅም ከሆነ ከጋራ

www.abyssinialaw.com



ሀብታቸው የጋራ ሀብታቸው ዕዳውን ለመሸፈን በቂ በማይሆንበት ጊዜ ከባል ወይም ከሚስት የግል ሀብት ይከፈላል ።

አንቀጽ ፹ ለትዳር ጥቅም እንደተደረገ የሚቆጠር ዕዳ

የሚከተሉት ዕዳዎች ለትዳር ጥቅም እንደተደረጉ የሚቆጠሩ ናቸው ፤

ሀ) ለባልና ለሚስት እንዲሁም ለልጆቻቸው የዕለት ኑሮ አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮች ለማሟላት የተገቡ ዕዳዎች ፤

ለ) ባል ወይም ሚስት ቀለብ ለመስጠት ያለባቸውን ግዴታ ለመወጣት የተደረጉ ወጪዎች ፤

ሐ) ከባልና ከሚስት በአንደኛው ወይም በዕዳ ጠያቂው አመልካችነት ለትዳር ጥቅም ስለመሆኑ ፍርድ ቤት የተቀበለው ሌላ ዕዳ ።

አንቀጽ ፹፩ የትዳር ወጪዎችን ስለመሸፈን

ተጋቢዎች የትዳራቸውን ወጪ ለመሸፈን እያንዳንዳቸው እንደየአቅማቸውና ችሎታቸው አስተዋጽኦ ማድረግ አለባቸው ።

አንቀጽ ፹፪ በተጋቢዎቹ መካከል ስለሚደረጉ ውሎች

ባልና ሚስቱ ተጋብተው በሚኖሩበት ጊዜ በመካከላቸው የሚያደርጓቸው ውሎች ፍርድ ቤት ካላፀደቃቸው በስተቀር ውጤት አይኖራቸውም ።

## ምዕራፍ አምስት
## ስለጋብቻ መፍረስ
### ክፍል ፩
### ጠቅላላ

አንቀጽ ፹፫ በማናቸውም ዓይነት የጋብቻ አፈፃፀም ሥርዓት የተቋቋሙ ጋብቻዎች እኩል ስለመሆናቸው

፩· ጋብቻው የተፈጸመበት ሥርዓት ማናቸውም ዓይነት ቢሆን የጋብቻው መፍረስና የሚያስከትለው ውጤት አንድ ዓይነት ነው ።

፪· ጋብቻው የተፈጸመው በማናቸውም የጋብቻ አፈፃፀም

www.abyssinialaw.com



ሥርዓት ቢሆንም የጋብቻውን መፍረስ በተመለከተ ማናቸውም ልዩነት አይደረግም ።

አንቀጽ ፸፩ ጋብቻ ስለሚፈርስባቸው ምክንያቶች

ጋብቻ የሚፈርሰው በሚከተሉት ምክንያቶች ነው ፤

ሀ) ከተጋቢዎቹ አንዱ ሲሞት ወይም በፍርድ ቤት የመጥፋት ወይም የመሞት ውሳኔ ሲሰጥ ፤ ወይም

ለ) ጋብቻ ለመፈጸም መሟላት ካለባቸው ሁኔታዎች አንዱ በመጣሱ ምክንያት በሕግ መሠረት ጋብቻው እንዲፈርስ ሲወሰን ፤ ወይም

ሐ) የፍቺ ውሳኔ ሲሰጥ ።

አንቀጽ ፸፪ ፍቺ ስለሚወሰንበት ሁኔታ

ጋብቻ በፍቺ እንዲፈርስ ሊወሰን የሚችለው ፤

ሀ) ባልና ሚስት በስምምነት ለመፋታት ሲወስኑና ይህንኑ ለፍርድ ቤት አቅርበው ውሳኔያቸው ተቀባይነት ሲያገኝ ወይም

ለ) ከተጋቢዎቹ አንዱ ወይም ሁለቱ ተጋቢዎች በአንድነት ጋብቻቸው በፍቺ እንዲፈርስ ለፍርድ ቤት ጥያቄ ሲያቀርቡ ነው ።

## ክፍል ፪
## በስምምነት ስለመፋታት

አንቀጽ ፸፫ በስምምነት ለመፋታት ስለሚቀርብ ጥያቄ

፩· ባልና ሚስት በስምምነት ለመፋታት የወሰኑ እንደሆነ የፍቺ ስምምነታቸውንና ፍቺው የሚያስከትለውን ውጤት በጽሑፍ ለፍርድ ቤት በማቅረብ ፍቺው እንዲፀድቅላቸው መጠየቅ ይችላሉ ።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ የተመለከተው ቢኖርም ተጋብተው ስድስት ወር ያልሞላቸው ባልና ሚስት በስም ምነት ለመፋታት አይፈቀድላቸውም ።

፫· ባልና ሚስት ለፍርድ ቤት በሚያቀርቡት የፍቺ ስምምነት ላይ ለመፋታት የወሰኑበትን ምክንያት እንዲገልጹ አይገ ደዱም ።

www.abyssinialaw.com



**አንቀጽ ፹፮ የፍርድ ቤት ሥልጣን**

፩· በዚህ ሕግ በአንቀጽ ፹፮ ንዑስ አንቀጽ /፩/ በተመለከተው ድንጋጌ መሠረት የመፋታት ጥያቄ ሲቀርብለት ፍርድ ቤቱ ባልና ሚስቱን በተናጠል ወይም በአንድ ላይ በማስቀረብ ስለጥያቄያቸው ያነጋግራቸዋል ፣ እንዲሁም የመፋታት ሃሣባቸውን እንዲለውጡ ይጠይቃቸዋል ።

፪· ባልና ሚስቱ የመፋታት ሃሣባቸውን የማይለውጡ መሆኑን የገለጹ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ እንደነገሩ ሁኔታ ከሦስት ወር የማይበልጥ የማሰላሰያ ጊዜ በመወሰን ሊያሰናብታቸው ይችላል ።

**አንቀጽ ፹፯ ጉዳዩን እንደገና ስለማንቀሳቀስ**

፩· ባልና ሚስቱ በዚህ ሕግ በአንቀጽ ፹፮ ንዑስ አንቀጽ /፪/ የተመለከተው የማሰላሰያ ጊዜ ቢሰጣቸውም እንኳን በመፋታት ሃሣባቸው ከፀኑ የተሰጣቸው የማሰላሰያ ጊዜ ከአበቃበት ቀን ጀምሮ በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ጉዳያቸውን እንደገና በማንቀሳቀስ የፍቺ ስምምነታ ቸውን እንዲያፀድቅላቸው ፍርድ ቤቱን መጠየቅ ይችላሉ።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ የተመለከተው የስድስት ወር የጊዜ ገደብ ቢኖርም ባልና ሚስቱ አዲስ የፍቺ ስምምነት ከማቅረብ የሚያግዳቸው አይሆንም ።

**አንቀጽ ፹፰ የፍቺ ስምምነቱን ስለማጽደቅ**

፩· ፍርድ ቤቱ የፍቺ ስምምነቱን የሚያፀድቀው የባልና ሚስቱ ትክክለኛ ፍላጐት መሆኑን እና ባልና ሚስቱ ፈቃዳቸውን በነፃ የሰጡ መሆኑን ፣ እንዲሁም ስምምነቱ ከሕግና ሞራል ጋር የማይቃረን መሆኑን ሲያምን ብቻ ነው ።

፪· ፍርድ ቤቱ የፍቺውን ስምምነት ያፀደቀው እንደሆነ ስለፍቺው ውጤት ያደረጉትንም ስምምነት አብሮ ያፀድቃል ።

፫· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፪/ የተመለከተው ቢኖርም ባልና ሚስቱ ስለፍቺው ውጤት ያደረጉት ስምምነት

www.abyssinialaw.com



የልጆቻቸውን ደህንነትና ጥቅም በበቂ ሁኔታ የማያስጠብቅ ወይም የአንደኛውን ተጋቢ ጥቅም የሚጐዳ ሆኖ ካገኘው ፍርድ ቤቱ የፍቺውን ስምምነት ብቻ በማጽደቅ የፍቺውን ውጤት በተመለከተ ጉድለቶቹ እንዲስተካከሉ ተገቢ መስሎ የታየውን ውሣኔ ይሰጣል ።

## ክፍል ፫
## ጥያቄ በመቅረቡ ምክንያት ስለሚወሰን ፍቺ

**አንቀጽ ፺ /፩/ የፍቺ ጥያቄ ስለማቅረብ**

፩· ከባልና ሚስት አንደኛው ወይም ሁለቱም ተጋቢዎች በአንድነት በመሆን ጋብቻቸው በፍቺ እንዲፈርስ ለፍርድ ቤት ጥያቄ ማቅረብ ይችላሉ ።

፪· ከባልና ሚስት አንደኛው ወይም ሁለቱም ተጋቢዎች በአንድነት በመሆን የፍቺ ጥያቄ ሲያቀርቡ ፍቺ ለመጠየቅ ምክንያት የሆናቸውን ጉዳይ መግለጽ ይችላሉ።

**አንቀጽ ፺፩ /፪/ የፍርድ ቤት ሥልጣን**

፩· በዚህ ሕግ አንቀጽ ፺ መሠረት ጋብቻው በፍቺ እንዲፈርስ ጥያቄ ሲቀርብለት ፣ ፍርድ ቤቱ ባልና ሚስቱን በተና ጠልም ሆነ በአንድነት በማነጋገር የፍቺው ጥያቄ የሚቀር በትንና አለመግባባቱን በስምምነት ለመፍታት የሚችሉ በትን ሁኔታ ለመፍጠር እንዲችሉ ያግባባቸዋል ።

፪· ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ በተመለ ከተው መሠረት ምክሮ ውጤት ያላገኘ እንደሆነ ወይም እንደነገሩ ሁኔታ ውጤት የማያገኝ መስሎ የታየው እንደሆነ ባልና ሚስቱ ከፍርድ ቤት ውጭ ራሳቸው በሚመርጧቸው ሽማግሌዎች አማካይነት ጉዳያቸውን በእርቅ እንዲጨርሱ ሊጠይቃቸው ይችላል ።

፫· ባልና ሚስቱ ጉዳያቸውን በሽማግሌ አማካይነት በእርቅ ለመጨረስ ያልተስማሙ ከሆነ ፍርድ ቤቱ ከሦስት ወር ያልበለጠ የማሰላሰያ ጊዜ በመወሰን ሊያሰናብታቸው ይችላል ።

፬· ከዚህ በላይ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት የተገ

www.abyssinialaw.com



ቢውን ሁሉ አድርጐ ጥረቱ ውጤት ካላገኘ ፍርድ ቤቱ የአስታራቂ ሽማግሌዎች ሪፖርት ከደረሰው ወይም እንደሁኔታው ለተጋቢዎቹ የተወሰነው የማሰላሰያ ጊዜ ከአበቃበት ቀን ጀምሮ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ የፍቺ ውሣኔ ይሰጣል ።

አንቀጽ ፺፪ /፫/ ለጊዜው የሚሰጡ ትዕዛዞች

፩· የፍቺ አቤቱታ ሲቀርብ ወይም በጋብቻ ውስጥ የሚፈጠር አለመግባባት በአስታራቂ ሽማግሌዎች በሚታይበት ወቅት ፍርድ ቤቱ ወዲያውኑ ባልና ሚስቱ ስለሚተዳደሩ በትና ስለሚኖሩበት ሁኔታ ስለልጆቻቸው አጠባበቅ ፣ ስለሚኖሩበት ሥፍራና ስለአኗኗራቸው እንዲሁም ስለን ብረታቸው አስተዳደር ተገቢ መስሎ የታየውን ትዕዛዝ ይሰጣል ።

፪· ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ በተመለ ከተው መሠረት ትዕዛዝ በሚሰጥበት ጊዜ ከሁለቱ ተጋቢዎች የአንዳቸው ከጋራ መኖሪያቸው መውጣት የግድ ሆኖ ከተገኘ የጋራ መኖሪያቸውን ለቆ ቢወጣ የባሰ ጉዳት የሚደርስበት ወገን የትኛው መሆኑን እንዲሁም የልጆችን ጥቅም ለማስጠበቅ አመቺ የሚሆነውን ሁኔታ ሁሉ ከግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል ።

አንቀጽ ፺፫ የፍቺ ውጤቶችን ስለመወሰን

፩· በዚህ ክፍል መሠረት ጋብቻው በፍቺ ከፈረሰ ፣ ፍርድ ቤቱ ፍቺው ስለሚያስከትለው ውጤት እንዲስማሙ ባልና ሚስቱን ይጠይቃቸዋል ።

፪· ባልና ሚስቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ መሠረት ለመስማማት ያልፈለጉ ወይም ለመስማማት ሞክረው ስምምነት ላይ ለመድረስ ካልቻሉ ፍርድ ቤቱ በሚሾ ማቸው ባለሙያዎች አማካይነት ወይም አመቺ መስሎ በሚታየው በማናቸውም ዘዴ የፍቺውን ውጤት ይወስናል ።

፫· የፍቺው ውጤት በስምምነት በሚያልቅበት ወይም በሽማ ግሌዎች ወይም በባለሙያዎች በሚወሰንበት ጊዜ ውሣኔው ተፈፃሚነት የሚኖረው ለፍርድ ቤቱ ቀርቦ

www.abyssinialaw.com



ተቀባይነት ሲያገኝ ብቻ ነው ፡፡

፬· ፍርድ ቤቱ ፍቺውን አስቀድሞ በመወሰን የፍቺውን ውጤት በተመለከተ የሚሰጠውን ውሣኔ እንደ ሁኔታው ከፍቺ በኋላ ከስድስት ወር ላልበለጠ ጊዜ ሊያዘገየው ይችላል ፡፡

አንቀጽ ፺፬ ስለካሣ (፩) መሠረቱ

፩· ከባልና ከሚስት አንዱ ለፍቺው ምክንያት የሆነውን በደል ፈጽሞ ከተገኘ ፍርድ ቤቱ ለፍትሕ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በሌላው ተጋቢ ላይ ስለደረሰው ጉዳት በዳዩ ተመጣጣኝ የሆነ ካሣ እንዲከፍል ሊወስን ይችላል ፡፡

፪· ስለ ካሣ አከፋፈል አንደኛው ተጋቢ በሌላው ላይ በደል ፈጽሞአል የሚባለው ፣

ሀ) የመከባበር ፣ የመተጋገዝ ፣ የመደጋገፍ ግዴታን ሲጥስ ፣

ለ) አብሮ የመኖር ግዴታን ያለበቂ ምክንያት ሲጥስ ፣

ሐ) የታማኝነትን እና የመሳሰሉትን ሌላ የአንድ ወገን ግዴታ ጥሶ ከተገኘ ነው ፡፡

አንቀጽ ፺፭ /፪/ የካሣው መጠን

፩· ፍርድ ቤቱ የካሣውን መጠን የሚወስነው የጥፋቱን ክብደት ግምት ውስጥ በማስገባት በርትዕ ነው ፡፡

፪· ስለሆነም የካሣው መጠን ከብር ፲ሺህ (አሥር ሺህ ብር) መብለጥ የለበትም ፡፡

፫· ፍርድ ቤቱ የታማኝነት ግዴታ ወይም አብሮ የመኖር ግዴታ የጣሰው ተጋቢ ሌላውን ተጋቢ ለመጉዳት መሆኑን ሲያረጋግጥ አብላጫውን የንብረት ድርሻ ለተጐጂው ሊወስን ይችላል ፡፡

## ምዕራፍ ስድስት
## የባልና ሚስትን ሀብት ስለማጣራት

አንቀጽ ፺፮ የባልና ሚስትን ሀብት በስምምነት ስለማጣራት

፩· በዚህ ሕግ ስለካሣ ከፍ ያ የተደነገጉት ድንጋጌዎች እንደተ ጠበቁ ሆነው ጋብቻው በዚህ ሕግ ድንጋጌዎች መሠረት ከፈረሰ ባልና ሚስቱ የጋብቻው መፍረስ በንብረት በኩል

www.abyssinialaw.com



የሚያስከትለውን ውጤት አስመልክተው በሚያደርጉት ስምምነት ወይም በጋብቻ ውላቸው መሠረት ይጣራል ፡፡

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ የተመለከተው የጋብቻ ውል ወይም ስምምነት የሌለ ወይም በሕግ ፊት የማይፀና ሆኖ ከተገኘ የባልና ሚስት ሀብት በሚከተሉት ድንጋጌዎች መሠረት ይጣራል ፡፡

አንቀጽ ፺፯ የግል ሀብትን መልሶ ስለመውሰድ

፩· ባል ወይም ሚስት የግሉ መሆኑን በማስረዳት የግል ሀብቱ የሆነውን ንብረቱን መልሶ የመውሰድ መብት ይኖረዋል ፡፡

፪· ከባልና ሚስቱ አንደኛው የግል ሀብቱ የሆነ ማናቸውም ንብረት ለሌላ ሰው የተላለፈ መሆኑና ከዚሁ ግብይት የተገኘውም ገንዘብ ከጋራ ሀብታቸው ጋር የተቀላቀለ መሆኑን ያስረዳ እንደሆን ፣ ከዚህ ንብረት ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ገንዘብ ወይም ንብረት ከጋራ ሀብታቸው በቅድሚያ የማንሳት መብት ይኖረዋል ፡፡

፫· ባልና ሚስት የየግል ሀብታቸውን የሚያነሱበት ሁኔታ ሲኖር ሁለቱም በመጨረሻ ከተገኘው የንብረት መጠን እንደየአስተዋጽኦዋቸው ሊደርሳቸው የሚችለውን ያህል የማንሳት መብት ይኖራቸዋል ፡፡

አንቀጽ ፺፰ ስለካሣ

፩· በዚህ ሕግ መሠረት የጋራ ንብረቱን ወይም የሌላኛውን ተጋቢ ንብረት በብቸኝነት እንዲያስተዳድር ሥልጣን የተሰጠው ተጋቢ ፣ ከተሰጠው ሥልጣን ውጭ በፈጸ ማቸው ድርጊቶች ምክንያት ወይም ከብልሹ አስተዳደር የተነሣ ወይም የካሣ ጠያቂውን መብት በማታለል ድርጊቱ የጐዳ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ በተበዳዩ ጥያቄ ሲቀርብለት ተገቢ የጉዳት ካሣ እንዲከፈለው ሊያዝ ይችላል ፡፡

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ መሠረት የሚቀርብ የካሣ ጥያቄ ተፈጸመ የተባለው ድርጊት ጋብቻው ከመፍረሱ ከአምስት ዓመት በፊት የሆነ እንደሆነ ተቀባ ይነት አይኖረውም ፡፡

www.abyssinialaw.com



**አንቀጽ ፺፬ ያለአግባብ ስለመበልጸግ**

ባልና ሚስት ተቃራኒ ስምምነት ካላደረጉ በስተቀር አንደኛው ተጋቢ ሌላው ተጋቢ በግል ንብረቱ ወይም በጋራ ሀብታቸው ያለአግባብ መበልፀጉን ካስረዳ ፍርድ ቤቱ ተገቢ ካሣ እንዲከፈለው ሊያዝ ይችላል ።

**አንቀጽ ፩፻ የዕዳ ጠያቂዎችን መብት ስለማስከበር**

ከባልና ሚስት አንደኛው ወይም ሁለቱም በጋራ በፍርድ የተረጋገጠባቸው ወይም ሁለቱም ያመኑት ዕዳ መኖሩ የታወቀ እንደሆነ ይኸው ዕዳ የባልና ሚስት ሀብት ከመከፋፈሉ በፊት ተቀንሶ ይከፈላል ።

**አንቀጽ ፩፻፩ /፩/ የጋራ ሀብትን ስለማከፋፈል**

ከዚህ በላይ የተመለከቱትና የባልና ሚስት ሀብትን በስምምነት ስለማከፋፈል የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆነው፤ የባልና ሚስት የጋራ ሃብት ለሁለቱም እኩል የሚከፋፈል ይሆናል።

**አንቀጽ ፩፻፪ /፪/ የባልና ሚስት ሀብት በዓይነት የሚከፋፈል ስለመሆኑ**

፩· በመሠረቱ እያንዳንዱ ተጋቢ ከጋራ ሀብቱ የተወሰነ ንብረት እንዲደርሰው በማድረግ የጋራ ሀብቱ በዓይነት እንዲከፋፈል ይደረጋል።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ በተመለከተው አኳኋን እኩል ለማከፋፈል የማይቻል ሆኖ የተገኘ እንደሆነ፣ ልዩነቱ በገንዘብ እንዲካካስ ይደረጋል።

፫· የሀብት ክፍፍሉ በሚደረግበት ጊዜ እያንዳንዱ ተጋቢ ይበልጥ ጠቃሚነት ያላቸውን ንብረቶች እንዲያገኝ ለማድረግ ጥረት መደረግ ይኖርበታል።

**አንቀጽ ፩፻፫ /፩/ ለማከፋፈል አዳጋች ስለሆኑ ንብረቶች**

፩· ንብረቱ ለክፍፍል የማያመች ወይም ለማከፋፈል የማይቻል ሆኖ የተገኘ እንደሆነና ባልና ሚስቱን ንብረቱ ከሁለቱ ለአንዳቸው እንዲሰጥ ለማስማማት ሳይቻል የቀረ እንደሆነ ንብረቱ ተሸጦ የተገኘውን ገንዘብ እንዲከፋፈል ይደረጋል።

www.abyssinialaw.com



፪· ስለአሻሻጡ ሁኔታ ባልና ሚስቱ ሳይስማሙ ቀርተው አንደኛው ጥያቄ ያቀረበ እንደሆነ ሽያጩ የሚደረገው በጨረታ ይሆናል።

አንቀጽ ፩፻፴ /፪/ ደመወዝና ጡረታ የማይከፋፈል ስለመሆኑ

፩· ደመወዝና የጡረታ ክፍያ በፍቺ ጊዜ አይከፋፈልም።

፪· ሆኖም ጋብቻ በሞት ምክንያት ሲፈርስ በልዩ ሕግ ስለባልና ሚስት ድርሻ የተወሰነው የተጠበቀ ነው።

አንቀጽ ፩፻፳ ጋብቻው ከፈረሰ በኋላ ከባልና ሚስት ስለሚጠበቅ ዕዳ

፩· ጋብቻው ከፈረሰና የባልና ሚስት ሀብት ከተከፋፈለ በኋላ የሚጠየቅ ዕዳ በጋራ መከፈል የነበረበት በሆነ ጊዜ ስለዕዳው አከፋፈል ሁለቱም በየድርሻቸው መጠን ተጠያቂ ይሆናሉ።

፪· ዕዳው የሚመለከተው አንደኛውን ተጋቢ ከሆነ የዕዳው ክፍያ ሊጠየቅ የሚችለው ባለዕዳ ከሆነው ተጋቢ ብቻ ይሆናል።

ምዕራፍ ሰባት

ጋብቻ መፈጸሙን ለማስረዳት ስለሚቀርቡ ማስረጃዎች

አንቀጽ ፩፻፺፮ የጋብቻ ምስክር ወረቀት

፩· ጋብቻ መፈጸሙን ለማስረዳት የሚቻለው ጋብቻው በተፈጸመበት ዕለት ወይም ከዚህ በኋላ በሕጉ መሠረት ተዘጋጅቶ የተሰጠውን የጋብቻ ምስክር ወረቀት በማቅረብ ነው።

፪· የክብር መዝገብ ሹም ባልተቋቋመበት ሥፍራ በመንግሥት የሚወከል አካል የሚሰጠው ማስረጃ እንደ ጋብቻ ምስክር ወረቀት ይቆጠራል።

አንቀጽ ፩፻፺፯ የጋብቻ ምስክር ወረቀት በሌለ ጊዜ ስለሚቀርብ ማስረጃ

የጋብቻ ምዝገባ ሳይደረግ የቀረ ወይም መዝገቡ በመጥፋቱ ምክንያት ጋብቻ መፈጸሙን በጋብቻ ምስክር ወረቀት ለማስረዳት ያልተቻለ እንደሆነ፣ ጋብቻ ለመፈጸሙ የትዳር ሁኔታ መኖሩን በማረጋገጥ ማስረዳት ይቻላል።

www.abyssinialaw.com



**አንቀጽ ፩፻፰ የትዳር ሁኔታ መኖር /፩) ትርጓሜ**

አንድ ወንድና አንዲት ሴት የትዳር ሁኔታ አላቸው የሚባሉት ራሳቸውን እንደባልና ሚስት የሚቆጥሩና ከሦስቱ በአንዱ የጋብቻ ሥርዓት መሠረት የሚኖሩ ከመሆናቸውም በላይ ቤተዘመዶቻቸውና ማኅበረሰቡ እንደባልና ሚስት የሚቀበሏቸው ሆነው ሲገኙ ነው።

**አንቀጽ ፩፻፱ /፪/ የትዳር ሁኔታ መኖርን ስለማስረዳት**

፩· የትዳር ሁኔታ መኖሩን ለማስረዳት የሚቻለው አራት ምስክሮችን በማቅረብ ነው።

፪· ምስክሮቹ ጋብቻ ሲፈጸም የነበሩ መሆን አለባቸው።

፫· የትዳር ሁኔታ አለመኖሩን ለማስረዳት የሚቻለው አራት የመከላከያ ምስክሮችን በማቅረብ ነው።

፬· የትዳር ሁኔታን ለማስረዳት ወይም አለመኖሩን ለማስረዳት ከምስክሮች በተጨማሪ ሌሎች ማስረጃዎችን ማቅረብ ይቻላል።

**አንቀጽ ፩፻፲ /፫/ ጋብቻ ለመፈጸሙ የትዳር ሁኔታ መኖርን ስለማስረዳት**

፩· ከዚህ በላይ በተመለከተው አንቀጽ መሠረት አንድ ሰው በራሱና ከእርሱ ጋር ጋብቻ አለኝ ከሚለው ወገን ጋር የትዳር ሁኔታ መኖሩን ለማስረዳት የቻለ እንደሆነ፣ ፍርድ ቤቱ ጋብቻ ተፈጽሞአል ሲል የሕግ ግምት ይወስዳል።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ የተመለከተውን ግምት ጋብቻው አለመፈጸሙን ማናቸውንም ዓይነት አስተማማኝ ማስረጃ በማቅረብ ለማፍረስ ይቻላል።

## ምዕራፍ ስምንት

## ጋብቻ ሳይፈጸም እንደ ባልና ሚስት አብሮ ስለመኖር

**አንቀጽ ፩፻፲፩ /፩/ ትርጓሜ**

ጋብቻ ሳይፈጸም እንደባልና ሚስት አብሮ መኖር ማለት አንድ ወንድና ሴት በሕግ በሚፀና አኳኋን ጋብቻ ሳይፈጸሙ በትዳር መልክ የኖሩ ሲሆን ነው።

www.abyssinialaw.com

አንቀጽ ፩፻፲፪ /፪/ ማብራሪያ

፩· ጋብቻ ሳይፈጽሙ እንደባልና ሚስት አብረው ኖሩ ለማለት ወንድየውና ሴትየዋ የሚያሳዩት ሁኔታ በሕግ እንደተጋቡ ሰዎች ዓይነት መሆኑ አስፈላጊና በቂ ነው።

፪· ለሦስተኛ ወገኖች እንደተጋቡ ሆነው መቅረብ አስፈላጊ አይደለም።

፫· አንድ ወንድና አንዲት ሴት በታወቀና በተደጋገመ ሁኔታ የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት መፈጸማቸው ብቻ በሁለቱ መካከል ጋብቻ ሳይፈጸም እንደባልና ሚስት ግንኙነት አላቸው ለማለት በቂ ምክንያት አይደለም።

አንቀጽ ፩፻፲፫ የጋብቻ ዝምድና የማያስከትል ስለመሆኑ

፩· ጋብቻ ሳይፈጽሙ እንደባልና ሚስት አብሮ መኖር በወንድየውና በሴቲቱ የሥጋ ዘመዶች መካከል እንዲሁም በሴትየዋና በወንድየው የሥጋ ዘመዶች መካከል አንዳችም የጋብቻ ዝምድና አያስከትልም።

፪· ሆኖም የጋብቻ ዝምድና ባለ ጊዜ፣ ጋብቻን የሚከለክሉ ድንጋጌዎች ጋብቻ ሳይፈጸም እንደባልና ሚስት አብሮ መኖር ባለጊዜም ተፈፃሚ ይሆናል።

አንቀጽ ፩፻፲፬ የጋብቻ ሁኔታዎች በከፊል ተፈፃሚ ስለመሆኑ

ዝምድና ባላቸው ሰዎች መካከል የተደረገው የጋብቻ ክልከላ እና የጋብቻ ዝቅተኛ ዕድሜ ጋብቻ ሳይፈጸም እንደባልና ሚስት አብሮ በመኖር ጊዜ ተፈፃሚ ይሆናሉ።

አንቀጽ ፩፻፲፭ የጋራ ኑሮ ወጪዎችን ስለመሸፈን

ጋብቻ ሳይፈጽሙ እንደባልና ሚስት አብረው የሚኖሩ ሰዎች የጋራ ኑሮአቸውን ወጪ ለመሸፈን እያንዳንዳቸው እንደየአቅማቸውና ችሎታቸው አስተዋጽኦ ማድረግ አለባቸው።

አንቀጽ ፩፻፲፮ ስለጋራ ሀብት

፩· የንብረት አስተዳደራቸውን አስመልክቶ የሚያደርጉት ውል እንደተጠበቀ ሆኖ ጋብቻ ሳይፈጽሙ እንደ ባልና

www.abyssinialaw.com



ሚስት አብረው የሚኖሩ ሰዎች ከሦስት ዓመት ላላነሰ ጊዜ አብረው ከኖሩ በግንኙነቱ ውስጥ እያሉ ያፈሩዋቸው ንብረቶች የጋራ ሀብታቸው ይሆናሉ።

፪· ተቃራኒ ማስረጃ እስካልቀረበ ድረስ አብረው በመኖር ላይ እያሉ የሚኖራቸው ንብረቶች በግንኙነቱ ውስጥ የተፈሩ ሀብቶች ተደርገው ይቆጠራሉ።

፫· ጋብቻ ሳይፈጽሙ እንደባልና ሚስት አብረው የሚኖሩ ወንድና ሴት የሚገቧቸው ዕዳዎች አብረው በሚኖሩበት ጊዜ ለጋራ ኑሮአቸው ወይም ከግንኙነቱ የተወለዱ ልጆችን መሠረታዊ ፍላጎቶች ለማሟላት ሲባል የተገቡ ዕዳዎች ሲሆኑ፣ ለዕዳዎቹ አከፋፈል ሁለቱም በአንድነትና በነጠላ ኃላፊዎች ይሆናሉ።

## አንቀጽ ፩፻፲፯ የጋራ ንብረት ስለሚያስከትለው ውጤት

በዚህ ሕግ በአንቀጽ ፩፻፲፮ ንዑስ አንቀጽ /፩/ በተመለከተው መሠረት የጋራ ሀብት በሚፈጠርበት ጊዜ ስለንብረቱ አስተዳደር፣ የሦስተኛ ወገን ዕዳ አከፋፈልና ንብረት ማጣራት ሂደት በዚህ ሕግ በጋብቻ ስለሚፈጠር የጋራ ንብረትና የማጣራት ሂደት የተነገሩት ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል። /አንቀጽ ፺፮–፩፻፰/

## አንቀጽ ፩፻፲፰ የልጆች መወለድ

ጋብቻ ሳይፈጸም እንደባልና ሚስት አብረው ከሚኖሩ ወንድና ሴት የተወለዱ ልጆች ተወላጅነታቸው የሚረጋገጠው በዚህ ሕግ ስለመወለድ በተመለከተው ምዕራፍ ውስጥ በተደነገገው መሠረት ይሆናል።

## አንቀጽ ፩፻፲፱ የግንኙነት መቋረጥ

፩· ጋብቻ ሳይፈጽሙ እንደባልና ሚስት አብረው የሚኖሩ ወንድና ሴት በማንኛውም ጊዜ ግንኙነታቸው እንዲቋረጥ ማድረግ ይችላሉ።

፪· በዚህ ሕግ በአንቀጽ ፩፻፲፮ ስለጋራ ሀብት የተነገረው እንደተጠበቀ ሆኖ ግንኙነቱ እንዲቋረጥ ያደረገው ወገን ጥፋት ካልፈጸመ በስተቀር ካሣ እንዲከፍል አይገደድም።

www.abyssinialaw.com


አንቀጽ ፩፻፭ <u>የግንኙነት ማስረጃ</u>

፩· ጋብቻ ሳይፈጽሙ እንደባልና ሚስት አብሮ መኖርን የግንኙነቱ ሁኔታ መኖሩን በማረጋገጥ በቂ ምስክሮች በማቅረብ ማስረዳት ይቻላል።

፪· አንድ ወንድና አንዲት ሴት ጋብቻ ሳይፈጽሙ እንደ ባልና ሚስት አብረው ይኖራሉ የሚባለው ምንም እንኳ በሕግ የተጋቡ ባይሆንም የተጋቡ ሰዎችን ሁኔታ ሲያሳዩና ቤተዘመዶቻቸውና ጓደኞቻቸው እንደተጋቡ ሰዎች የሚኖሩ ናቸው ብለው ሲገምቷቸው ነው።

፫· ከዚህ በላይ የተመለከተውን የሕግ ግምት ለማፍረስ በቂ ምስክሮች በማቅረብ የግንኙነቱን አለመኖር ማስረዳት ይቻላል።

፬· የግንኙነቱን መኖር ወይም አለመኖር ለማስረዳት ከምስክሮች በተጨማሪ ሌሎች ማስረጃዎችን ማቅረብ ይቻላል።

አንቀጽ ፩፻፭፩ <u>ጋብቻ ሳይፈጸም የሚደረጉ ሌሎች ግንኙነቶች</u>

፩· ከጋብቻ ሥርዓት ወይም ጋብቻ ሳይፈጸም እንደባልና ሚስት አብሮ ከመኖር ውጭ በአንድ ወንድና በአንዲት ሴት መካከል የሚደረጉ ሌሎች ግንኙነቶች በሕግ ፊት ምንም ውጤት አይኖራቸውም።

፪· በዚህ ሕግ ስለጉዲፈቻ ልጅ ወይም ልጅነትን ስለመቀበል ወይም በፍርድ አባትነህ ስለማለት የተወሰኑት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ከእንደዚህ ያለ ግንኙነት የተወለዱ ልጆች ከእናታቸው በስተቀር ከሌላ ሰው ጋር ማናቸውም ዓይነት ሕጋዊ ግንኙነት አይኖራቸውም።

## ምዕራፍ ዘጠኝ
## በጋብቻ እና ጋብቻ ሳይፈጸም እንደባልና ሚስት አብሮ በመኖር የሚነሱ ክርክሮችን ስለመወሰን

### ክፍል ፩
### ጠቅላላ

አንቀጽ ፩፻፭፪ <u>ተፈፃሚነት ስለሚኖረው ሕግ</u>

በዚህ ሕግ የተመለከቱት የሥነ ሥርዓት ድንጋጌዎች

www.abyssinialaw.com



እንደተጠበቁ ሆነው በዚህ ሕግ ውስጥ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ለሚነሱ ክርክሮች የኢትዮጵያ የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል።

አንቀጽ ፩፻፳፫ የባልና ሚስትን ሀብት ስለማጣራት የተደነገጉት ተፈፃሚ ስለመሆናቸው

፩· ጋብቻው የፈረሰው በፍቺ ባይሆንም፣ የባልና ሚስትን ሀብት ስለማጣራት ከዚህ በላይ በምዕራፍ ስድስት የተደነገጉት እንደየአግባብነታቸው ተፈፃሚ ይሆናሉ።

፪· በተለይም ጋብቻው የፈረሰው በሞት በሆነ ጊዜ በሕይወት ባለው ተጋቢ እና በሟች ወራሾች መካከል የንብረት ክፍፍልን በተመለከተ ክርክር የተነሣ እንደሆነ፣ የባልና የሚስት ሀብት ስለማጣራት በዚህ ሕግ በምዕራፍ ፮ የተደነገጉት እንደየአግባብነታቸው ተፈፃሚ ይሆናሉ።

አንቀጽ ፩፻፳፬ የጋብቻ ሁኔታዎች ባለመሟላታቸው ምክንያት የጋብቻ መፍረስ ውጤት

፩· የጋብቻ ሁኔታዎች ከመጓደሉ የተነሣ ፍ/ቤት ጋብቻ እንዲፈርስ በሚወስንበት ጊዜ መፍረሱ የሚያስከትለውን ውጤት በርትዕ ይወስናሉ።

፪· በተለይም ዳኞች ተጋቢዎቹ ጋብቻውን የፈጸሙት በቅን ልቦና ወይም በመጥፎ ልቦና መሆን አለመሆኑን፣ የሩካቤ ሥጋ መፈጸሙን ወይም አለመፈጸሙን፣ ከጋብቻ የተወለዱትን ልጆችና በቅን ልቦና ከሦስተኛ ወገኖች ጋር የተደረገውን ጥቅም ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ነው።

አንቀጽ ፩፻፳፭ የባልና ሚስት ክርክር ስለሚታይበት ሁኔታ

ፍርድ ቤት የባልና ሚስትን ክርክር በሚያይበት ጊዜ እንደነገሩ ሁኔታ አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው፣ ባልና ሚስቱን በአንድነት ወይም በተናጠል ሲያነጋግር ወይም ጉዳዩን ሲመረምር ምስክር ሲሰማ በዝግ ያስችላል።

አንቀጽ ፩፻፳፮ ስለውሣኔ አሰጣጥ

ፍርድ ቤቱ አስፈላጊና ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው ፍቺ

www.abyssinialaw.com



በሚወስንበት ጊዜ የተጋቢዎቹን ወይም የቤተዘመዶቻቸውን መልካም ስም ለመጠበቅ ዝርዝር ጉዳዮችን ከመተቸት በመቆጠብ ፍቺውን ለመወሰን የሚያስችሉ ምክንያቶች መኖራቸውን ብቻ በውሣኔው ላይ ሊያሰፍር ይችላል።

አንቀጽ ፩፻፳፯ ስለ ይግባኝ

ፍርድ ቤቱ ፍቺ መወሰኑን ብቻ መሠረት በማድረግ ይግባኝ መጠየቅ አይቻልም።

አንቀጽ ፩፻፳፰ የልጆችን አጠባበቅና አያያዝ በሚመለከት ፍርድ ቤቱ ስለሚሰጠው ውሣኔ

፩· ፍርድ ቤቱ ጋብቻው እንዲፈርስ ሲወስን ልጆቹ ከማን ጋር ሊኖሩ እንደሚገባ፣ ስለትምህርታቸው እና ስለጤናቸው አጠባበቅ፣ ስለቀለባቸውና በአጠቃላይም ስለ አኗኗራቸው፣ እንዲሁም ወላጆችና ልጆቻቸው ለመጠያየቅ ስላላቸው መብት መወሰን አለበት።

፪· ፍርድ ቤቱ ከዚህ በላይ በተመለከተው ሁኔታ ውሣኔ በሚሰጥበት ጊዜ የወላጆቹን የገቢ፣ ዕድሜ፣ የጤና እና የአኗኗር ሁኔታ እንዲሁም የልጆችን የዕድሜ፣ ጥቅማቸውና ፍላጎታቸው የሚጠበቅበትን ሁኔታ ማገናዘብ ይኖርበታል።

፫· ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀጽ መሠረት ስለልጆች አያያዝና አጠባበቅ የሚሰጠው ውሣኔ የሁኔታዎች መለወጥን ምክንያት በማድረግ በሚቀርብ ጥያቄ ሊሻሻል ወይም ሊለወጥ ይችላል።

አንቀጽ ፩፻፳፱ ጋብቻ ሳይፈጸም እንደ ባልና ሚስት አብሮ ስለመኖር

በዚህ ክፍል የተመለከቱት ድንጋጌዎች እንደየአግባብነታቸው ጋብቻ ሳይፈጸም እንደባልና ሚስት አብረው በሚኖሩ ሰዎችም ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ።

www.abyssinialaw.com



## ክፍል ፪
## ስለፍርድ ቤት ሥልጣን

**አንቀጽ ፩፻፴ የሚፀና ጋብቻ ስለመኖሩ**

ጋብቻ የተፈጸመ ወይም የሚፀና ስለመሆኑ ክርክር የተነሣ እንደሆነ ጉዳዩን አይቶ ለመወሰን ሥልጣን የሚኖረው ፍርድ ቤት ብቻ ነው።

**አንቀጽ ፩፻፴፩ ጋብቻ ሳይፈጸም እንደ ባልና ሚስት አብሮ ስለመኖር**

በአንድ ወንድና ሴት መካከል ጋብቻ ሳይፈጸም እንደ ባልና ሚስት አብሮ የመኖር ግንኙነት ስለመኖሩ ክርክር የተነሣ እንደሆነ ጉዳዩን አይቶ ለመወሰን ሥልጣን የሚኖረው ፍርድ ቤት ብቻ ነው።

**አንቀጽ ፩፻፴፪ ስለፍቺና ስለፍቺ ውጤቶች**

ፍቺን የመወሰን ወይም በዚህ ሕግ አንቀጽ ፺፫ በተደነገገው መሠረት የፍቺ ውጤቶችን በተመለከተ ውሣኔ የመስጠት ወይም የማጽደቅ ሥልጣን የፍርድ ቤት ብቻ ነው።

**አንቀጽ ፩፻፴፫ በጋብቻ ውስጥ ስለሚፈጠሩ አለመግባባቶች**

፩. በዚህ ሕግ በአንቀጽ ፩፻፴፪ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በጋብቻ ውስጥ የሚፈጠሩ አለመግባባቶች ባልና ሚስቱ በሚመርጧቸው ሽማግሌዎች አማካይነት ይወሰናሉ።

፪. ሽማግሌዎች በሚሰጡት ውሣኔ ቅር የተሰኘ ወገን ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት አቤቱታ ለማቅረብ ይችላል።

፫. ፍርድ ቤቱ የቀረበለትን ቅሬታ መርምሮ በሽማግሌዎች የተሰጠውን ውሣኔ ሊያፀና፣ ሊያሻሽል ወይም ሊሽር ይችላል፣ የሚሰጠውም ውሣኔ የመጨረሻ ይሆናል።

www.abyssinialaw.com


## ክፍል ፫
## ስለ እርቅ

**አንቀጽ ፩፻፴፩ አስታራቂ ሽማግሌዎችን ስለመምረጥ**

፩· በዚህ ሕግ አንቀጽ ፺፩ ንዑስ አንቀጽ /፪/ መሠረት ባልና ሚስት ጉዳያቸውን በእርቅ ለመጨረስ ከወሰኑ፣ አመቺ ሆኖ በሚያገኙት መንገድ አንድ ወይም ቁጥራቸው ከአንድ በላይ የሆኑ ሽማግሌዎችን በመምረጥ ሽማግሌ እንዲመርጡ ከተነገራቸው ቀን አንስቶ በ፲፭ ቀናት ውስጥ የሽማግሌዎቹን ስም ዝርዝር ለፍርድ ቤቱ ማሳወቅ ይኖርባቸዋል።

፪· ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ መሠረት የሽማግሌዎች ስም ዝርዝር ሲቀርብለት ወይም ሽማግሌዎቹ እንደቀረቡ ወዲያውኑ መዝግቦ እርቅ የሚከናወንበትን የመፍትሔ አቅጣጫ የሚጠቁም ምክርና መመሪያ በመስጠት ወይም እንዲደርሳቸው በማድረግ የእርቁ ወይም የእርቁ ሙከራ ውጤት በሦስት ወራት ጊዜ ውስጥ እንዲቀርብለት ያዛል።

፫· የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፪/ ድንጋጌ ቢኖርም ፍርድ ቤቱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የእርቁ ሂደት የደረሰበትን ደረጃ በየጊዜው ለመመርመርና ወቅታዊ ሪፖርት እንዲቀርብለት ማዘዝ ይችላል።

**አንቀጽ ፩፻፴፪ ስለተጨማሪ ጊዜ**

ከእርቅ ሙከራው ሂደት አኳያ ባልና ሚስት ያለመግባባታቸውን በእርቅ ሊጨርሱ ይችላሉ የሚል ግምት ያለው እንደሆነ ፍርድ ቤቱ በዚህ ሕግ በአንቀጽ ፩፻፴፩ በተመለከተው ጊዜ ሳይገድብ ከአንድ ወር ያልበለጠ ተጨማሪ ጊዜ በመስጠት የእርቅ ሙከራው እንዲቀጥል ሊያዝ ይችላል።

**አንቀጽ ፩፻፴፫ የአስታራቂ ሽማግሌዎች ኃላፊነት**

፩· አስታራቂ ሽማግሌዎች ባልና ሚስቱ የመፋታት ሃሳባቸውን እንዲተውና ጉዳያቸውን በመግባባት እንዲጨርሱ

www.abyssinialaw.com



ለማድረግ ያላሰለሰ ጥረት ማድረግ አለባቸው።

፪· አስታራቂ ሽማግሌዎቹ ጉዳዩ ከፍቺ በመለስ ሊፈታ እንደማይችል የተረዱ እንደሆነ ተጨማሪ ጊዜ ሳያስፈልጋቸው ስለደረሱበት ውጤት ለፍርድ ቤቱ ሪፖርት ማቅረብ አለባቸው።

፫· አስታራቂ ሽማግሌዎች ጉዳዩን ከፍቺ በመለስ በማግባባት ለመፍታት ከመጣር አልፈው ባልና ሚስቱን የሚመለከት ማናቸውንም ትዕዛዝ ሆነ ውሣኔ የመስጠት ሥልጣን አይኖራቸውም።

አንቀጽ ፩፻፴፮ የሪፖርት አለመቅረብ

፩· በዚህ ሕግ በአንቀጽ ፩፻፴፬ እና ፩፻፴፭ መሠረት አስታራቂዎቹ ሪፖርት ሳያቀርቡ የቀሩ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ መዝገቡን ይዘጋዋል።

፪· መዝገቡ በተዘጋ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ባልና ሚስቱ ወይም ከሁለቱ አንዳቸው ጉዳያቸውን በእርቅ አለመጨረሳቸውንና ሪፖርቱ በወቅቱ ያልቀረበበትን ምክንያት በመግለጽ ጉዳያቸው እንዲንቀሳቀስላቸው የጠየቁ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ጥያቄያቸው ተገቢ ሆኖ ካገኘው መዝገቡን በመክፈት በሕጉ መሠረት የራሱን ውሣኔ ይሰጣል።

፫· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ መሠረት የሚሰጠው መዝገቡን የመዝጋት ውሣኔ ባልና ሚስቱ ወይም ከሁለቱ አንዳቸው አዲስ አቤቱታ በማቅረብ ጉዳያቸው እንዲታይላቸው ከመጠየቅ የሚያግዳቸው አይሆንም።

## ምዕራፍ አሥር
## ስለመወለድ
## ክፍል ፩
## አባትነትና እናትነት ስለማወቅ
### ንዑስ ክፍል ፩
### አጠቃላይ ድንጋጌዎች

አንቀጽ ፩፻፴፯ የሕጉ ድንጋጌዎች አስገዳጅ ስለመሆናቸው

ሕጉ በግልጽ የሚፈቅድ ካልሆነ በስተቀር አባትነትና እናትነት

www.abyssinialaw.com



ለማወቅ የተደነገጉት የዚህ ሕግ ድንጋጌዎች በስምምነት ሊለወጡ አይችሉም፡፡

አንቀጽ ፩፻፴፱ ስለእናትነት

እናት የተባለችው ሴት ልጁን የወለደችው በመሆንዋ ብቻ እናትነቷ ይታወቃል፡፡

አንቀጽ ፩፻፵ ስለአባትነት

፩· ልጁ በሚፀነስበት ወይም በሚወለድበት ጊዜ በእናት የዋና በአንድ ወንድ መካከል በሕግ የታወቀ ግንኙነት ለመኖሩ በመረጋገጡ ምክንያት አባትነት ይታወቃል፡፡

፪· አባትየው ልጁን ልጄ ነው ሲል በዚህ ሕግ ድንጋጌዎች መሠረት በመቀበሉ ምክንያትም አባትነት ሊታወቅ ይችላል፡፡

፫· በፍርድ ቤት በሚሰጥ ውሣኔም አባትነት እንዲታወቅ ሊደረግ ይችላል፡፡

## ንዑስ ክፍል ፪
## አባትነት በሕግ ግምት የሚታወቅ ስለመሆኑ

አንቀጽ ፩፻፵፩ ባል አባት ነው ተብሎ የሚገመት ስለመሆኑ

በጋብቻ ውስጥ የተፀነሰ ወይም የተወለደ ልጅ አባቱ ነው የሚባለው ባልየው ነው፡፡

አንቀጽ ፩፻፵፪ የግምቱ አጠቃላይነት

፩· ከልጁ ጋር ያለው የእናት ግንኙነት በየትኛውም ዘዴ የተረጋገጠ ቢሆንም ከዚህ በላይ በአንቀጽ ፩፻፵፩ የተመለ ከተው ድንጋጌ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

፪· የልጁ የልደት ምስክር ወረቀት ባልየው አባት ያለመ ሆኑን ወይም የልጁ አባት ሌላ ሰው መሆኑን የሚያመ ለክት ቢሆንም እንኳ ይኸው ድንጋጌ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

፫· ከዚህ በላይ የተመለከተው ሁኔታ ባጋጠመ ጊዜ የልደት ምስክር ወረቀቱ እንዲታረም ይደረጋል፡፡

www.abyssinialaw.com



**አንቀጽ ፩፻፳፰ እርግዝናው ስለሚቆይበት ጊዜ**

፩· ጋብቻው ከተፈጸመ ከ፩፻፹ ቀናት በኋላ ወይም ጋብቻው በፈረሰ በ፫፻ ቀናት ውስጥ የተወለደ እንደሆነ ልጁ በጋብቻው ውስጥ እንደተፀነሰ ይቆጠራል።

፪· ይህን የሕግ ግምት በተቃራኒ ማስረጃ ማስተባበል አይቻልም።

**አንቀጽ ፩፻፳፱ የባልየው መጥፋት/አለመኖር/**

በዚህ ሕግ ስለ አባትነት የተደነገጉት የሕግ ግምቶች በሕግ አባት ነው የሚባለው ሰው መጥፋቱ በተነገረበት ፍርድ ላይ ስለ መኖሩ የተሰማበት የመጨረሻ ቀን ነው ከተባለበት ከ፫፻ ቀናት በኋላ ለተወለደው ልጅ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

**አንቀጽ ፩፻፴ ጋብቻ ሳይፈጸም እንደባልና ሚስት አብሮ መኖር**

፩· ጋብቻ ሳይፈጸም እንደባልና ሚስት አብረው በሚኖሩበት ጊዜ የተፀነሰ ወይም የተወለደ ልጅ አባት በዚህ ግንኙነት ከእናትየው ጋር አብሮ የሚኖረው ሰው ነው።

፪· በዚህ ሕግ አንቀጽ ፩፻፳፮ እና ፩፻፳፰ ስለግምቱ አጠቃላይነት እና እርግዝናው ስለሚቆይበት ጊዜ የተመለከቱት ድንጋጌዎች በዚህ አንቀጽ ለተመለከተው የሕግ ግምትም ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል።

## ንዑስ ክፍል ፫
## ልጅነትን ስለመቀበል

**አንቀጽ ፩፻፴፩ /፩/ መሠረቱ**

ከዚህ በላይ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት የልጁ አባት ማን እንደሆነ ሊታወቅ ያልቻለ ሲሆን አባትየው ልጄ ነው ሲል በመቀበሉ አባትነት ሊታወቅ ይችላል።

**አንቀጽ ፩፻፴፪ /፪/ ትርጓሜ**

አንድ ሰው አንድን የተፀነሰ ወይም የተወለደ ልጅ የእርሱ ልጅ መሆኑን አምኖ በመቀበል ቃሉን የሰጠ

www.abyssinialaw.com


እንደሆነ የልጁ አባት መሆኑን ተቀበለ ይባላል።

አንቀጽ ፩፻፴፫ /፫/ ሥርዓት /ፎርም/

አንድ ሰው የክብር መዝገብ ሹም ፊት በመቅረብ አባት መሆኑን በመግለጽ በሚሰጠው ቃል ወይም በጽሑፍ በሚያደርገው ኑዛዜ ወይም በሌላ በማና ቸውም ሥልጣን በተሰጠው ባለሥልጣን በተረጋገጠ ሠነድ አማካይነት አባት መሆኑን በመግለጽ ልጅነትን ለመቀበል ይችላል።

አንቀጽ ፩፻፴፱ ስለወኪልነት

፩· አካለ መጠን ያልደረሰ ቢሆንም እንኳ ልጄ ነው ሲል ቃል ለመስጠት የሚችለው አባት ብቻ ነው።

፪· ቃሉን ሌላ ሰው እንዲሰጥለት ማድረግ የሚችለው በፍርድ ቤት የፀደቀ ልዩ ውክልና ሥልጣን በመስጠት ብቻ ይሆናል።

፫· በፍርድ የተከለከለ ሰው ቃሉን በራሱ ወይም ፍርድ ቤት ሲፈቅድ በእርሱ ስም በሕጋዊ ወኪሉ አማካይነት ሊሰጥ ይችላል።

አንቀጽ ፩፻፵ የአባትየው መሞት

የልጅ አባት የሞተ ወይም ፈቃዱን ለመስጠት የማይችል በሆነ ጊዜ ከአባትየው ወላጆች አንድ በእርሱ ስም ልጁን ሊቀበል ይችላል።

አንቀጽ ፩፻፵፩ እናት የተቀባዩን አባትነት ስለማመንዋ

፩· የልጁ እናት የተቀባዩን አባትነት እውነትነት ያለው መሆኑን ካላመነች በስተቀር አባት ልጄ ነው ሲል የሚሰጠው ቃል በሕግ ፊት ውጤት አይኖረውም።

፪· የልጁ እናት የሞተች ወይም ፈቃድዋን ለመግለጽ የማትችል ሆና የተገኘች እንደሆነ፣ የእምነት ቃሉ ከልጁ እናት ወላጆች በአንደኛው ሊሰጥ ይችላል።

፫·የልጁ እናት ወላጆች በሌሉ ጊዜ ወደላይ በሚቆጠር ሌላ ወላጅ ወይም በፍርድ በተከለከለው ሰው አሳዳሪ ሊሰጥ ይችላል።

www.abyssinialaw.com



**አንቀጽ ፩፻፺፪ ስለልጁ ለአካለ መጠን መድረስ**

ልጅነትን የመቀበሉ ተግባር የተከናወነው ልጁ አካለ መጠን ከደረሰ በኋላ የሆን እንደሆነ አባት ልጁን መቀበሉ ውጤት የሚያገኘው ልጁ አባትነቱን የተቀበለ እንደሆነ ነው።

**አንቀጽ ፩፻፺፫ እምና የመቀበሉ ሁኔታ**

በዚህ ሕግ በአንቀጽ ፩፻፺፩ እና ፩፻፺፪ የተመለከቱት ሰዎች የመቀበሉ ድርጊት መከናወኑን ካወቁበት ቀን ጀምሮ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ክርክር ያላነሡ እንደሆነ እምነው እንደተቀበሉ ይቆጠራል።

**አንቀጽ ፩፻፺፬ የልጁ መሞት**

ልጅየው ወደታች የሚቆጠሩ ተወላጆችን ተክቶ ካልሞተ በስተቀር ልጅነቱን አውቆ መቀበል አይችልም።

**አንቀጽ ፩፻፺፭ ቃልን ስለመሻር**

፩· ልጂ ነው ሲል አባት የሰጠውን ቃል መሻር አይችልም።
፪· አሳዳሪው አስቀድሞ ስምምነቱን ካልሰጠ በስተቀር ልጅነትን የተቀበለ አካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ አካለ መጠን እስካልደረሰበት ጊዜ ድረስና አካለ መጠን ከደረሰ በኋላ እስከ አንድ ዓመት ጊዜ ድረስ ልጂ ነው ሲል የሰጠውን ቃል ሊሽር ይችላል።
፫· ልጂ ነው ሲል የተቀበለበትን ቃሉን ለመሻር ብቸኛ መብት ያለው አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ ብቻ ነው። የልጁ ሕጋዊ ወኪሎችም ሆኑ ወራሾች በዚህ መብት መጠቀም አይችሉም።

**አንቀጽ ፩፻፺፮ ስለማፍረስ**

፩· ልጅነት ለመቀበል የተነገረው ቃል በኃይል የተሰጠ መሆኑን በማስረዳት ሊፈርስ ይችላል።
፪· ልጂ ነው ብሉ ከተቀበለው ሰው ሊሆንስ የማይቻል ለመሆኑ የማያሻማ አኳኋን ካልተረጋገጠ በስተቀር ልጅነት የመቀበሉ ድርጊት በስህተት ወይም በማታለል የተደረገ ነው በማለት ሊፈርስ አይችልም።

www.abyssinialaw.com


አንቀጽ ፩፻፶፯ <u>አንድን ልጅ ብዙ አባቶች ሊቀበሉት ስላለመቻላቸው</u>

ቀደም ሲል የተሰጠ ልጅነትን የመቀበል ቃል እንዲፈርስ ካልተደረገ በስተቀር ሌላ ሰው ልጄ ነው ሲል የሚሰጠው ቃል ተቀባይነት አይኖረውም።

## <u>ንዑስ ክፍል ፬</u>
## <u>በፍርድ ቤት ውሣኔ አባትነት እንዲታወቅ ስለማድረግ</u>

አንቀጽ ፩፻፶፰/፩/ <u>በፍርድ ስለሚነገር አባትነት</u>

ከዚህ በላይ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት የልጁ አባት ያልታወቀ ወይም የተካደ እንደሆነና ከዚህ በታች የተመለከቱት ሁኔታዎች ሲሟሉ አባትነት በፍርድ ቤት ውሣኔ ሊታወቅ ይችላል።

ሀ) ልጁ በተፀነሰበት ጊዜ በእናቲቱ ላይ የመድፈር ወይም የመጠለፍ ተግባር የተፈጸመባት ሲሆን፣

ለ) ሆን ተብሎ በተደረገ የተንኮል ድርጊት ሥልጣንን ያለ አግባብ በመጠቀም አገባሻለሁ ሲል የተስፋ ቃል በመስጠት ወይም በሌላ ተመሳሳይ መንገድ ልጁ በተፀነ ሰበት ጊዜ በእናቲቱ ላይ የማሳት ተግባር የተፈፀመባት ሲሆን፣

ሐ) አባት ነው በተባለው ሰው የተጻፈና በማያሻማ ሁኔታ አባትነቱን የሚያረጋግጡ ደብዳቤዎች ወይም ሌሎች ጽሑፎች ሲኖሩ፣

መ) በሕግ የታወቁ ግንኙነት ሳይኖራቸው የልጁ እናትና አባት የተባለው ሰው በሕግ በተመለከተው የእርግዝና ጊዜ ቀጣይነት ባለው ሁኔታ በግብረ ሥጋ ግንኙነት አብረው የኖሩ እንደሆነ፣

ሠ) አባት ነው የተባለው ሰው ልጁን በመንከባከብ በማስ ተማር ወይም በማሳደጉ ላይ እንደ አባት በመሆን የተሳተፈ እንደሆነ።

አንቀጽ ፩፻፶፱/፪/ <u>አባትነትን በፍርድ ለማረጋገጥ ስለሚቀርብ ክስ</u>

ከዚህ በላይ በተመለከተው አካኋን አባትነት በፍርድ እንዲነገር የሚቀርብ ክስ ከዚህ በታች የተመለከቱት

www.abyssinialaw.com



ሁኔታዎች ባሉ ጊዜ ተቀባይነት አይኖረውም።

ሀ) ሌላኛው ሰው የልጁ አባት ላለመሆኑ በደም ምርመራ ወይም በሌላ አስተማማኝ የሕክምና ዘዴ ካልተረጋገጠ በስተቀር በሕግ በተወሰነው የእርግዝና ጊዜ ውስጥ እናቲቱ ከሌላ ሰው ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት መፈጸምዋ የተረጋገጠ እንደሆነ

ለ) አባት ነው የተባለው ሰው በሕግ በተወሰነው የእርግዝና ጊዜ ውስጥ በመጥፋቱ ወይም በአደጋ ምክንያት አባት ሊሆን የማይችልበት ሁኔታ ሲረጋገጥ፣

ሐ). አባት ነው የተባለው ሰው በደም ምርመራ ወይም በሌላ አስተማማኝ የሕክምና ዘዴ የልጁ አባት ሊሆን የማይችል መሆኑን ሲያረጋግጥ።

<u>አንቀጽ ፩፻፷ ሌላ ሁኔታ ስለመኖሩ</u>

በዚህ ሕግ አንቀጽ ፩፻፶፷ ከተመለከቱት ሁኔታዎች ውጪ አባትነት በፍርድ ቤት ውሣኔ ሊታወቅ አይችልም።

## <u>ክፍል ፪</u>
## <u>አባትነት በመወሰን ላይ ስለሚኖረው የሕግ ግጭት</u>

<u>አንቀጽ ፩፻፷፩ አባትነት ስለመወሰን /፩/ መሠረቱ</u>

አባትነትን ስለመወሰን ከዚህ በላይ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ተፈፃሚ በማድረግ አንድ ልጅ ከአንድ በላይ አባቶች አሉት ከተባለ የልጁ አባትነት በሕግ በሚሰጣቸው ሰዎች መካከል በሚደረግ ስምምነት ሊወሰን ይችላል።

<u>አንቀጽ ፩፻፷፪ /፪/ ሥርዓት (ፎርም)</u>

፩· የአባትነትን ውሣኔ የሚሰጠውን ስምምነት ሦስት ምስክሮች ሊያረጋግጡትና ፍርድ ቤት ሊያፀድቀው ይገባል።

፪ ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ካላጋጠመ በስተቀር የልጅን እናት ቃል መስማት ይገባል።

www.abyssinialaw.com



**አንቀጽ ፩፻፷፫ የሕግ ግምት**

ስለአባትነት በሚደረገው ክርክር ስምምነት ያልተገኘ እንደሆነና አስረጂ ሆኖ ከተገኘ ከዚህ ቀጥሎው ያሉትን ሁለት የሕግ ግምቶች በመከተል ይፈጸማል፡፡

ሀ) ጋብቻ ሳይፈጸም እንደ ባል ከሚኖር ሰው ይልቅ ሕጋዊ ባል ይመረጣል፡፡

ለ) ልጁ በተፀነሰበት ጊዜ ከነበረው ባል ወይም ከሴትየዋ ጋር አብሮ ይኖር ከነበረው ሰው ይልቅ እናቲቱ ልጁን ስትወልድ የነበራት ባል ወይም አብሮ የሚኖር ሰው የልጁ አባት ነው ማለት ይገባል፡፡

**አንቀጽ ፩፻፷፬ /፩/ አባትነትን በስምምነት ስለማስተባበል**

፩· ልጁ የተወለደው ጋብቻው ከተፈጸመ ወይም ጋብቻ ሳይፈጸም እንደባልና ሚስት አብሮ መኖር ከተጀመረ አንስቶ በ፻፹ ቀናት ውስጥ የሆነ እንደሆነ ባልየው ወይም ከሴትየዋ ጋር እንደባል አብሮ የሚኖረው ሰው የልጁ አባት እኔ ነኝ ለሚል ሌላ ሰው በስምምነት አባትነቱን ሊያስተባልፈልት ይችላል፡፡

፪ እንዲሁም ልጁ ከጋብቻው መፍረስ ውይም እንደባልና ሚስት አብሮ መኖሩ ከተቋረጠበት ቀን በኋላ ፫፻ ቀናች አሳልፎ ተወልዶ እንደሆነ ባልየው ወይም እንደባል አብሮ የኖረው ሰው ከዚህ በላይ የተነገረው መብት ይኖራል፡፡

**አንቀጽ ፩፻፷፭ /፪/ ሥርዓት (ፎርም)**

፩· በስምምነት የሚደረግ አባትነትን የማስተባለፍ ድርጊት ሦስት ምስክሮች ሊያረጋግጡትና ፍርድ ቤት ሊያፀድቀው ይገባል፡፡

፪· ከአትም በላይ የሆነ ችግር ካላጋጠመ በስተቀር የእናቲቱ ቃል መሰማት አለበት፡፡

**አንቀጽ ፩፻፷፮ ስለወኪልነት**

፩· በዚህ ክፍል የተመለከቱት ስምምነቶች አካለ መጠን የደረሱና በፍርድ ያልተከለከሉ ባለጉዳዮች ራሳቸው

www.abyssinialaw.com



መጨረስ አለባቸው።

፪· ስምምነቱ ሌላ ሰው እንዲያከናውኑለት ማድረግ የሚቻለው በፍርድ ቤት የፀደቀ ልዩ የውክልና ሥልጣን በመስጠት ብቻ ይሆናል።

አንቀጽ ፩፻፷፯ ቃልን ስለመሻር

አባትነትን በስምምነት የመወሰን ወይም የማስተላለፍ ድርጊት ሊሻር አይቻልም ።

አንቀጽ ፩፻፷፰ ስለማፍረስ

፩· ልጅነትን ለመቀበል የተደረገ ስምምነት በኃይል ድርጊት የተሰጠ መሆኑን በማስረዳት ሊፈርስ ይቻላል።

፪· ልጅ ነው ብሎ ከተቀበለው ሰው ሊፀነስ የማይቻል ለመሆኑ በማያሻማ አኳኋን ካልተረጋገጠ በስተቀር ልጅነት የመቀበሉ ስምምነት በስህተት ወይም በማታለል የተደረገ ነው በማለት ሊፈርስ አይችልም።

## ክፍል ፫
## ስለ ልጅነት ማስረጃ

አንቀጽ ፩፻፷፱ የልደት የምስክር ወረቀት

በአባትነት ወይም በእናትነት በኩል የአንድ ሰው ልጅነት የእገሌ ልጅ ነው የሚል የልደት ምስክር ወረቀት በማቅረብ ይረጋገጣል።

አንቀጽ ፩፻፸ የልደት የምስክር ወረቀት በሌለ ጊዜ ስለሚቀርብ ማስረጃ

የልደት ምስክር ወረቀት የሌለ እንደሆነ የልጅነት ሁኔታ በመኖሩ ልጅነት ይረጋገጣል።

አንቀጽ ፩፻፸፩ የልጅነት ሁኔታ መኖር /፩/ ትርጓሜ

አንድ ሰው የልጅነት ሁኔታ አለው የሚባለው በማህበረሰቡ ዘንድ የእርሱ ወይም የእርሷ ልጅ ነው እየተባለ የሚገመት ሲሆን ነው።

አንቀጽ ፩፻፸፪ /፪/ ልጅነትን በልጅነት ሁኔታ ስለማስረዳት

፩· ከዚህ በላይ በተመለከተው አንቀጽ መሠረት የልጅነት

www.abyssinialaw.com



ሁኔታ መኖሩን ለማስረዳት የተቻለ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ልጁ ነው ሲል የሕግ ግምት ይወስዳል።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ አንድ የተመለከተው ግምት ልጁ የተባለ ሰው ልጅ ሊሆን እንደማይችል በማስረዳት ማፍረስ ይቻላል።

አንቀጽ ፩፻፷፫ ተወላጅነትን ለማስረዳት ስለሚቀርብ ክስ

፩· የልጅነት ሁኔታ የሌለ እንደሆነ ተወላጅነትን በምስክሮች ወይም በማናቸውም ዓይነት ማስረጃ በማቅረብ ማስረዳት ይቻላል።

፪· ተወላጅነትን የማረጋገጥ ክስ ፍርድ ቤቱ ካልፈቀደው በስተቀር ሊቀርብ አይችልም።

፫· ተወላጅነትን ለማረጋገጥ ለሚቀርብ ክስ ፈቃድ የሚሰጠው ፍርድ ቤቱ ክሱን እንዲቀበል የሚያደርጉ ተጨባጭነት ካላቸው ተግባራት የሚመነጩ ግምቶች ወይም ምልክቶች ሲኖሩ ብቻ ነው።

አንቀጽ ፩፻፷፬ ስለከሣሽ

፩· ተወላጅነትን ለማረጋገጥ ክስ ለማቅረብ የሚችሉት ልጅ ወይም አሳዳሪው ወይም ወራሾቹ ናቸው።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ አንድ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ የልጅ አባት ወይም እናት ነን የሚሉት ሰዎች ክስ ለማቅረብ ይችላሉ።

አንቀጽ ፩፻፷፭ ክስን ስላለመቀበል

ተወላጅነቱን ለማረጋገጥ የሚፈልገው ሰው ስለመወለዱ ከተሰጠው የልደት ምስክር ወረቀት ጋር የሚስማማ የልጅነት ሁኔታ ያለው እንደሆነ ከሌላ ሰው ተወላጅነቱን ለማረጋገጥ ክስ ለማቅረብ አይፈቀድለትም።

አንቀጽ ፩፻፷፮ ስለተከሳሽ

፩· ተወላጅነትን ለማረጋገጥ ክሱን ያቀረበችው እናት ነኝ የምትል ሴት በሆነች ጊዜ ክስ የሚቀርበው በልጁ ላይ ነው።

፪· ሆኖም ክሱ የቀረበው በሌላ ሰው ሲሆን ክሱ የሚቀርበው

www.abyssinialaw.com



እናት ነች በተበለችው ወይም በወራሾቿ ላይ ነው።

አንቀጽ ፩፻፷፺ ክስ ስለሚቀርብበት ጊዜ

፩· ልጁ በሕይወት እስካለ ድረስ ተወላጅነትን ለማረጋገጥ ክስ ለማቅረብ ይችላል።

፪· የልጁ ወላጆች ወይም አሳዳሪዎች ልጁ አካለ መጠን ባልደረሰበት ጊዜ ካልሆነ በስተቀር ክስ ለማቅረብ አይችሉም።

፫· ልጁ ፳ ዓመት ሳይሞላው የሞተ እንደሆነ እርሱ ከሞተ በኋላ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ካልሆነ በስተቀር ወራሾቹ ክስ ለማቅረብ አይችሉም።

## ክፍል ፬
## በተወላጅነት ላይ ስለሚነሳ ክርክርና ስለመካድ
### ንዑስ ክፍል ፩
### በተወላጅነት ላይ ስለሚነሣ ክርክር

አንቀጽ ፩፻፷፰ መሠረቱ

በእናት በኩል ያለው ተወላጅነት በማንኛውም ባለጉዳይ በማንኛውም ጊዜ ሁሉ ክርክር ሊደረግበት ይችላል።

አንቀጽ ፩፻፷፱ ክስን ስለመቀበል

፩· በተወላጅነት ላይ ስለሚደረገው ክርክር የሚቀርበው ክስ ፍርድ ቤት ካልፈቀደ በስተቀር ሊቀርብ አይችልም።

፪· በተወላጅነት ላይ ክርክር ለማድረግ ለሚቀርበው ክስ ፈቃድ የሚሰጠው ፍርድ ቤቱ ክሱን እንዲቀበል የሚያደርጉት ተጨባጭነት ካላቸው ተግባራት የሚመነጩ ግምቶች ወይም ምልክቶች ሲኖሩ ብቻ ነው።

አንቀጽ ፩፻፸ ክስን ስላለመቀበል

ልጁ ተወላጅነቱን የሚያረጋግጥ የልደት የምስክር ወረቀትና ከዚሁ ጋር የሚስማማ የልጅነት ሁኔታ ያለው እንደሆነ በተወላጅነት ላይ ለማከራከር ፈቃድ አይሰጥም።

አንቀጽ ፩፻፸፩ ስለ ተከሣሽ

፩· በተወላጅነት ምክንያት የሚቀርበው ክስ በተወላጅነቱ

www.abyssinialaw.com



ላይ ክርክር በተነሣበት ሰው ላይ ወይም በወራሾቹ ላይ ይመሠረታል።

፪· የልጁን እናት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም የልጁን አባት ክርክሩ ውስጥ እንዲገቡ ማድረግ አስፈላጊ ነው።

## ንዑስ ክፍል ፪
## ስለመካድ

**አንቀጽ ፩፻፷፪ መሠረቱ**

በአባት በኩል ያለን መወለድ መቃወም የሚችለው የመካድ ክስ በማቅረብ ብቻ ነው።

**አንቀጽ ፩፻፷፫ ከልጁ እናት ጋር የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት ስላለመኖር /፩/ መሠረቱ**

የልጁ አባት ነህ ተብሎ በሕግ አባትነት የሚሰጠው ሰው ልጁ ከመወለዱ በፊት በሦስት መቶኛውና በአንድ መቶ ስማንያኛው ቀናት መካከል ባለው ጊዜ ውስጥ ከልጁ እናት ጋር የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት ላለመፈጸሙ በማያጠራጥር ሁኔታ ያስረዳ እንደሆነ የተባለውን ልጅ ልጄ አይደለም ለማለት ይችላል።

**አንቀጽ ፩፻፷፬ /፪/ የሕግ ግምት**

፩· ከሁለቱ አንዱ ባቀረበው የመፋታት ጥያቄ መሠረት ወይም በሁለቱ መካከል በተደረገው የመለያየት ስምምነት ምክንያት ባልና ሚስቱ በእውነት ተለያይተው በነበሩበት ጊዜ በመካከላቸው የሩካቤ ሥጋ ግንኙነት እንዳልተደረገ ይገመታል።

፪· ለዚህ ተቃራኒ ሆኖ የሚቀርበው ማስረጃ በማንኛዎቹም ምክንያቶች ቢሆን ይሰማል።

**አንቀጽ ፩፻፷፭ አባት ለመሆን ስለአለመቻሉ /፩/ መሠረቱ**

በሕግ የልጅ አባት ነህ የተባለው ሰው የዚሁ ልጅ አባት ሊሆን አለመቻሉን በማያጠራጥር አኳኋን በማስረዳት ለመካድ ይችላል።

**አንቀጽ ፩፻፷፮ /፪/ ክስን ለመቀበል ስለ መቻል**

፩· ከዚህ በላይ በተመለከተው አንቀጽ መሠረት የሚቀርበው

www.abyssinialaw.com



የመካድ ክስ ፍርድ ቤት ካልፈቀደ በቀር ሊቀርብ አይችልም፡፡

፪· ፈቃዱም የሚሰጠው ፍርድ ቤት ክሱን እንዲቀበል የሚያደርገው በቂና አስተማማኝ ከሆነ መረጃ የሚመነጭ የህሊና ግምት ወይም ከባድ ምልክት ሲኖር ብቻ ነው፡፡

አንቀጽ ፩፻፷፯ /፫/ <u>ስለህሊና ግምቶችና ከባድ ምልክቶች</u>

፩· የህሊና ግምቶችና ከባድ ምልክቶች የሚባሉት ልጅህ ነው ከተባለው ሰው አባትነት ጋር የማይስማሙ ለመሆ ናቸው በግልጽ ዕውቀት ተለይተው የሚታዩ ተጨባጭ መረጃዎች ሊሆኑ ይችላሉ ፡፡

፪· እንዲሁም እነዚህ ነገሮች ሴቲቱ በሰውየው አባትነት ላይ ጥርጣሬ በሚያሳድር አኳኋን የልጁን መወለድ እርግዝ ናዋን ከሰውየው የደበቀችበት ድርጊት ሊመነጩ ይችላሉ፡፡

አንቀጽ ፩፻፷፰ /፬/ <u>ስለሴሰኝነት በባል ላይ የሚደረግ ዝሙት ወይም ስለ እናቲቱ ግመን</u>

እናቲቱ በባልዋ ላይ ያደረገችው የሴሰኝነት /የዝሙት/ ሥራ ወይም ልጁ የሌላ ሰው ስለመሆኑ ፤ የምትሰጠው የእምነት ቃል ብቻ እንደ ከባድ ምክንያት ሊቆጠሩ አይችሉም ፡፡

አንቀጽ ፩፻፷፱ <u>ስለከሳሽ</u>

፩· የእኔ ልጅ አይደለም ብሎ የመካድ ክስ ለማቅረብ የሚችለው የልጅ አባት ነህ ተብሎ በሕግ ግምት የሚሰጠው ሰው ብቻ ነው ፡፡

፪· በዚህ ጉዳይ ላይ በተለይ እናቲቱ አባት ነኝ ባዩ ፤ ዐቃቤ ሕግ ወይም ልጁ ራሱ ክስ ሊያቀርቡ አይችሉም ፡፡

አንቀጽ ፩፻፸ <u>በፍርድ የተከለከለው ሰው</u>

፩· በፍርድ የተከለከለው ሰው ፍርድ ቤትን በማስፈቀድ የመካድ ክስ ሊያቀርብ ይችላል ፡፡

፪· እንዲሁም በፍርድ የተከለከለው ሰው አሳዳሪው ይህንኑ የፍርድ ቤት ፈቃድ ከተቀበለ በኋላ በፍርድ በተከለከለው

www.abyssinialaw.com


ሰው ስም የመካድ ክስ ለማቅረብ ይችላል ።

አንቀጽ ፩፻፺፩ የመካድ ክስ ስለሚቀርብበት ጊዜ /፩/ መሠረቱ

፩· የእኔ ልጅ አይደለም የሚል የመካድ ክስ የልጁን መወለድ ካወቀበት ወይም ማወቅ ከሚገባው ቀን ጀምሮ ባሉት ፩፻፹ ቀናት ውስጥ መቅረብ አለበት ።

፪· እናትነት የተወሰነው ተወላጅነትን ለማረጋገጥ ለቀረበ ክስ ሲሆን የመካድ ክስ የሚቀርበው ተወላጅነትን ለማረጋገጥ የቀረበውን ክስ የሚወስን የመጨረሻ ፍርድ ከተሰጠ ጀምሮ ባሉት ፩፻፹ ቀናት ውስጥ ነው ።

አንቀጽ ፩፻፺፪ /፪/ ልዩ ልዩ ሁኔታ

፩· በሕግ ግምት የልጁ አባት ነህ የሚባለው ሰው የሞተ ወይም የመካድ ክስ ለማቅረብ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ችሎታውን ያጣ እንደሆነ ከተወላጆቹ አንዱ በርሱ ፈንታ ሆኖ የመካድ ክስ ሊያቀርብ ይችላል ።

፪· ተወላጆቹ የሌሉ እንደሆነ አባትና እናቱ እነዚህ የሌሉ እንደሆነ ወደ ላይ የሚቆጠሩ ወላጆቹ አንዱ መብቱን ሊሠራበት ይችላል ።

፫· ወደ ላይ የሚቆጠሩ ወላጆቹ የሌሉ እንደሆነ የተባለውን መብት ማናቸውም ሌላ ወራሽ ወይም ወኪል ሳይጨምር ከወንድሞቹ ወይም እህቶቹ አንዱ ሊሠራበት ይችላል ።

አንቀጽ ፩፻፺፫ ክስን ስላለመቀበል

ባልየው በጽሑፍ በሰጠው ፈቃድ መሠረት ልጁ በሰው ሠራሽ ዘዴ የተፀነሰ ስለመሆኑ የተረጋገጠ እንደሆነ የመካድ ክስ ለማቅረብ የሚቀርብ ጥያቄ ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም ።

አንቀጽ ፩፻፺፬ ስለተከሣሾች

፩· የመካድ ክስ በልጁ ላይ እርሱም ሞቶ እንደሆነ በወራሾቹ ላይ ይቀርባል ።

፪· የልጁ እናት በሚቀርበው ክስ ውስጥ እንድትገባ ማድረግ ያስፈልጋል ።

፫· ልጁ አካለ መጠን ያላደረሰ ከሆነ ፍርድ ቤት በተለይ የመረጠው ተጠባባቂ ሞግዚት ወኪል ይሆነዋል ።

www.abyssinialaw.com



## ምዕራፍ አሥራ አንድ
## ስለ ጉዲፈቻ

**አንቀጽ ፩፻፺፫ ስለጉዲፈቻ ዝምድና /፩/ መሠረቱ**

በአንድ ሰውና በአንድ ልጅ መካከል በሚደረግ ስምምነት ጉዲፈቻ ዝምድና ሊፈጠር ይችላል ።

**አንቀጽ ፩፻፺፯ /፪/ ውጤቱ**

ከዚህ በታች በአንቀጽ ፩፻፺፯ የተመለከቱት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የጉዲፈቻ ልጅ በማናቸውም ረገድ ቢሆን እንደጉዲፈቻ አድራጊው ልጅ ይቆጠራል ።

**አንቀጽ ፩፻፺፯ /፫/ ልዩ ሁኔታ**

፩· የጉዲፈቻ ስምምነት በግልጽ የተቃወሙት ወደላይ በሚቆጠሩ ወላጆች ወይም ወደ ጐን የሚቆጠሩ ዘመዶችን በሚመለከት ውጤት አይኖረውም ።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ የተመለከተው ተቃውሞ ስምምነቱ በፍርድ ቤት መጽደቁን ካወቁ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ በፍርድ ቤት መዝገብ ካልተመዘገበ በቀር አይፀናም ።

**አንቀጽ ፩፻፺፰ የጉዲፈቻ ልጅ ከቀደምት ቤተሰቦቹ ጋር ስለሚኖር ግንኙነት**

፩· የጉዲፈቻ ልጅ ከቀደምት ቤተሰቦቹ ጋር ያለው የዝምድና ግንኙነት እንደተጠበቀ ይቆያል ።

፪· የጉዲፈቻ ልጅየው ሚስት፣/ባል እና ተወላጆችም ከቀደምት ቤተሰቦቹ ጋር የዝምድና ግንኙነት ይኖራቸዋል።

፫· በቀደምት ቤተሰቦቹና በጉዲፈቻ ቤተሰቦቹ መካከል መምረጥ አስፈላጊ ሆኖ በተገኘ ጊዜ ለጉዲፈቻ ቤተሰቦቹ ቅድሚያ ይሰጣል ።

**አንቀጽ ፩፻፺፱ የጉዲፈቻ አድራጊው ዕድሜ**

፩· ዕድሜው ከ፳፭ ዓመት ያላነሰ ማንኛውም ሰው የጉዲፈቻ አድራጊ ሊሆን ይችላል ።

www.abyssinialaw.com



፪· የጉዲፈቻ አድራጊዎች ባልና ሚስት በሆኑ ጊዜ የአንዳቸው ዕድሜ ፳፭ ዓመት የሞላ ከሆነ በቂ ነው።

አንቀጽ ፻፺ የጉዲፈቻው ልጅ ዕድሜ

ዕድሜው ከአሥራ ስምንት ዓመት በታች የሆነና ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ ያልወጣ ማናቸውም ሰው የጉዲፈቻ ልጅ ለመሆን ይችላል ።

አንቀጽ ፻፺፩ ያገባ ሰው ስለሚያደርገው የጉዲፈቻ ስምምነት

፩· የጉዲፈቻ አድራጊው ያገባ በሚሆንበት ጊዜ ፤ ባልና ሚስቱ በጋራ ልጁን የጉዲፈቻ ልጃቸው የሚያደርጉት ካልሆነ በቀር የጉዲፈቻ ስምምነት ለማድረግ አይቻልም።

፪· የጉዲፈቻ ልጅ ፤ የጉዲፈቻ አድራጊው ባል ወይም ሚስት ልጅ በሆነ ጊዜ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ የተመለከተው ድንጋጌ ተፈፃሚነት አይኖረውም ።

፫· እንዲሁም ከባል ወይም ከሚስት አንደኛው ፈቃድ ለመስጠት የማይችል ከሆነ ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ /፩/ የተመለከተው ተፈፃሚነት አይኖረውም ።

አንቀጽ ፻፺፪ የተፀነሰን ልጅ የጉዲፈቻ ልጅ ስለማድረግ

፩· የተፀነሰን ልጅ የጉዲፈቻ ልጅ ማድረግ ይቻላል ።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ የተመለከተው ቢኖርም ልጁ በተወለደ በስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ እናቲቱ ስምምነቱን በገዛ ፈቃድዋ ብቻ ለመሠረዝ ትችላለች ።

አንቀጽ ፻፺፫ ስለ ጉዲፈቻ አድራጊው ልጆች

፩· የጉዲፈቻ አድራጊው ከአብራኩ የተገኙ ልጆች ያሉት መሆኑ የጉዲፈቻ ስምምነት ከማድረግ የሚያግደው አይሆንም ።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ የተመለከተው ድንጋጌ ቢኖርም ፍርድ ቤቱ የጉዲፈቻ ስምምነቱን ከማጽደቁ አስቀድሞ የጉዲፈቻ አድራጊው ከአብራኩ የተገኙ ልጆች ያሉት መሆኑ በጉዲፈቻ ልጅ መልካም አስተዳደግና ጥቅም ላይ ሊኖር የሚችለውን ተጽዕና ከግምት ውስጥ ማስገባት አለበት ።

www.abyssinialaw.com



**አንቀጽ ፻፹፩ አንድ ልጅ ከአንድ በላይ የጉዲፈቻ አድራጊ ሊኖረው የማይችል ስለመሆኑ**

፩· ባልና ሚስት ካልሆኑ በቀር ማንኛውም ልጅ ለብዙ ሰዎች የጉዲፈቻ ልጅ ሊሆን አይችልም ፡፡

፪· ጉዲፈቻ አድራጊው የሞተ እንደሆነ ግን አዲስ የጉዲፈቻ ስምምነት ለማድረግ ይቻላል ፡፡

፫· ልጅየው የባልና ሚስት የጉዲፈቻ ልጅ ከሆነና ከባልና ሚስቱ አንደኛው የሞተ እንደሆነ በሕይወት ካለው ሰው ጋር የሚጋባው አዲስ ተጋቢ የጉዲፈቻ ልጅ ሊያደርገው ይችላል ፡፡

**አንቀጽ ፻፹፪ ስምምነቱን ስለሚያደርጉ ወገኖች**

የጉዲፈቻ ስምምነት በጉዲፈቻ አድራጊውና በልጁ አሳዳሪ መካከል ይደረጋል ፡፡

**አንቀጽ ፻፹፫ የጉዲፈቻው ልጅ ወላጆች ፈቃድ**

፩· የልጁ እናትና አባት በሕይወት ያሉና የታወቁ ከሆነ ልጁ የጉዲፈቻ ልጅ እንዲሆን ፈቃዳቸውን እንዲሰጡ ያስፈልጋል ፡፡

፪· ከወላጆች አንደኛው የሞተ ፣ የጠፋ ፣ የማይታወቅ እንደሆነ ወይም ፈቃዱን ለመስጠት የማይችል ሲሆን ሌላኛው ወላጅ ፈቃዱን ይሰጣል ፡፡

፫· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ የተደነገገው ቢኖርም ከወላጆቹ አንዱ ፈቃዱን ለመስጠት ያልፈለገ እንደሆነና የልጁ ዕድሜ ፲፰ ዓመትና ከዚያ በላይ ከሆነ ፍርድ ቤት የአንድን ወላጅ ፈቃድና የልጁን አስተያየት በመጠየቅ የጉዲፈቻ ስምምነት ሊያጸድቀው ይችላል ፡፡

**አንቀጽ ፻፹፬ ስለ መንግሥት ወይም የግል እጓለማውታን አሳዳጊ ተቋሞች**

፩· የመንግሥት ወይም የግል እጓለማውታን አሳዳጊ ተቋሞች እያሳደጉት ያሉትን ማንኛውንም ልጅ ለጉዲፈቻ አድራጊዎች በስምምነት ለመስጠት ይችላሉ ፡፡

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ /፩/ የተመለከቱት ተቋሞች አንዱ ልጅ በስምምነት ከመስጠታቸው በፊት የሕፃናት

www.abyssinialaw.com



ደህንነት ለመከታተል ሥልጣን ለተሰጠው የመንግሥት አካል ስለ ልጁ ማንነት ፤ በምን ሁኔታ ተቋሙ እንደተረከበውና ስለጉዲፈቻ አድራጊው ግላዊ ፤ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አቋም መግለጫ ማቅረብ አለባቸው ።

አንቀጽ ፪፻፰ ጉዲፈቻ አድራጊው የውጭ ዜጋ ሲሆን

፩· የጉዲፈቻ አድራጊው የውጭ ዜጋ ሲሆን የሕፃናትን ደህንነት ለመከታተል ሥልጣን የተሰጠው አካል ስለጉዲፈቻ አድራጊው ግላዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አቋም አግባብ ያላቸውን መረጃዎች በማጠናቀርና በመመርመር ስምምነቱ ቢደረግ ለልጁ ጠቃሚነት ይኖረዋል ሲል አስተያየቱን ካልሰጠ በቀር የጉዲፈቻውን ስምምነት ፍርድ ቤት ሊያፀድቀው አይችልም።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ የተመለከተው ቢኖርም ፍርድ ቤቱ ስምምነቱ ለልጁ ጠቃሚነት አይኖረውም ሲል የገመተ እንደሆነ የባለሥልጣኑን አስተያየት ባለመ ቀበል ስምምነቱን ላያፀድቀው ይችላል ።

፫· ፍርድ ቤቱ ከባለሥልጣኑ የቀረበለት መረጃ በቂ መስሎ ያልታየው እንደሆነ አዲስ ምርመራ በማከናወን ተጨማሪ መረጃ እንዲቀርብለት ባለሥልጣንን ለማዘዝ እንዲሁም ሌሎች ግለሰቦች ሆኑ ድርጅቶች አስፈላጊ መስሎ የሚታ ያቸውንና በእጃቸው የሚገኘውን መረጃ እንዲሰጡ ለማዘዝ ይችላል ።

አንቀጽ ፪፻፱ የፍርድ ቤቱ ሥልጣን

፩· የጉዲፈቻ ስምምነት ፍርድ ቤት ካላፀደቀው በስተቀር ውጤት አይኖረውም ።

፪· ፍርድ ቤቱ የጉዲፈቻ ስምምነቱን ከማጽደቁ አስቀድሞ በወሳኝ መልኩ ለልጁ መልካም አስተዳደግና ጥቅም የሚበጅ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት ።

፫· ከዚህ በላይ በአንቀጽ ፪፻፯ እና ፪፻፰ የተመለከቱትና የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፪/ አጠቃላይ አነጋገር እንደተ ጠበቀ ሆኖ ፍርድ ቤቱ የጉዲፈቻ ስምምነቱን ከማጽደቁ በፊት የሚከተሉትን ከግምት ማስገባት አለበት ፤

www.abyssinialaw.com



ሀ) ልጅየው ስለጉዲፈቻ ስምምነት ያለውን አስተያየት
ለ) አስቀድሞ ፈቃድ ያልሰጠ ከሆነም የአሳዳሪውን አስተያየት
ሐ) የጉዲፈቻ አድራጊው ልጁን ለማሳደግና ለመንከባከብ ያለው ብቃት
መ) የጉዲፈቻ አድራጊው የውጭ ዜጋ ሲሆን ልጅየው በኢትዮጵያ ውስጥ የሚያድግበት ሁኔታ አለመኖሩን
ሠ) ጉዲፈቻ አድራጊው እንደልጁ አድርጐ እንደሚያሳድገውና አለአግባብ መጠቀሚያ እንደማያደርገው ለመገመት የሚያስችል መረጃ መኖሩን ፤

፬· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፫/ በፊደል ተራ /ሠ/ የተመለከተውን በሚያጣራበት ጊዜ ጉዲፈቻ አድራጊው የውጭ ዜጋ ሲሆን ፍርድ ቤቱ ልዩ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርበታል ።

አንቀጽ ፩፻፺ የጉዲፈቻ ስምምነት የማይሠረዝ ስለመሆኑ፣

፩· የጉዲፈቻ ስምምነት በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ /፪/ ከተመለከተው ሁኔታ ውጭ ሊሠረዝ አይችልም ።

፪· የጉዲፈቻ አድራጊው በጉዲፈቻ የተቀበለውን ልጅ እንደልጁ በማሳደግ ፈንታ በባርነት ወይም ባርነትን በሚመስል ሁኔታ ወይም ከግብረገብ ውጭ በሆነ ፤ ተግባሮች እንዲሰማራ በማድረግ መጠቀሚያ ያደረገው እንደሆነ ወይም በማናቸውም ሌላ መንገድ የልጁን የወደፊት ሕይወት ክፉኛ በሚጐዳ አኳኋን የያዘው መሆኑን የተረዳ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ የጉዲፈቻ ስምምነቱን ለመሠረዝ ይችላል ።

አንቀጽ ፩፻፺፩ የጉዲፈቻ ስምምነት እንዲሠረዝ አቤቱታ ስለማቅረብ

፩· የጉዲፈቻ ልጅ ራሱ ፣ የሕፃናትን ደህንነት ለመከታተል ሥልጣን የተየሰጠው የመንግሥት አካል በጉዳዩ ያገባኛል የሚል ማንኛውም ሰው ከዚህ በላይ በተመለከተው አንቀጽ የተደነገገውን መሠረት በማድረግ የጉዲፈቻ ስምምነት እንዲሠረዝ አቤቱታ ለማቅረብ ይችላል ።

www.abyssinialaw.com



፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ መሠረት አቤቱታ ሲቀርብለት ፣ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን እንዲያጣራው ያዘዘው ሰው በፊት ለአቤቱታ ምክንያት ናቸው የተባሉትን መረጃዎች እውነት ሆነው ቢገኙ የጉዳዩን ስምምነቱን ለማፍረስ በቂ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለበት።

## ምዕራፍ አሥራ ሁለት
## ቀለብ የመስጠት ግዴታ

### አንቀጽ ፪፻፲፱ ስለግዴታው ይዘት

በዚህ ሕግ በአንቀጽ ፪፻፲፫ ድንጋጌዎች መሠረት ቀለብ የመስጠት ግዴታ ያለበት ሰው እንደ ባለጉዳዮቹ ሁኔታና እንደ አካባቢው ልማድ የሚስማማውን በመከተል ለቀለብ ተቀባዩ ምግብ፣ መኖሪያ፣ ልብስ፣ ጤናውን የሚጠብቅ በትና እንደሁኔታው ለትምህርት አስፈላጊ የሆነውን ነገር መስጠት አለበት።

### አንቀጽ ፪፻፲፫ ግዴታው በእነማን መካከል ስለመሆኑ

፩· በዚህ ሕግ አንቀጽ ፶፰ ንዑስ አንቀጽ /፩/ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ቀለብ የመስጠት ግዴታ የሚኖረው በቀጥታ ወላጆችና ተወላጆች ወይም በቀጥታ የጋብቻ ዘመዳሞች መካከል ነው።

፪· እንዲሁም ወንድማማቾችና እህትማማቾች በሆኑት መካከል ቀለብ የመስጠት ግዴታ ይኖራል።

### አንቀጽ ፪፻፲፬ ግዴታ ስለሚቀርበት ሁኔታ

ጋብቻው የፈረሰው በሞት ምክንያት ካልሆነ በስተቀር በጋብቻ ዘመዶች መካከል ያለው ቀለብ የመስጠት ግዴታ ቀሪ ይሆናል።

### አንቀጽ ፪፻፲፭ ቀለብ ተቀባዩ መብቱን ስለሚያጣበት ሁኔታ

ቀለብ ተቀባዩ በቀለብ ሰጪው ወይም በዚህ ሰው ወደ ላይና ወደታች በሚቆጠሩ ወላጆች ወይም ተወላጆች ወይም ባል ወይም ሚስት ሕይወት ወይም ንብረት ላይ የወንጀል ተግባር የፈጸመ ወይም ለመፈጸም የሞከረ ስለመሆኑ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ቀለብ የመቀበል መብቱን ያጣል።

www.abyssinialaw.com



**አንቀጽ ፪፻፲፮ ግዴታው እንዲኖር አስፈላጊ ሁኔታዎች**

ቀለብ የመስጠት ግዴታ ተፈፃሚ የሚሆነው ቀለብ ጠያቂው ሠርቶ ለመኖር አስፈላጊ የሆነ ገቢ ለማግኘት አቅም የሌለው ወይም የመሥራት አቅም ቢኖረውም ሥራ ማግኘት ያልቻለና በችግር ላይ የሚገኝ ሲሆን ብቻ ነው።

**አንቀጽ ፪፻፲፯ ስለግዴታው አፈፃፀም**

፩· በመሠረቱ ቀለብ የመስጠት ግዴታ የሚፈጸመው ቀለብ ሰጪው ለቀለብ ተቀባዩ የቀለቡን ገንዘብ በመስጠት ነው።

፪· የቀለቡ መጠን የሚወሰነው ቀለብ ጠያቂው ያለበትን ችግር እና የቀለብ ሰጪውን አቅም በማመዛዘን ነው።

**አንቀጽ ፪፻፲፰ ሁኔታውን ማሻሻል የሚቻል ስለመሆኑ**

ቀለብ ሰጪው ወይም ተቀባዩ በሚያቀርቡት ጥያቄ መሠረት ስለቀለቡ መጠን ወይም ስለቀለብ ተቀባዩ መኖሪያ የተሰጠውን ውሣኔ በማናቸውም ጊዜ ማሻሻል ይችላል።

**አንቀጽ ፪፻፲፱ ቀለቡ ስለሚከፈልበት ቦታ**

ቀለቡ የሚከፈለው በተቻለ መጠን ለቀለብ ተቀባዩ በሚያመቸው ቦታ ይሆናል።

**አንቀጽ ፪፻፳ የቀለብ ገንዘብ ሊተላለፍና ሊያዝ የማይቻል ስለመሆኑ**

፩· ለቀለብ የሚከፈል ገንዘብ ሊተላለፍ ወይም ሊያዝ አይችልም።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ የተደነገገው ቢኖርም ለቀለብ የሚከፈል ገንዘብ የሚከፈልበት ጊዜ ከመድረሱ አስቀድሞ ቢሆንም እንኳ ቀለብ ተቀባዩ ላለበት ችግር አሳቢ ለሚሆኑ ለዕርዳታ ለተቋቋሙ ድርጅቶች ሊተላለፍ ይችላል።

፫· እንዲሁም ለቀለብ ተቀባይ ኑሮ አስፈላጊ የሆነውን ነገር ያበደሩት ሌሎች ሰዎች በተመለከተ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ ድንጋጌ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

www.abyssinialaw.com



**አንቀጽ ፪፻፳፩ የቀለብ ገንዘብ የማይጠራቀም ስለመሆኑ**

ቀለብ ተቀባዩ ለኑሮው አስፈላጊ መሆኑን ካላረጋገጠ በቀር የቀለቡን ገንዘብ በመቀበል ካለበት ቀን ጀምሮ በተከ ታዮቹ ሦስት ወራት ውስጥ ያልተቀበለው ወይም ሳይጠ ይቀው የቀረ እንደሆነ የተጠራቀመ ቀለብ እንዲሰጠው መጠየቅ አይችልም።

**አንቀጽ ፪፻፳፪ ቀለብ ተቀባዩን በቀለብ ሰጭው ቤት ለማኖር ስለመቻል**

፩· ቀለብ ሰጪው ቀለብ ተቀባዩን በመኖሪያ ቤቱ ተቀብሎ በማስቀመጥ ቀለብ የመስጠት ግዴታውን ሊፈጽም ይችላል።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ ስለተመለከተው ጉዳይ ክርክር የተነሣ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ የነገሩን የአካባቢ ሁኔታዎች በመመልከት ተገቢ መስሎ የታየውን ይወስናል።

፫· ቀለብ ሰጪው ቀለብ ተቀባዩን በመኖሪያ ቤቱ እንዲያስ ቀምጥ ምን ጊዜም ቢሆን አይገደድም።

**አንቀጽ ፪፻፳፫ ስለቀለብ ሰጪዎች ብዛት /፩/ መሠረቱ**

ለቀለብ ተቀባዩ ቀለብ የመስጠት ግዴታ ያለባቸው ሰዎች ብዙ፣ የሆኑ እንደሆነ ከእነርሱ መካከል አንዱ ቀለቡን እንዲሰጠው ሊጠይቀው ይችላል።

**አንቀጽ ፪፻፳፬ /፪/ ስለአቤቱታ**

፩· ቀለብ የመስጠት ግዴታ ያለባቸው ሰዎች ብዙ ሆነው ከእነርሱ መካከል አንዱ ወይም ከዚያ በላይ የሆኑት ቀለቡን የከፈሉ እንደሆነ ሳይከፍሉ የቀሩት ድርሻቸውን እንዲከፍሏ ቸው ለመጠየቅ ይችላል።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ ስለተመለከተው ጉዳይ ክርክር የተነሣ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ተከሣሾቹ ያላቸውን ሀብትና ከከሣሽ ጋር ያላቸውን የሥጋ ወይም የጋብቻ ዝምድናና ደረጃ በማመዛዘን ተከሣሾቹ የቀለቡን ገንዘብ በሙሉ ወይም በከፊል እንዲከፍሉ ሊወስንባቸው ይችላል።

www.abyssinialaw.com


አንቀጽ ፪፻፳፩ /፫/ ለቀለብ ሰጪዎች የሚሰጥ የከፋይነት ተራ

በዚህ ሕግ አንቀጽ ፪፻፲፫ መሠረት ቀለብ የመስጠት ግዴታ ያለባቸው ሰዎች ቅደም ተከተል

ሀ) በመጀመሪያ ደረጃ ባል ወይም ሚስት

ለ) በሁለተኛ ደረጃ ተወላጆች እንደየደረጃቸው

ሐ) በሦስተኛ ደረጃ ወደላይ የሚቆጠሩ ወላጆች እንደየ ደረጃቸው

መ) በአራተኛ ደረጃ ወንድማማቾችና እህትማማቾች

ሠ) በአምስተኛ ደረጃ የጋብቻ ወደላይ የሚቆጠሩ ወላጆች እንደየደረጃቸው

አንቀጽ ፪፻፳፪ በጋራ ቀለብ ሰጪዎች መካከል የሚደረግ ስምምነት

፩· የጋራ ቀለብ ሰጪዎች እርስ በራሳቸው ስላላቸው ግንኙነት ለጋራ ቀለብ ተቀባያቸው ከእነርሱ መካከል አንዱ ቀለቡን እንዲሰጠው በማለት የሚፀና ስምምነት ለማድረግ ይችላሉ።

፪· ቀለብ ተቀባይ ስምምነቱን ወዶ የተቀበለ እንደሆነ ይህንን ስምምነት የሚያከራክርበት ከባድ ምክንያት ካልተገኘ በቀር ቀለቡን ከሌሎች ቀለብ ሰጪዎች መጠየቅ አይችልም።

አንቀጽ ፪፻፳፫ ስለጉዲፈቻ ልጅ ልዩ ሁኔታ

፩· የጉዲፈቻ ልጅ ባል ወይም ሚስትና የቀጥታ መስመር ተወላጆች የጉዲፈቻ አድራጊው ቤተዘመዶች ቀለቡን መስጠት በማይችሉበት ሁኔታ ካልተገኙ በቀር የሥር ወላጆቹን ቤተዘመዶች ቀለብ ለመጠየቅ አይችልም።

፪· የቀደምት ቤተሰቦቹ ወደላይ የሚቆጠሩ ወላጆች ቀለብ ለማግኘት ከዘመዳቸው አንዱን ለመጠየቅ የማይችሉ ካልሆነ በቀር በጉዲፈቻ የሰጡትን ልጅ ቀለብ ሊጠይቁት አይችሉም።

አንቀጽ ፪፻፳፬ ስለ ሥርዓተ ቀብር ወጪ

፩· ቀለብ የመስጠት ግዴታ ያለበት ሰው ለዚህ ለተባለው ሰው ሥርዓተ ቀብር የወጣውን ወጪ ለመክፈል ይገደዳል።

www.abyssinialaw.com


፪· ይህን ወጪ ያደረገው ሰው ወጪው እንዲተካለት ቀለብ ሰጪውን ለመጠየቅ ይችላል።

አንቀጽ ፪፻፳፱ ልዩ ስምምነቶች

ልዩ ስምምነቶች በማድረግ በዚህ ምዕራፍ የተደነገጉትን ድንጋጌዎች ለመለወጥ አይፈቀድም።

## ምዕራፍ አሥራ ሦስት
## አካለ መጠን ስላልደረሱ ሰዎች
### ክፍል ፩
### ጠቅላላ ድንጋጌዎች

አንቀጽ ፪፻፴ ትርጓሜ

አካለ መጠን ያልደረሰ ሰው ማለት ፆታ ሳይለይ ዕድሜው አሥራ ስምንት ዓመት ያልሞላው ልጅ ነው።

አንቀጽ ፪፻፴፩ አካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ ችሎታ የሌለው ስለመሆኑ

፩· አካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ ስለ መልካም አስተዳደጉና ደህንነቱ ጉዳይ በአንድ አሳዳሪው እየተጠበቀ ይቆያል።
፪· ንብረት ነክ ጥቅሞቹንና በአጠቃላይ የንብረቱን አስተዳደር በሚመለከት በሞግዚቱ ይወከላል።
፫· በሕግ በግልጽ ለተመለከቱት ጉዳዮች ካልሆነ በስተቀር አካለ መጠን ያልደረሰው ሰው ሕጋዊ ድርጊቶችን ለመፈጸም አይችልም።

አንቀጽ ፪፻፴፪ የዕድሜ ማስረጃ

፩· የአንድ ሰው ዕድሜ የሚረጋገጠው በልደት ምስክር ወረቀት ነው።
፪· የልደት ምስክር ወረቀት የሌለ እንደሆነ ዕድሜውን በአስተማማኝነት ለማረጋገጥ ያስችላሉ በሚባሉ ሠነዶች ወይም ከሁለት ያላነሱ ምስክሮችን ቃል መሠረት በማድረግ ፍርድ ቤት ዕድሜውን ይወስናል።

አንቀጽ ፪፻፴፫ ውሣኔ ሰጪ አካላት መከተል ስላለባቸው መርህ

በዚህ ምዕራፍ መሠረት ውሣኔ የሚሰጥባቸው ጉዳዮች ሁሉ ለልጆች ደህንነትና መልካም አስተዳደግ የሚበጅ

www.abyssinialaw.com



መሆን ይኖርባቸዋል።

## ክፍል ፪
## አካለ መጠን ያልደረሰን ልጅ ስለሚጠብቁ ተቋሞች

### አንቀጽ ፪፻፶፩ የወላጆች ሥልጣን

አባትና እናት ጋብቻው ፀንቶ ባለበት ጊዜ ሁሉ አካለ መጠን ላልደረሱት ልጆቻቸው የአሳዳሪነትና የሞግዚትነት የጋራ ሥልጣን አላቸው።

### አንቀጽ ፪፻፶፪ ከወላጆቹ የአንዱ ብቁ አለመሆን

፩· ከወላጆች አንዱ የሞተ፣ ችሎታ ያጣ፣ የተጋቢነት መብት ያጣ፣ ወይም ከቤተዘመድ አስተዳዳሪነት መብቱ የታገደ እንደሆነ የአሳዳሪነትና ሞግዚትነት ሥልጣኑን ይዞ የሚቆየው አንደኛው ወገን ብቻ ይሆናል።

፪· እንዲሁም የልጁ አባት ያልታወቀ በሆነ ጊዜ የዚህን ሥልጣን ሥራ የምትፈጽመው እናቱ ብቻ ትሆናለች።

### አንቀጽ ፪፻፶፫ የልጆቹ አባትና እናት መፋታት

፩· በዚህ ሕግ አንቀጽ ፹፪ መሠረት ባልና ሚስት በስምምነት ሲፋቱ የልጆቻቸውን አሳዳሪነትና ሞግዚትነትን በተመለከተ በስምምነት ይወስናሉ።

፪· በማናቸውም የፍቺ ሁኔታ የልጆቻቸውን አሳዳሪነትና ሞግዚትነት ባልና ሚስቱ በስምምነት ሊወስኑ ካልቻሉ፣ ፍችውን የወሰነው ፍርድ ቤት ስለ ልጆቹ አሳዳሪና ሞግዚትም አብሮ ይወስናል።

### አንቀጽ ፪፻፶፬ በኑዛዜ ቃል የተመረጠ አሳዳሪ ወይም ሞግዚት /፩/ መሠረቱ

፩· አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ በሕይወት ያለው ወላጅ ከሞቱ በኋላ ልጁን የሚያስተዳድር ወይም ለልጁ ሞግዚት የሚሆነውን ሰው በመጨረሻ በኑዛዜ ቃል ለመምረጥ ይችላል።

፪· እንዲሁም የአሳዳሪውን ወይም የሞግዚቱን ሥልጣን ለመወሰንና የአሳዳጊነቱን የሥራ አመራር ሥልጣን ለተወሰነ ሁኔታ ብቻ ለመስጠት ይችላል።

www.abyssinialaw.com



**አንቀጽ ፪፻፵፰ /፪/ አሳዳሪ ወይም ሞግዚት ለመሾም የሚፈጸም ግዴታ**

አባት ወይም እናት በሕይወት ሳለ አካለ መጠን ያልደረሰውን ልጅ የአሳዳሪነት ወይም ሞግዚትነት ሥራ ያካሂድ የነበረ ካልሆነና በዚሁም ጊዜ በገዛ ፈቃዱ ሥልጣኑን አውቆ የተወ ካልሆነ በስተቀር ከዚህ በላይ በአንቀጽ ፪፻፵፯ ለአባት ወይም ለእናት የተሰጠው መብት አይኖርም።

**አንቀጽ ፪፻፵፱ /፫/ ለፍርድ ቤት አቤቱታ ስለማቅረብ**

አካለ መጠን ያልደረሰውን ልጅ ጥቅም የሚያስገድድ ሆኖ የተገኘ እንደሆነ ስለ አሳዳሪው ወይም ስለሞግዚቱ አባት ወይም እናቱ ያደረጉትን ውሣኔ ፍርድ ቤት ሊሽረው ወይም ሊያሻሽለው ይችላል።

**አንቀጽ ፪፻፶ የልጅን አሳዳሪነት ወይም የሞግዚትነት ሥልጣን ሊይዙ የሚገባቸው ዘመዶች /፩/ ሊከተሉት የሚገባ ቅደም ተከተል**

አንድ ልጅ አባትና እናት የሌለው እንደሆነና ከሁለቱ በመጨረሻ የሞተው ወላጅ በሚገባ ሁኔታ አሳዳሪ ወይም ሞግዚት ሳያደርግለት ቀርቶ እንደሆነ ለልጁ አሳዳሪነት ወይም ሞግዚትነት በሕጉ መሠረት የሚመረጡና ይህ ሥልጣን የሚሰጣቸው ከዚህ ቀጥሎ የተመለከቱት ሰዎች ናቸው።

ሀ) የልጁ ወደ ላይ የሚቆጠሩ ወላጆች

ለ) እነዚህ በሌሉ ጊዜ አካለ መጠን የደረሱ የልጁ ወንድሞች ወይም እህቶች፣

ሐ) እነዚህ በሌሉ ጊዜ የልጁ አጐት ወይም አክስት

**አንቀጽ ፪፻፶፩ /፪/ ይህ ቅደም ተከተል ስለሚለወጥበት ሁኔታ**

፩· ከዚህ በላይ በተመለከተው መሠረት ሥልጣን በሚሰጠው ሰው ምትክ ለልጁ የሥጋ ዝምድና ወይም የጋብቻ ዝምድና ያለው ማንኛውም ሰው የአሳዳሪነቱ ወይም የሞግዚትነቱ ሥልጣን ይሰጠኝ ሲል ጥያቄ ለማቅረብ ይችላል።

www.abyssinialaw.com



፪· ይህም ጥያቄ መቅረብ የሚገባው ቅደም ተከተሉ ለሚመለከታቸው ዘመዶች ሲሆን ስምምነት ካልተገኘ ግን ጉዳዩ ለፍርድ ቤት ይቀርባል።

፫· ጥያቄው መቅረብ ያለበት አሳዳሪው ወይም ሞግዚቱ ይህን ሥልጣን መያዙ ከታወቀበት ቀን ጀምሮ በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ ይሆናል።

፬· ጥያቄውን ለመቀበል ወይም ላለመቀበል መሠረት የሚሆነው የልጁ ደህንነትና ጥቅም ሊሆን ይገባል።

አንቀጽ ፪፻፵፪ በሕግ የሚመረጡ ዘመዶች መታጣት

፩· ከዚህ በላይ ባሉት አንቀጾች የተመለከተውን መሠረት በማድረግ ለልጁ አንድ አሳዳሪ ወይም ሞግዚት ለማግኘት ያልተቻለ እንደሆነ ይህን ሥራና ሥልጣን ፍርድ ቤት ለመረጠው ሰው ሊሰጥ ይችላል።

፪· ፍርድ ቤቱ ይህን ጉዳይ ለመወሰን የልጁ ዘመድ በሆነ ወይም ባልሆነ ያገባኛል ባይ በሚቀርብ ጥያቄ ሊመሠረት ይችላል።

፫· የሕፃናትን ደህንነት ለመከታተል ሥልጣን የተሰጠው የመንግሥት አካልም ጉዳዩን ለፍርድ ቤት ሊያቀርብ ይችላል።

አንቀጽ ፪፻፵፫ የፍርድ ቤት ምርጫ /፩/ አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ የሥጋ ወይም የጋብቻ ዘመዶች

ፍርድ ቤት ለልጁ አሳዳሪ ወይም ሞግዚት እንዲሆን የሚመረጠውና ይህን ሥልጣን የሚሰጠው የልጁ የቅርብ የሥጋ ዘመድ የሆነን ወይም የጋብቻ ዝምድና ያለውና በተቻለም መጠን ይህን ሥራ ለማከናወን ችሎታና ፈቃደኛነት ያለውን ሰው ነው።

አንቀጽ ፪፻፵፬ /፪/ የበጐ አድራጐት ድርጅት

ፍርድ ቤቱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የአሳዳሪነት ወይም የሞግዚትነቱን ሥልጣን ለዚህ ዓይነት ጉዳይ ለተቋቋመው የበጐ አድራጐት ድርጅት ሊሰጥ ይችላል።

www.abyssinialaw.com



## አንቀጽ ነ፪፻፲፭ ተመሳሳይ ሁኔታዎች

ከዚህ በላይ ለተገለጹት ድንጋጌዎች አፈፃፀም አንድ ሰው በሕግ ወይም በሌላ ማናቸውም ምክንያት የአሳዳሪነት ወይም የሞግዚትነት ተግባሮቹን ለማከናወን የማይችል እንደሆነ እንደሌለ ይቆጠራል።

## አንቀጽ ፪፻፲፮ የአሳዳሪው ወይም የሞግዚቱ መታወቂያ

፩· በመሠረቱ አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ አሳዳሪ እንዲሆን ሥልጣን ተሰጥቶት የልጁን አሳዳሪነት የተቀበለው ሰው ሞግዚቱም ነው።

፪· የነገሩ ሁኔታ ተቃራኒ ትርጉም የሚሰጥ ካልሆነ በስተቀር በሕይወት ያለው አባት ወይም እናት ወይም ፍርድ ቤት ለልጁ የሚሾመው ሞግዚት ወይም አሳዳሪ ሁለቱንም ሥልጣን እንደያዘ ይቆጠራል።

## አንቀጽ ፪፻፲፯ ለአባትና ለእናት የተሰጠ መብት

አባት ወይም እናት ጉዳዩ ጠቃሚ መስሎ የታያቸው እንደሆነ የልጃቸውን የአሳዳሪነት ሥልጣን ራሳቸው ይዘው ሞግዚት ለመሾም ይችላሉ።

## አንቀጽ ፪፻፲፰ ለፍርድ ቤት የተሰጠ ሥልጣን

ፍርድ ቤት የልጁን አሳዳሪና ሞግዚት የመሾም ሥልጣን በያዘበት ጊዜና ይህን ለማድረግ አሳማኝ ምክንያት ሲኖር፣ ከአሳዳሪው በተጨማሪ ሌላ ሞግዚት ለመሾም ይችላል።

## አንቀጽ ፪፻፲፱ ምትክ ሞግዚት /፩/ በሞግዚቱና አካለመጠን ባልደረሰው ልጅ መካከል ስለሚነሳ የጥቅም ግጭት

፩· በሞግዚቱና አካለመጠን ባልደረሰው ልጅ መካከል የጥቅም ግጭት የተነሣ እንደሆነ ፍርድ ቤት አካለመጠን ላልደረሰው ልጅ ምትክ ሞግዚት ይሾምለታል።

፪· ምትክ ሞግዚት የሚመረጠው በሞግዚቱ ወይም ወደላይ ከሚቆጠሩ የልጁ ወላጆች ወይም አካለ መጠን ከደረሱ ወንድሞቹና እህቶቹ በአንዳቸው ጥያቄ አቅራቢነት ነው።

www.abyssinialaw.com



**አንቀጽ ፪፻፶ /፪/ አካለ መጠን ባልደረሱት ብዙ ልጆች መካከል ስለሚነሣ የጥቅም ግጭት**

፩· አካለ መጠን ባልደረሱ በብዙ ልጆች መካከል የጥቅም ግጭት የተፈጠረ እንደሆነና የነዚህም ተጠሪ ወኪል አንድ የጋራ ሞግዚት ብቻ በሆነ ጊዜ ከዚህ በላይ በአንቀጽ ፪፻፵፱ የተመለከተው ድንጋጌ ተፈፃሚ ይሆናል።

፪· የጥቅም ግጭት የሚፈታውም በሞግዚቱና በምትክ ሞግዚቱ መካከል በሚደረግ ስምምነት መሠረት ይሆናል።

**አንቀጽ ፪፻፶፩ የሥራው አጀማመር**

፩· የአሣዳሪነቱ ወይም የሞግዚትነቱ ሥራ የሚጀመረው አሳዳሪው ወይም ሞግዚቱ በሕጉ መሠረት ወይም በፍርድ ውሣኔ ተመርጠው እንደተሾሙ ወዲያውኑ ነው።

፪· ሆኖም የአሳዳሪነት ወይም የሞግዚትነት ሥራ የተሰጠው መሆኑን ከማወቁ በፊት አሳዳሪው ወይም ሞግዚቱ ይህን ሥራ ሳይጀምር ለደረሰው ጉዳት ሁሉ በኃላፊነት ሊጠይቅ አይችልም።

**አንቀጽ ፪፻፶፪ ሥራው የግዴታ ስለመሆኑ**

የአሳዳሪነት ወይም የሞግዚትነት ሥራ እንዲያከናውን ተመርጦ የተሾመ ማንኛውም ሰው ሥራውን የማከናውን ግዴታ አለበት።

**አንቀጽ ፪፻፶፫ ሥራው እንዲቀርለት የሚቀርብ ጥያቄ**

፩· አንድ ሰው የአሳዳሪነት ወይም የሞግዚትነት ተግባርን ማከናወን በራሱ ላይ ከበድ ያሉ ችግሮችን በአጠቃላይ ኑሮውም ላይ እንቅፋት የሚያስከትልበት ከሆነ ሥራው እንዲቀርለት ፍርድ ቤቱን ሊጠይቅ ይችላል።

፪· እንዲሁም በተጨማሪ ሁኔታ አሳዳሪው ወይም ሞግዚቱ ከተሰጠው የአሳዳሪነት ወይም የሞግዚትነት ሥራው እንዲሻር ጥያቄ ማቅረብ ይችላል።

www.abyssinialaw.com



**አንቀጽ ፪፻፶፩ በሕግ አግባብ የሚሰጥ ልዩ አስተያየት**

በዚህ ሕግ መሠረት ለአሳዳሪነት ወይም ለሞግዚትነት ስለሚመረጡ ሰዎች የተደነገገው ቢኖርም ከዚህ የሚከተሉት ሰዎች በአሳዳሪነት ወይም በሞግዚትነት እንዳይሾሙ ወይም እንዲሻሩ ጥያቄ ካቀረቡና ይህም ጥያቄ የራሳቸውን ልጆች የሚመለከት ካልሆነ በቀር የአሳዳሪነት ወይም የሞግዚትነት ሥራ እንዲሠሩ አይገደዱም፣

ሀ) ዕድሜው ስድሣ አምስት ዓመት የሞላው ሰው፣
ለ) አካለ መጠን ያልደረሱ አራት ልጆች ያሉት ሰው፣
ሐ) በውትድርና የተሰማሩ ሰዎች።

**አንቀጽ ፪፻፶፪ ለጊዜው ሥራውን የማከናወን ግዴታ**

፩· የልጁ አሳዳሪነት ወይም የሞግዚትነት ሥራ ችግር ያደርስብኛል ብሎ ምክንያት በማቅረብ ይህ ኃላፊነት እንዲወገድለት የሚጠይቅ አሳዳሪ ወይም ሞግዚት በዚህ ሥራ ሌላ አሳዳሪ ወይም ሞግዚት ተተክቶ ሥልጣኑን እስኪረከበው ድረስ የተሰጠውን ሥራ ለጊዜው የማከናወን ግዴታ አለበት።

፪· እንዲሁም በሹመቱ ላይ ተቃውሞ የተነሣበት አሳዳሪ ወይም ሞግዚትም ተመሳሳይ ግዴታ ይኖርበታል።

**አንቀጽ ፪፻፶፫ ስለ ሥራው መቅረት**

፩· የአሳዳሪው ወይም የሞግዚቱ ሥራ ቀሪ የሚሆነው የሚጠበቀው ልጅ የሞተ እንደሆነ ወይም አካለ መጠን በደረሰ ጊዜ ወይም ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ በወጣ ጊዜ ነው።

፪· እንዲሁም አሳዳሪው ወይም ሞግዚቱ ሲሞት ወይም ችሎታ ሲያጣ ወይም ብቁ ያለመሆኑ ሲገለጽ ወይም ከሥራው ሲሻር ቀሪ ይሆናል።

፫· በመጨረሻም አዲስ አሳዳሪ ወይም ሞግዚት አካለ መጠን ላልደረሰው ልጅ ሲሾምለት የቀድሞዎቹ ተሿሚዎች ኃላፊነት ያበቃል።

**አንቀጽ ፪፻፶፬ ችሎታ ማጣት /፩/ አካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ**

የራሱን ልጆች በሚመለከት ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር፣ አካለ

www.abyssinialaw.com



መጠን ያልደረሰ ልጅ የአሳዳሪነት ወይም የሞግዚትነት ሥራን ለማካሄድ ችሎታው የለውም።

አንቀጽ ፪፻፶፰ /፪/ በፍርድ የተከለከሉ ሰዎች

፩· በፍርድ የተከለከለ ማንኛውም ሰው የአሳዳሪነት ወይም የሞግዚትነት ሥራን ለማከናወን አይችልም።

፪· ይህን ሥራ ያከናውን የነበረ አንድ ሰው ችሎታ ያጣ መሆኑ በፍርድ ቤት ውሣኔ የተገለጸ እንደሆነ፣ የዚህ ሰው ሞግዚት በሕግ መሠረት የተከለከለውን ሰው ሥራ ተረክቦ በምትክነት ማካሄድ ለሚገባው ሰው ወዲያውኑ ማስታወቅ አለበት።

፫· እንዲህ ያለ ሰው የሌለም እንደሆነ በፍርድ የተከለከለው ሰው ምትክ እንዲደረግለት ሞግዚቱ ለፍርድ ቤት ጥያቄ ማቅረብ አለበት።

አንቀጽ ፪፻፶፱ ብቁ ስላለመሆን

፩· አንድ ሰው የአሳዳሪነት ወይም የሞግዚትነት ሥራ ለማካሄድ ብቁ አይደለም ብሎ ፍርድ ቤት ለመወሰን የሚችለው የወንጀል ተግባር በመፈጸሙ የግል ነፃነትን የሚከለክል የእሥራት ወይም የሞት ቅጣት የተፈረደበት ሲሆን ነው።

፪· ፍርድ ቤት የዚህን ዓይነት ቅጣት በአንድ ሰው ላይ በሚወስንበት ጊዜ ነገሩ ተገቢ መሆኑን የገመተ እንደሆነ የተፈረደበት ሰው ለዚህ ሥራ ብቁ አለመሆኑን ጭምር ለመወሰን ይችላል።

አንቀጽ ፪፻፷ /፩/ የአሳዳሪው መሻር

፩· አካለ መጠን ላልደረሰ ልጅ አሳዳሪ እንዲሆን የተሾመ ሰው ልጁ ለኑሮው አስፈላጊ የሆነውን ጥበቃ ሳያገኝ ወይም ከሞራል ጋር የሚስማማ የአእምሮ አስተዳደግ ወይም ከችሎታው ጋር ተመዛዛኝ የሆነ ትምህርት እንዲያገኝ ሳይደረግለት የቀረ እንደሆነ አሳዳሪው እንዲሻር ፍርድ ቤት ሊወስን ይችላል።

፪· ይህንንም ውሣኔ ለመስጠት አሳዳሪው የሚኖርበትን የአካባቢ ሁኔታና ጊዜውንም መመርመርና መሠረት

www.abyssinialaw.com


ማድረግ አስፈላጊ ነው።

፫· በተለይም ፍርድ ቤቱ አሳዳሪውን ለመሻር የሚችለው አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ ወንጀል መሥራቱ የተረጋገጠ ሲሆንና ይህንንም ወንጀል የፈጸመው በመጥፎ አስተዳደግ ወይም በአሳዳሪው ጉድለት ተገቢውን የግብረ ገብ ትምህርት ለማግኘት ባለመቻሉ የሆነ እንደሆነ ነው።

አንቀጽ ፪፻፷፩ /፪/ የሞግዚቱ መሻር

አካለ መጠን ላልደረሰ ልጅ ሞግዚት የሆነ ሰው እንዲሻር ፍርድ ቤት የሚወሰነው ሞግዚቱ የልጁን ንብረትና ሀብት በመጥፎ ሁኔታ ያስተዳደረና አጠባበቁም በቂ ያልሆነ እንደሆነ፣ ወይም ልጁን በሞግዚ ትነት እንዲያስተዳድር ሥልጣን የሰጠው ሰው ወይም አካል የሰጠውን መመሪያና የንብረት አስተዳደር ሥርዓት ሳይጠብቅና ሳይፈጽም የቀረ እንደሆነ ወይም ዕዳ ለመክፈል ያለመቻሉ በፍርድ ውሣኔ የተረጋገጠ እንደሆነ ነው።

አንቀጽ ፪፻፷፪ /፫/ የወላጆች መሻር

፩· የልጁ አባት ወይም እናት ወይም ሌሎች ወደላይ የሚቆጠሩ ወላጆቹ ከልጃቸው አሳዳሪነት ወይም ሞግዚ ትነት ሥራቸው እንዲሻሩ መወሰን ሲያስፈልግ ፍርድ ቤቱ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ይጠበቅበታል።

፪· ፍርድ ቤቱ በዚህ ጉዳይ ላይ የሰጠውን ውሣኔ በተሻረው ወገን ጠያቂነት በማንኛውም ጊዜ እንደገና ሊመረምር ይችላል።

አንቀጽ ፪፻፷፫ /፬/ ሥነ ሥርዓት

፩· አንድ አሳዳሪ ወይም ሞግዚት እንዲሻር የሚቀርበው ጥያቄ፣ በማናቸውም በጉዳዩ ያገባኛል ባይ ወገን ወይም በዐቃቤ ሕግ በኩል ሊቀርብ ይችላል።

፪· ፍርድ ቤቱ አሳዳሪውን ወይም ሞግዚቱን ለመሻር ከመወሰኑ በፊት በርሱ በኩል ያለውን ሃሣብ ሊያዳ ምጠው ይገባል።

www.abyssinialaw.com



፫· ሆኖም ፍርድ ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፪/ የተመለከተውን ሲያከናውን በልጁ ደህንነት ወይም ሀብት ላይ ተጨማሪ ጉዳት ይደርሳል ተብሎ የሚገመት ከሆነ ተገቢ መስሎ የታየውን ጊዜያዊ ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል።

አንቀጽ ፪፻፷፬ የፍርድ ቤት ኃላፊነት

፩· ፍርድ ቤት አንድን ሰው አካለ መጠን ላልደረሰ ልጅ አሳዳሪነት ወይም ሞግዚትነት ለመሾም ሲመርጥ ወይም የተሾመውን ከሥራው ሲሽር ከውሣኔው በፊት በተቻለ መጠን ከልጁ ወደ ላይ የሚቆጠሩ ወላጆች፣ አካለ መጠን ከደረሱ ወንድሞቹና እህቶቹ ጋር መመካከር ይገባዋል።

፪· አስፈላጊ መስሎ ሲታየው አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ ያለውን ሃሣብ ሊያዳምጥ ይችላል።

፫· ፍርድ ቤቱ ውሣኔውን ሲሰጥ አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ ጥቅም የማይጓደልበትን አሠራር ብቻ መከተል እንጂ የቀረቡለትን ሃሣቦች የመቀበል ግዴታ አይኖርበትም።

አንቀጽ ፪፻፷፭ ሥራው ያለዋጋ የሚከናወን ስለመሆኑ

፩· አሳዳሪነትና የሞግዚትነት ሥራ የሚከናወነው ማናቸውም ዋጋ ሳይከፈልበት በነፃ ነው።

፪· ሆኖም አሳዳሪው ወይም ሞግዚቱ ሥራውን ለማከናወን ረጅም ጊዜ የሚጠይቀው የሆነ እንደሆነ እንደነገሩ ሁኔታ አንድ የተወሰነ አበል ሊቆረጥለት ይችላል።

፫· ይህም አበል አካለ መጠን ካልደረሰው ልጅ የሀብት ገቢ ላይ ካልሆነ በስተቀር ከሌላ ሀብት ሊወሰድ አይችልም ፣ የአበሉም ልክ ከጠቅላላው የሀብት ገቢ ሲሶ ሊበልጥ አይችልም ።

አንቀጽ ፪፻፷፮ የሥራው አካሄድ የግል ስለመሆኑ

፩· የአሳዳሪነቱ ወይም የሞግዚትነቱ ሥራ የግል ጠባይ የያዘ ስለሆነ ሥራውን የሚያከናውነው ራሱ እንጂ ለአሳዳሪው ወይም ለሞግዚቱ ወራሾች ሊተላለፍ አይችልም ።

፪· ወራሾቹ በኃላፊነት የሚጠየቁት አሳዳሪው ወይም

www.abyssinialaw.com



ሞግዚቱ በፈጸመው የሥራ አካሄድ ጉድለት ብቻ ነው ። ይኸውም በውርስ ሕግ መሠረት ይወሰናል ።

አንቀጽ ፪፻፷፯ የወራሾች ግዴታ

፩· የአንድ አሳዳሪ ወይም ሞግዚት ወራሾች አሳዳሪው ወይም ሞግዚቱ እንደሞተ ወዲያውኑ በዚህ ህግ አንቀጽ ፪፻፵ በተመለከተው መሠረት ለሚቹ ምትክ ሊሆን ለሚገባው ሰው የማስታወቅ ግዴታ አለባቸው ።

፪· የዚህ ዓይነት ሰው የሌለ እንደሆነ ፣ በሚቹ ምትክ የሚመረጠው ሰው እንዲሾም ለፍርድ ቤት ማስታወቅ አለባቸው ።

፫· የአሳዳሪው ወይም የሞግዚቱ ወራሾች ከዚህ በላይ ባሉት ንዑሳን አንቀጾች የተመለከቱትን ግዴታዎች እስኪወጡ ድረስ አካለመጠን ላልደረሰው ልጅም ሆነ ለሌላ ሦስተኛ ወገኖች ኃላፊዎች ሆነው ይቆያሉ ።

አንቀጽ ፪፻፷፰ የአሳዳሪነትና የሞግዚትነት ማስረጃ

አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ አሳዳሪነቱን ወይም ሞግዚትነቱን የሚያስረዳለት ጽሑፍ እንዲሰጠው አሳዳሪው ወይም ሞግዚቱ ፍርድ ቤቱን ለመጠየቅ ይችላል ።

አንቀጽ ፪፻፷፱ ከሞግዚት ጋር የሚመሳሰል ሁኔታ

ሞግዚትን የሚመለከቱት የዚህ ሕግ ድንጋጌዎች በምትክ ሞግዚት ጉዳይም ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል።

## ክፍል ፫
## የአሳዳሪውና የሞግዚቱ ሥልጣን
### ንዑስ ክፍል ፩
### አካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ አስተዳደግና ጥበቃ

አንቀጽ ፪፻፸ አሳዳሪው የመንግሥት ተቋማትን እገዛ መጠየቅ ስለመቻሉ

አሳዳሪው ከዚህ በታች በተመለከቱት አንቀጾች የተሰጠውን ሥልጣን በሥራ ላይ ለማዋል እንዲችል አግባብነት ያላቸውን የመንግሥት ተቋሞች እገዛ ሊጠይቅ ይችላል ።

www.abyssinialaw.com



**አንቀጽ ፪፻፷፩ አካለ መጠን ስላልደረሰ ልጅ መኖሪያ ቦታ**

፩· አሳዳሪው አካለ መጠን ያልደረሰውን ልጅ የመኖሪያ ቦታ ይወስናል ።

፪· አካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ ያለአሳዳሪው ፈቃድ የተመደ በለትን የመኖሪያ ቦታ ሊተው አይችልም ።

፫· አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ የተመደበለትን የመኖሪያ ቦታ ትቶ የሄደ እንደሆነ አሳዳሪው ወደ መኖሪያ ቦታው እንዲመለስ ሊያስገድደው ይችላል።

**አንቀጽ ፪፻፷፪ አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ጤና አጠባበቅ**

፩· አሳዳሪው አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ጤንነት ሁኔታ ይከታተላል ።

፪· አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ሲታመም ከሕመሙ እንዲ ፈወስ አስፈላጊውን እርምጃ ሁሉ ይወስዳል ።

**አንቀጽ ፪፻፷፫· አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ አስተዳደግ**

፩· አሳዳሪው አካለ መጠን ያልደረሰውን ልጅ አስተዳደግ ይመራል ።

፪· አሳዳሪው አካለ መጠን ላልደረሰው ልጅ መልካም አስተ ዳደግ ተገቢነት ያለው የዲስፕሊን እርምጃ ለመውሰድ ይችላል ።

**አንቀጽ ፪፻፷፬· አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ ማህበራዊ ግንኙነት**

፩· አሳዳሪው አካለ መጠን ያልደረሰውን ልጅ ማህበራዊ ግንኙነት ይመራል ፣ ይቆጣጠራል ።

፪· ሆኖም አሳዳሪው በቂ ምክንያት ሳይኖረው አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ወደ ላይ ከሚቆጠሩ ወላጆቹ ጋር ግንኙነት እንዳያደርግ ሊያግደው አይችልም ።

**አንቀጽ ፪፻፷፭· አጠቃላይ እና የሙያ ትምህርት የመስጠት ግዴታ**

አሳዳሪው አካለመጠን ላልደረሰው ልጅ ዕድሜና ችሎታ ተመጣጣኝ የሆነ አጠቃላይ ትምህርት ወይም የሙያ ሥልጠና እንዲያገኝ ማድረግ አለበት ።

www.abyssinialaw.com



አንቀጽ ፪፻፹፮· አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ገቢ /፩/ መሠረቱ

፩· አሳዳሪው አካለ መጠን ያልደረሰውን ልጅ ገቢዎች በመቀበል ለልጅየው ጥቅም ያውላል ።

፪· አሳዳሪው ገንዘቡን ለምን አገልግሎት እንዳዋለው መግለጫ ለመስጠት አይገደድም ።

አንቀጽ ፪፻፹፯ /፪/· ከፍተኛ ስለሆነ ገቢ

፩· አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ ገቢ ከፍተኛ ሲሆንና አሳዳሪው የልጁ አባት ወይም እናት ያልሆነ እንደሆነ ፍርድ ቤት ከዚህ በላይ በአንቀጽ ፪፻፹፮ /፪/ የተመለከተው ድንጋጌ ተፈፃሚ እንዳይሆን ሊያግድ ይችላል ።

፪· ፍርድ ቤቱ ትዕዛዙን በሚሰጥበት ጊዜ አካለ መጠን ላልደረሰው ልጅ ለአስተዳደጉና ትምህርቱ በቂ ነው የሚለውን የገንዘብ መጠንና የሚከፈልበትን ጊዜ በመወሰን ለአሳዳሪው እንዲሰጠው ያደርጋል ።

፫· ተራፊውን ገንዘብ በአትራፊ ሥራ ላይ እንዲያውለው በሞግዚቱ እጅ ተቀማጭ ይደረጋል ።

አንቀጽ ፪፻፹፰ /፫/· አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ ከሥራው ስለሚያገኘው ገቢ

፩· አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ ዕድሜው ከ፲፭ ዓመት በላይ ሲሆን ከሥራው የሚያገኘውን ገቢ ራሱ ይቀበላል።

፪· ለራሱ ቀለብ የሚሆነውን ለአሳዳሪው ከሰጠ በኋላ ቀሪውን ገንዘብ በዚህ ሕግ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ሊጠቀምበት ሙሉ ነፃነት አለው ።

አንቀጽ ፪፻፹፱ /፬/· በስጦታ ወይም በውርስ ስለተላለፉ ሀብቶች

፩· አካለ መጠን ላልደረሰው ልጅ በስጦታ ወይም በውርስ ሀብት የሚያስተላልፍ ሰው ልጁ አካለመጠን ሳይደርስ አሳዳሪው ተቀብሎ ጥቅም ላይ እንዳያውለው ሊያዝ ይችላል ።

፪· በስጦታው ውል ወይም በኑዛዜው ስለንብረቱ አስተዳደርና ስለሚገኘውም ገቢ የተመለከቱት ኃይለ ቃሎች ተፈፃሚ መሆን አለባቸው ።

www.abyssinialaw.com



**አንቀጽ ፪፻፹· የመክፈያ ጊዜያቸው ያልደረሱ ገቢዎች**

የመክፈያ ጊዜአቸው ያልደረሱ ገቢዎችን አሳዳሪው ግዴታ ሊገባባቸው አይችልም ፡፡

**አንቀጽ ፪፻፹፩· ስለወላጆች ሥልጣን**

፩· አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ አባትና እናት በጋራ አሳዳሪዎቹ በሆኑ ጊዜ የአሳዳሪነት ተግባራቸውን በመመካከርና በመግባባት ይወጣሉ ፡፡

፪· አባትና እናት ያለመግባባታቸውን በግላቸው ወይም በሽምግልና ለመፍታት ያልቻሉ እንደሆነ ፣ ከሁለቱ አንደኛው በሚያቀርበው አቤቱታ መነሻነት ፍርድ ቤቱ አካለመጠን ላልደረሰው ልጅ ጥቅም ቅድሚያ በመስጠት ውሣኔ ይሰጣል ፡፡

፫· ከዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፪/ የተመለከተው ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ፣ አባትና እናት በአሳዳሪነታቸው በሚሰጡት ውሣኔ ላይ አቤቱታ ሊቀርብበት አይችልም።

**አንቀጽ ፪፻፹፪· የወላጆች መለያየት**

ወላጆች በመለያየታቸው ምክንያት የአሳዳሪነቱ ሥልጣን የአንደኛው ወላጅ ብቻ የሆነ እንደሆነ፣ ይኸው ወላጅ በሚሰጠው ውሣኔ ላይ የአሳዳሪነት ተግባር በማከናወን ላይ የሌለው ወገን ወደላይ ከሚቆጠሩ ወላጆች ወይም አካለ መጠን ከደረሱ ወንድሞቹና እህቶቹ አንዳቸው አቤቱታ ለፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላሉ ፡፡

**አንቀጽ ፪፻፹፫· አሳዳሪው አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ ወላጅ በማይሆንበት ጊዜ**

አሳዳሪው አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ወላጅ ያልሆነ እንደሆነ ፣ በልጁ አስተዳደግ ረገድ በሚሰጠው ውሣኔ ላይ ከወላጆቹ አንዳቸው ወይም ሌላ በጉዳዩ ያገባኛል የሚል ሰው ወይም ዐቃቤ ሕግ ለፍርድ ቤት አቤቱታ ሊያቀርብ ይችላል ፡፡

www.abyssinialaw.com



## ንዑስ ክፍል ፪
## አካለ መጠን ያልደረሰን ልጅ ንብረት ስለማስተዳደር

**አንቀጽ ፪፻፹፬· ,መሠረቱ፣**

፩· ሀብቱንና ንብረት ነክ ጥቅሞቹን በተመለከተ አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ በሞግዚቱ ይወከላል ።

፪· ሀብቱንና ንብረት ነክ ጥቅሞቹን በማስከበርና በማስተ ዳደር ረገድ ሞግዚቱ ከፍተኛ ጥንቃቄ የማድረግ ግዴታ አለበት ።

**አንቀጽ ፪፻፹፭· የንብረት ቆጠራና የዋጋ ግምት /፩/ ሞግዚቱ የሞግዚ ትነት ሥራውን ከጀመረ በኋላ**

፩· ሞግዚቱ ፣ የሞግዚትነቱን ሥራ ከጀመረ በኋላ በሁለት ወራት ጊዜ ውስጥ ሦስት ምስክሮች ባሉበት አካለ መጠን ያልደረሰውን ልጅ ንብረት ይቆጥራል ፣ የዋጋውንም ግምት ያወጣል ።

፪· ሞግዚቱ አካለመጠን ካልደረሰው ልጅ የሚጠይቀው ዕዳ ሲኖር ፣ በንብረት ቆጠራው መዝገብ በወቅቱ ካላሰፈረው በስተቀር የዕዳው ክፍያ ቀሪ ይሆንበታል ።

**አንቀጽ ፪፻፹፮ /፪/· አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ የውርስ ሀብት**

፩· አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ ወራሽ በሚሆንበት ጊዜ ሞግዚቱ ስለልጁ ሆኖ ውርሱን ከመቀበሉ አስቀድሞ ሦስት ምስክሮች ባሉበት የውርስ ንብረቱን ቆጠራ ያከናውናል ፣ የዋጋውንም ግምት ያወጣል ።

፪· ሞግዚቱ ከውርስ ሀብቱ ውስጥ ድርሻ ያለው እንደሆነ ፣ ይህንኑ በንብረት ቆጠራው መዝገብ ያላሰፈረው እንደሆነ ድርሻው ቀሪ ይሆንበታል ።

፫· የንብረት ቆጠራው ባለመከናወኑ ወይም በአግባቡ ባለመ ሠራቱ ለሚደርስ ጉዳት ሞግዚቱ በኃላፊነት ይጠየቅ በታል ።

**አንቀጽ ፪፻፹፯· የሞግዚቱ ንብረት አካለመጠን ካልደረሰው ልጅ ንብረት ጋር ስለሚቀላቀልበት ሁኔታ**

፩· ሞግዚቱ አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ንብረት ከግል

www.abyssinialaw.com



ንብረቱ ጋር እንዳይቀላቀል አስፈላጊውን ጥንቃቄ ሁሉ ማድረግ አለበት ።

፪· በተለይም አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ገንዘብ ሞግዚቱ በራሱ የባንክ ሂግብ ማስቀመጥ ወይም እንዲቀመጥ ማድረግ አይፈቀድለትም ።

**አንቀጽ ፪፻፹፰· የገንዘብ ሠነዶችና ሌሎች ውድ ዕቃዎች ስለሚቀመጡበት ሁኔታ**

አካለ መጠን ያልደረሰውን ልጅ ንብረት በማስተዳደር ረገድ ችግር የሚፈጥር ካልሆነ በስተቀር ፣ የገንዘብ ሠነዶችን ፣ ውድ ዕቃዎቹን ፣ ጠቃሚ ጽሑፎችንና ሌሎች ተመሳሳይ ነገሮችን ሁሉ ሞግዚቱ ሊጠፉ ወይም ሊባክኑ በማይችሉበት አስተማማኝ ስፍራ ማስቀመጥ አለበት ።

**፪፻፹፱· የፍርድ ቤት ሥልጣን**

፩· አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ ሞግዚት የልጁ ወላጅ ባልሆነ ጊዜ ፣ አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ሀብት መልካም አስተዳደር በሚመለከት ለሞግዚቱ መመሪያ እንዲሰጥ የልጁ ወደላይ ከሚቆጠሩ ወላጆች ወይም አካለመጠን ከደረሱ ወንድሞቹ ወይም እህቶቹ አንዳቸው ለፍርድ ቤት ጥያቄ ማቅረብ ይችላሉ።

፪· ፍርድ ቤቱም አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ሀብት አጠቃላይ ሁኔታ ፣ የሞግዚቱን ችሎታና የልጅየውን ጥቅም በማመዛዘን ስለሀብቱ አስተዳደር ጠቃሚ መስሎ የሚታየውን መመሪያ ይሰጠዋል ።

**አንቀጽ ፪፻፺· አካለመጠን ላልደረሰው ልጅ በስጦታ ወይም በውርስ ስለሚተላለፍ ንብረት**

፩· አካለመጠን ላልደረሰው ልጅ ንብረት በስጦታ ወይም በውርስ የሚያስተላልፍ ሰው የንብረቱን አስተዳደር በሚመለከት ተገቢ ናቸው የሚላቸውን የአሠራር መመሪያዎች ሞግዚቱ እንዲከተል ሊያዝ ይችላል ።

፪· የአሠራር መመሪያዎቹን ተከትሎ ለመሥራት የማይቻል ወይም አካለመጠን ባልደረሰው ልጅ ጥቅም ላይ ጉዳት

www.abyssinialaw.com



የሚያደርስበት መስሎ የታየው እንደሆነ ፣ ሞግዚት መመሪያዎቹ እንዲስ ተካከሉበት ፍርድ ቤትን ሊጠይቅ ይችላል ።

አንቀጽ ፪፻፺፩· ስለንግድ ድርጅቶችና ሌሎች መሰል ድርጅቶች

፩· የንግድ ፣ የኢንዱስትሪ ወይም ሌሎች መሰል ድርጅቶች አካለመጠን ያልረሰው ልጅ ሀብት አካል የሆኑ እንደሆነ ፣ ወደላይ ከሚቆጠሩ ወላጆቹ ወይም አካለመጠን ከደረሱ ወንድሞቹና እህቶቹ አንዳቸው በሚያቀርቡት ጥያቄ የልጁ አባት ወይም እናት ያልሆነው ሞግዚት ንብረቱን እንዲያጣራ ወይም እንዳለ እንዲቀጥል እንዲያደርግ ፍርድ ቤት ሊያዘው ይችላል ።

፪· ፍርድ ቤቱ ይህንን ትዕዛዝ በሚሰጥበት ጊዜ ሞግዚትንቱ ለምን ያህል ጊዜ እንደሚቆይ የሞግዚቱን ችሎታና አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ጥቅም ከግምት ውስጥ ማስገባት አለበት ።

አንቀጽ ፪፻፺፪· አንዳንድ ንብረቶችን ስለመሸጥ

፩· ሞግዚቱ አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ንብረት የሆኑ የሚንቀሳቀሱ ግዙፍ ንብረቶችን ፣ አክስዮኖችንና የገንዘብ ሠነዶችን ለመሸጥ ይችላል ።

፪· በልጁ አባት ወይም እናት ላይ ካልሆነ በስተቀር ፣ በጉዳዩ ያገባኛል የሚል ማናቸውም ሰው ጥያቄ ሲያቀርብለት ፍርድ ቤት ስለሽያጩ መመሪያ ለመስጠት ወይም ሽያጩ እንዳይካሄድ ለመከልከል ይችላል ።

አንቀጽ ፪፻፺፫· ለእምጪው እንዲከፈል ስለሚሉ ሠነዶች

፩· አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ አባት ወይም እናት ያልሆነ ሞግዚት ለእምጪው እንዲከፈል የሚሉ ሠነዶች የልጁ ሀብት ከሆኑበት ጊዜ ጀምሮ በሦስት ወራት ውስጥ እንዲሸጡ ወይም በልጁ ስም በተመዘገቡ ሠነዶች እንዲ ለወጡ ማድረግ አለበት ።

፪· ሞግዚቱ ጥያቄ ሲያቀርብለት ፣ ፍርድ ቤቱ ከዚህ በላይ በንዑስ አንቀጽ /፩/ ከተመለከተው ግዴታ ነፃ እንዲሆን ሊያዝ ይችላል ።

www.abyssinialaw.com



አንቀጽ ፪፻፺፩· ዕዳዎችና ገቢ ገንዘቦች

፩· ሞግዚቱ አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ዕዳዎች ከልጁ ሀብት በመቀነስ ይከፍላል ።

፪· አካለመጠን ላልደረሰው ልጅ መከፈል የሚገባውን ካፒታል እና ሌላ ገቢ ይቀበልለታል ፣ ስለመቀበሉ ፣ ለማረጋገጥም ደረሰኝ ይሰጣል ።

አንቀጽ ፪፻፺፫· ካፒታልን አትራፊ በሆነ ሥራ ላይ ስለማዋል /፩/ የሞግዚቱ ግዴታ

፩· የገንዘቡ መጠን ከ፭፻ ብር በላይ የሆነ አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ካፒታል ሞግዚቱ አትራፊ በሆነ ሥራ ላይ ማዋል አለበት ።

፪· ፍርድ ቤት በዚህ አንቀጽ ንዑስ /፩/ የተመለከተውን የገንዘብ መጠን ሊያሻሽለው ይችላል ።

አንቀጽ ፪፻፺፯ /፪/· የጊዜ ገደብ

፩· ካፒታሉ በሞግዚቱ እጅ በገባ በሦስት ወራት ውስጥ በአትራፊ ሥራ ላይ ማዋል አለበት ።

፪· ፍርድ ቤቱ የጊዜውን መጠን ሊያሻሽለው ይችላል።

አንቀጽ ፪፻፺፯· ኃላፊነት

፩· በአትራፊ ሥራ ላይ ላልዋለው ገንዘብ ሞግዚቱ ሕጋዊ ወለዱን አካለመጠን ላልደረሰው ልጅ መክፈል አለበት ።

፪· አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም ተጨማሪ የጉዳት ካሣ እንዲከፍል ሊፈረድበት ይችላል ።

አንቀጽ ፪፻፺፰· ገቢዎች

፩· አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ገቢዎች ፣ ገቢዎቹ በቂ ሆነው የማይገኙ ሲሆንም ከሀብቱ ቀንሶ ለአስተዳደጉና ለትምህርቱ አገልግሎት እንዲውል ሞግዚቱ ለአሳዳሪው ይሰጠዋል ።

፪· ፍርድ ቤቱ በሌላ አኳኋን ካልወሰነ በስተቀር ፣ ለዚህ አገልግሎት የሚውለው ገንዘብ በየወሩ ለአሳዳሪው ይከፈላል ።

፫· የአከፋፈሉ ሁኔታ በአሳዳሪውና በሞግዚቱ ስምምነት

www.abyssinialaw.com


ወይም በፍርድ ቤት በሚሰጥ ውሣኔ መሠረት ሊሻሻል ይችላል ፡፡

አንቀጽ ፪፻፺፱· የኪራይ ውሎች

በፍርድ ቤት ፈቃድ የተደረጉ ካልሆኑ በስተቀር ፣ ሞግዚቱ የሚያደርጋቸውን የኪራይ ውሎች ልጅየው አካለመጠን ከደረሰ ከሦስት ዓመታት በኋላ እንዲፈጸ ማቸው አይገደድም ፡፡

አንቀጽ ፫፻· ስለውርስ

፩· ልጁ በውርስ የሚያገኘውን ንብረት ሞግዚቱ ይቀበላል ፡፡
፪· ሞግዚቱ የውርሱ ሀብት ዕዳውን ለመክፈል ፈጽሞ የማይችል ካልሆነ በስተቀር ውርሱን አልፈልግም ለማለት አይችልም ፡፡

አንቀጽ ፫፻፩· ስለስጦታ

፩· አካለመጠን ላልደረሰው ልጅ የሚሰጠው ስጦታ ጠቃሚነት የለውም በማለት ካልሆነ በቀር ሞግዚቱ አልቀበልም ለማለት አይችልም ፡፡
፪· በተለምዶ ከሚሰጡ አነስተኛ ስጦታዎች ውጪ ሞግዚቱ አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ንብረት በልጁ ስም በስጦታ ለመስጠት አይችልም ፡፡

አንቀጽ ፫፻፪· የዋስትና ግዴታ መግባት የማይችል ስለመሆኑ

ሞግዚቱ አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ንብረት ለሌላ ሰው ዕዳ በዋስትና ሊያሲይዝ አይችልም ፡፡

አንቀጽ ፫፻፫· ስለግልግል

ክርክር የሚደረግበት ጥቅም ከአንድ ሺህ ብር ያነሰ ካልሆነ ወይም አካለ መጠን ያልደረሰውን ልጅ ጥቅም በሚመለከት ፍርድ ቤት ካልፈቀደ በስተቀር ሞግዚቱ ጉዳዩን በግልግል ለመጨረስ አይችልም ፡፡

አንቀጽ ፫፻፬· ሞግዚቱ አካለመጠን ካልደረሰው ልጅ ጋር ስለሚያደርጋቸው ውሎች

www.abyssinialaw.com



፩· ሞግዚቱ ፍርድ ቤት ካልፈቀደለት በስተቀር አካለመጠን ያልደረሰውን ልጅ ንብረት ለመግዛት ፣ በኪራይ ለመጠቀም ወይም ሌላ ማናቸውም ውል ከእርሱ ጋር ለመፈጸም አይችልም ።

፪· እንዲሁም ሞግዚቱ በፍርድ ቤት ካልተፈቀደለት በስተቀር አካለመጠን ባልደረሰው ልጅ ላይ ማናቸውም መብት ወይም ገንዘብ የሚጠይቅበትን መብት ለመቀበል አይችልም ።

አንቀጽ ፫፻፫· ስለብድር

ፍርድ ቤት ካልፈቀደ በስተቀር ፣ ሞግዚቱ አካለመጠን ባልደረሰው ልጅ ስም የብድር ውል ለመዋዋል አይችልም ።

አንቀጽ ፫፻፬· አካለ መጠን ካልደረሰው ልጅ ጋር መመካከር ስለማስፈለጉ

፩· አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ ዕድሜ ከአሥራ አራት ዓመት ያነሰ ካልሆነ በስተቀር ሞግዚቱ የልጁ ዕድሜ በሚፈቅድለት መጠንና እርሱን የሚመለከቱ ከፍተኛ ጉዳዮች በተነሱ ጊዜ አካለ መጠን ያልደረሰውን ልጅ ማማከር አለበት ።

፪· አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ ፈቃዱን መስጠቱ ሞግዚቱን ከተጠያቂነት አያድነውም ።

አንቀጽ ፫፻፭· ሞግዚቱ አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ እንዲሠራ ስለሚሰጠው ፈቃድ /፩/ መሠረቱ

፩· አካለ መጠን ያልደረሰውን ልጅ ዕድሜና የገንዘብ አቅም መሠረት በማድረግ የዕለት ጉዳዮችን የሚመለከቱ ውሎችን ብቻ እንዲያደርግ ሞግዚቱ ፈቃድ ሊሰጠው ይችላል ።

፪· ይኸው ፈቃድ በዝምታም ሊሰጥ ይችላል ።

አንቀጽ ፫፻፮· /፪/ የዕለት ጉዳዮች

፩· ድርጊቱ እንዲፈጸም የፍርድ ቤት ፈቃድ የሚያስፈልገው እንደሆነ በምንም መንገድ የዕለት ጉዳይ ሊባል

www.abyssinialaw.com


አይችልም።

፪· አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ከ፫፻ ብር በላይ ግዴታ እንዲገባ የሚያስገድደው ሲሆን ድርጊቱ የዕለት ጉዳይ ነው ሊባል አይችልም።

አንቀጽ ፫፻፱· /፫/ በሞግዚቱ ላይ ስለሚኖረው ውጤት

አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ በሞግዚቱ ፈቃድ ለሚገባቸው ግዴታዎች ሞግዚቱ ለሦስተኛ ወገኖች ዋስ ነው።

አንቀጽ ፫፻፲· ኑዛዜ

፩· ሞግዚቱ አካለ መጠን ባልደረሰው ልጅ ስም ኑዛዜ ሊያደርግ አይችልም

፪· አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ ፲፮ ዓመት ሳይሞላው ኑዛዜ ማድረግ አይችልም።

፫· አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ ፲፮ ዓመት ሳይሞላው የሚያደርገው ኑዛዜ ፲፮ ዓመት ከሞላው በኋላ ባይሰር ዘውም ውጤት አይኖረውም።

አንቀጽ ፫፻፲፩· ንብረት ለማስተዳደር ሞግዚት ስለሚያደርገው ወጪ

ሞግዚቱ አካለ መጠን ላልደረሰው ልጅ ጥቅም ሲል ከግሉ የሚያወጣቸው ወጪዎች እንዲተኩለት መብት አለው።

አንቀጽ ፫፻፲፪· አካለ መጠን ስላልደረሰው ልጅ ሀብት አስተዳደር ሪፖርት ማቅረብ ያለበት ስለመሆኑ

፩· ሞግዚቱ አካለመጠን ያልደረሰው ልጅ ሀብት አስተዳደር ሁኔታና ሂሣቡን የሚያመለክት ሪፖርት አዘጋጅቶ መያዝ አለበት።

፪· አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ ወደ ላይ የሚቆጠሩ ወላጆች ወይም አካለመጠን የደረሱ ወንድሞቹና እህቶቹ በጋራ ወይም በተናጠል ጥያቄ ሲያቀርቡለት ሞግዚቱ የአስተዳደርና የሂሣብ ሪፖርቱን እንዲመለከቱት ያደርጋል።

አንቀጽ ፫፻፲፫· ተፈፃሚነት

በዚህ ሕግ ከአንቀጽ ፪፻፰፱ እስከ ፪፻፹፩ የተመለከቱት

www.abyssinialaw.com


ድንጋጌዎች ለሞግዚትም ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል።

## ክፍል ፬
## አካለ መጠን ያልደረሰን ልጅ ለመጠበቅ የተመለከቱትን ደንቦች መጣስ ስለሚያስከትለው ውጤት
### ንዑስ ክፍል ፩
### አካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ ሥራዎች

አንቀጽ ፫፻፲፬· መሠረቱ

አካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ ከሥልጣኑ በላይ የሚፈጽ ማቸው ሕጋዊ ድርጊቶች ሁሉ ፈራሽ ይሆናሉ።

አንቀጽ ፫፻፲፭· እንዲፈርስ ስለመጠየቅ

አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ የፈጸማቸው ሕጋዊ ድርጊቶች እንዲፈርሱ መጠየቅ የሚችሉት አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ ወይም ወራሾች ወይም ወኪሎች ናቸው።

አንቀጽ ፫፻፲፮· ስለተዋዋዮች ቅን ልቦና

፩· ከዚህ በላይ በአንቀጽ ፫፻፲፬ የተደነገገው ቢኖርም ሌላው ተዋዋይ ወገን ከልጁ ጋር የተዋዋለው ይህንን እንዲያ ደርግ ፈቃድ አለው ብሎ በቅን ልቦና በማመን የሆነ እንደሆነ ውሉ የፀና ይሆናል።

፪· ሌላው ተዋዋይ በልጁ አላዋቂነት የተጠቀመ ከሆነ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ የተደነገገው ተፈፃሚነት አይኖረውም።

አንቀጽ ፫፻፲፯· ስለሚመለስ ገንዘብ

፩· አካለ መጠን ላልደረሰው ልጅ የተከፈለ ገንዘብ ሊመለስ የሚችለው ውሉ እንዲፈርስ ክስ በቀረበበት ቀን በልጅነ በተገኘው መጠን ብቻ ይሆናል።

፪· ከዚህ ሁኔታ ውጪ አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ ለመመለስ አይገደድም።

፫· ሞግዚቱ አካለ መጠን ላልደረሰው ልጅ ሲል ለፈጸማቸው ሕጋዊ ድርጊት ኃላፊ አይሆንም።

www.abyssinialaw.com

**አንቀጽ ፫፻፲፰· ከውል ውጭ ስለሚደርስ ኃላፊነትና ያለአግባብ ስለመበልፀግ /፩/ መሠረቱ**

አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ ሕገወጥ በሆኑ ሥራዎች ያለአግባብ የበለፀገ ወይም በሌላ ሰው ላይ ጉዳት ያደረሰ እንደሆነ በፍትሐብሔር ሕግ ውስጥ ከውል ውጭ ስለሚደርስ ኃላፊነትና ያለአግባብ ስለመበልጸግ በተደነገገው መሠረት ተጠያቂ ይሆናል።

**አንቀጽ ፫፻፲፱· /፪/ አካለ መጠን ሳይደርስ ደርሻለሁ ማለት**

፩· አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ አካለ መጠን ሳይደርስ ደርሻለሁ ብሎ ቢናገርም እንኳ ይህን በመናገሩ ብቻ አካለመጠን ባለመድረሱ ምክንያት የሚጠቀምበትን መብት አያጣም።

፪· እንዲሁም አካለ መጠን ደርሻለሁ ማለቱ ከውል ውጭ የሆነ ኃላፊነትን የሚያመጣ ጥፋት ሆኖ አይቆጠርበትም።

## ንዑስ ክፍል ፪
## የሞግዚቱ ሕጋዊ ድርጊቶች

**አንቀጽ ፫፻፳· በደንብ ስለተፈጸሙ ድርጊቶች**

፩· ሞግዚቱ አካለ መጠን ላልደረሰው ልጅ የፈጸማቸው ሕጋዊ ድርጊቶች ሁሉ ልጁ አካለ መጠን በደረሰ ጊዜ እንዲፈጽማቸው ተቆጥረው በኃላፊነት ያስጠይቁታል።

፪· ሞግዚቱ በኃላፊነት እጠየቅበታለሁ ሲል ግዴታ የገባበት ወይም በሕግ መሠረት ግዴታ የተጣለበት ካልሆነ በስተቀር አካለ መጠን ላልደረሰው ልጅ ሲል ለፈጸማቸው ሕጋዊ ድርጊቶች ኃላፊ አይሆንም።

**አንቀጽ ፫፻፳፩· ሕጋዊ ድንጋጌዎች ስለመተላለፍ**

የሕግ ድንጋጌዎችን በመተላለፍ ሞግዚቱ ለሚፈጽማቸው ድርጊቶች ወኪል የሆነ ሰው ከተሰጠው ሥልጣን በላይ በሚሠራበት ጊዜ አግባብነት ያላቸው የውክልና ሕግ ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል።

www.abyssinialaw.com



አንቀጽ ፫፻፳፪· ስለሦስተኛ ወገኖች

፩· ፍርድ ቤት ለሞግዚቱ የተሰጠውን መመሪያ ሦስተኛ ወገኖች ካላወቁ ወይም ማወቅ የሚገባቸው ካልሆነ በስተቀር ሞግዚቱ መመሪያውን መተላለፉ በሦስተኛ ወገኖች ላይ መቃወሚያ ሊሆን አይችልም።

፪· አካለ መጠን ላልደረሰው ልጅ ንብረቱን የሰጠ የተናዘዘ ወይም የተወ ሰው ለሞግዚቱ መመሪያ በሰጠ ጊዜም የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ ድንጋጌ ተፈፃሚ ይሆናል።

አንቀጽ ፫፻፳፫· ስለምትክ ሞግዚት

በዚህ ንዑስ ክፍል የተደነገጉ ድንጋጌዎች በምትክ ሞግዚትም ላይ ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል።

## ንዑስ ክፍል ፫
## በኃላፊነት ሊያስጠይቁ ስለሚችሉ ድርጊቶች

አንቀጽ ፫፻፳፬· ስለሞግዚት

፩· ሞግዚቱ በፈጸመው የንብረት አስተዳደር ጉድለት ምክንያት ወይም መመሪያ ባለመከበሩ ወይም የእርሱ ጥቅም አካለ መጠን ካልደረሰ ልጅ ጥቅም ጋር የሚጋጭ ሆኖ እያለ ድርጊቱን በመፈጸሙ አካለመጠን ባልደረሰ ልጅ ላይ ለሚደርሰው ጉዳት ሁሉ በኃላፊነት ይጠየቃል።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ የተመለከተው ድንጋጌ በምትክ ሞግዚትም ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

## ክፍል ፭
## አካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ ችሎታ ማጣት ስለመቅረቱ

አንቀጽ፫፻፳፭· ችሎታ ማጣት ስለሚቀርባቸው ምክንያቶች

አካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ ችሎታ የለውም መባሉ የሚቀረው

ሀ) አካለ መጠን ሲደርስ ወይም
ለ) ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ ይውጣ ሲባል ነው።

www.abyssinialaw.com


## ንዑስ ክፍል ፩
## ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ ስለመውጣት

**አንቀጽ ፫፻፳፯· ጋብቻ**

አካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ በዚህ ሕግ አንቀጽ ፲፯ ንዑስ አንቀጽ /፪/ በተመለከተው መሠረት ጋብቻ የፈጸመ እንደሆነ በጋብቻው ምክንያት ብቻ ከሞግዚት አስተ ዳደር ነፃ ይወጣል።

**አንቀጽ ፫፻፳፰· በልዩ ሁኔታ ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ ስለመውጣት**

፩· አካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ ፲፭ ዓመት ሲሞላው አሳዳሪው ወይም ሞግዚቱ ወይም ያገባኛል የሚል ሌላ ሰው ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ እንዲወጣ መጠየቅ ይችላል።

፪· ፍርድ ቤት ጥያቄው ሲቀርብለት የልጁን ሁኔታና ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ እንዲወጣ የተጠየቀበትን ምክንያት ተመልክቶ ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ መሆኑ ለልጁ የሚጠቅም ሆኖ ካገኘው ጥያቄውን ተቀብሎ ሊፈቅድ ይችላል።

**አንቀጽ ፫፻፳፱· ውጤቶች**

ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ የወጣ ልጅ በሕግ አካለ መጠን እንደደረሰ ሆኖ ይቆጠራል።

**አንቀጽ ፫፻፴· የማይሻር ስለመሆኑ**

፩· አካለ መጠን ያልደረሰ ልጅ ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ እንዲሆን የተሰጠ ፈቃድ ሊሻር አይችልም።

፪· በጋብቻ ምክንያት የተገኘው ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ የመሆን ሁኔታ ጋብቻው ቢፈርስም እንኳን ውጤቱ እንደተጠበቀ ይቀራል።

፫· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፪/ የተደነገገው ቢኖርም ጋብቻው የፈረሰው ለጋብቻ የተፈቀደው ሕጋዊ ዕድሜ ባለመጠበቁ ምክንያት የሆነ እንደሆነ ከሞግዚት አስተ ዳደር ነፃ መውጣቱን በተመለከተ ፍርድ ቤቱ ተገቢ መስሎ የታየውን ሊወስን ይችላል።

www.abyssinialaw.com


## ንዑስ ክፍል ፱
## የሞግዚትነት ሥራ ሂሳቦችን ስለማስታወቅ

**አንቀጽ ፫፻፴· መሠረቱ**

፩· ሞግዚቱ የሞግዚትነት ሥራው ሲያበቃ፣ ሞግዚት ሆኖ ለአስተዳደረው ሰው ወይም ለወራሾቹ ያስተዳደረበትን ሂሳብ ማቅረብ አለበት።

፪· እንዲሁም በሞግዚትነት ያስተዳደረውን ሰው ንብረት ሁሉ ማስረከብ፣ የመብቶቹን ሁኔታና የሚገደድባቸው ዕዳዎች ካሉም ማስታወቅ አለበት።

**አንቀጽ ፫፻፴፩· የንብረቶች በመዝገብ አለመግባት**

፩· ሞግዚቱ የሞግዚትነት ሥራውን በያዘበት ጊዜ ወይም አካለ መጠን ላልደረሰው ልጅ በውርስ ሀብት ሲሰጠው የንብረቶቹን ዝርዝር በመዝገብ ከመያዝ ቸል ያለ እንደሆነ፣ የልጁን ንበረት፣ በውርስ ወይም በስጦታ ያገኘውን ሀብት በማናቸውም ሁኔታ ለማስረዳት ይቻላል።

፪· ሌላ ተቃራኒ ማስረጃ ካልቀረበ በስተቀር፣ ምስክሮች በሚሰጡት ቃል አንድ ንብረት አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ ንብረት እንደሆነ ይቆጠራል።

**አንቀጽ ፫፻፴፪· ሂሳቦችን ስለማጽደቅ**

፩· ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ የወጣው ልጅ የሞግዚቱን ሥራ ሂሳቦች ያጸደቀ እንደሆነና ዕድሜው ፲፰ ዓመት ያልሞላው ከሆነ ሂሣቦቹን ካጸደቀ በኋላ እስከ አንድ ዓመት ድረስ አጽድቆት የነበረውን ሂሳብ ራሱ ሊያፈርሰው ይችላል።

፪· ከሞግዚት አስተዳደር ነፃ የወጣው ልጅ ሂሳብ እንዳያቀርብ ለሞግዚቱ ፈቃድ ሰጥቶ የነበረ ቢሆንም ከዚህ በላይ ያለው ድንጋጌ ተፈፃሚነት ይኖረዋል።

፫· አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ አካለ መጠን የደረሱ ሲወርሱት፣ እነዚህ ወራሾች የልጁ ሞግዚት ያደረገውን ሂሳብ ያጸደቁት ወይም ሞግዚቱን ሂሳብ ከማቅረብ ነፃ

www.abyssinialaw.com


አውጥተውት እንደሆነ ከዚህ በላይ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ጠቅሰው ለመከራከር አይችሉም።

አንቀጽ ፫፻፴፫· ስለ ይርጋ

፩· አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ ወኪሎች ወይም ወራሾች በሞግዚትነት ሥራ ምክንያት በሞግዚቱ ላይ ስለኃላፊነቱ የሚያቀርቡዋቸው ማናቸውም ክሶች ሞግዚቱ የሞግዚትነት ሥራውን ከተወበት ጊዜ ጀምሮ እስከ አምስት ዓመት ሳያቀርቡ የቀሩ እንደሆነ በይርጋ ይታገዳል።

፪· ሆኖም አካለ መጠን ያልደረሰው ልጅ ንብረቶቹ እንዲመለሱለት ለመጠየቅ ክስ የማቅረብ መብቱ ከዚህ በላይ የተመለከተው ጊዜ ካለፈ በኋላም ቢሆን አይከለከልም።

## ምዕራፍ አሥራ አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

አንቀጽ ፫፻፴፬· ተፈፃሚነት የሌላቸው ሕጎችና ልማዶች

ይህን አዋጅ የሚቃረኑ ሕጎች ደንቦች መመሪያዎች ውሳኔዎችና የአሠራር ልምዶች ይህን አዋጅ በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚ አይሆኑም።

አንቀጽ ፫፻፴፭· በነባር ሕጎች መሠረት ተገኝተው ስለነበሩ መብቶች

፩· ግልጽ የሆነ ተቃራኒ ድንጋጌ ከሌለ በስተቀር ይህ ሕግ ከመጽናቱ በፊት የነበሩ ሕጋዊ ሁኔታዎችን ለማስገኘት አዲሱ ሕግ የሚጠይቃቸው መመዘኛዎች ከድሮው የተለዩ ቢሆኑም እንኳን በነባሩ ሕግ መሠረት ተገኝተው የነበሩት ሕጋዊ ሁኔታዎች ሁሉ ፀንተው ይቀጥላሉ።

፪· ግልጽ ሆነ ተቃራኒ ድንጋጌ ከሌለ በስተቀር ይህ ሕግ ከመጽናቱ በፊት በነበረው ሕግ መሠረት ተገኝተው የነበሩት ሕጋዊ ሁኔታዎች ያስገኟቸውን ውጤቶች ይህ ሕግ አይለውጣቸውም።

አንቀጽ ፫፻፴፮· ስለምዝገባ

፩· የክልሉ መንግሥት ይህ ሕግ በሥራ ላይ በዋለ በአንድ ዓመት ውስጥ ምዝገባን ለሚሹ ጉዳዮች የምዝገባ ሕግ

www.abyssinialaw.com


ያወጣል፣ አስፈላጊ ተቋሞችንም ያደራጃል።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ መሠረት የክብር መዝገብ ሹም ጽ/ቤት ተቋቁሞ ሥራውን እስኪጀምር ድረስ አግባብ ባለው አካል የተሰጡ ወይም የሚሰጡ የልደት፣ የጋብቻና ሌሎች አግባብነት ያላቸው የምስክር ወረቀቶች በክብር መዝገብ ሹም እንደተሰጡ ሰነዶች ተቆጥረው ሕጋዊነት ይኖራቸዋል።

አንቀጽ ፫፻፴፮· በሂደት ላይ ስላሉ የቤተሰብ ክርክሮች

፩· ይህ ሕግ ከመጽናቱ በፊት በፍርድ ቤት የተያዙ የቤተሰብ ጉዳይ ክርክሮች በዚህ ሕግ መሠረት ፍፃሜ ያገኛሉ።

፪· ይህ ሕግ ከመጽናቱ በፊት በቀድሞው ሕግ መሠረት በቤተዘመድ ሽምግልና ጉባኤ የተያዙ የፍቺ ክርክሮች በሙሉ አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ሥልጣን ወዳላቸው ፍርድ ቤቶች ይተላለፋሉ።

፫· ፍርድ ቤቶችም እነዚህን ጉዳዮች ተረክበው በዚህ ሕግ ድንጋጌዎች መሠረት ውሣኔ ይሰጣሉ።

አንቀጽ ፫፻፴፯· ደንብ የማውጣት ሥልጣን

የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ለዚህ ሕግ የአፈፃፀም ደንብ ሊያወጣ ይችላል።

፪· አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ከጥቅምት ፲፩ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ·ም· ጀምሮ የፀና ይሆናል ።

አዋሣ የካቲት ፲፮ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ·ም·
ኃይለማርያም ደሣለኝ
የደ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግሥት
ርዕሰ መስተዳድር

www.abyssinialaw.com


## ማውጫ

ገጽ

የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ............ ፩

ምዕራፍ አንድ

ስለመተጫጨት፤ ............ 2-4

ምዕራፍ ሁለት

ስለ ጋብቻ አፈጻጸም ............ 4-12

ክፍል ፩ ጠቅላላ ............

ክፍል ፪ ጋብቻ ለመፈጸም መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች ______

ክፍል ፫ ጋብቻ እንዳይፈጸም ስለመቃወም ______

ክፍል ፬ የጋብቻ አፈጻጸም ሥርዓቶች ______

ክፍል ፭ ስለ ጋብቻ ምዝገባ ______

ምዕራፍ ሦስት

የጋብቻ ሁኔታዎች አለመሟላት የሚያስከትለው ውጤት ______ 12-14

ክፍል ፩ ጠቅላላ ............

ክፍል ፪ ጋብቻ በተጋቢዎች ግላዊ ግንኙነት ላይ ስለሚኖረው ውጤት ............

ክፍል ፫ ጋብቻ በንብረት በኩል ስለሚኖረው ውጤት ______

ምዕራፍ አራት

የጋብቻ ውጤት ............ 14-22

ክፍል ፩ ጠቅላላ ............

ክፍል ፪ ጋብቻ በተጋቢዎች ግላዊ ግንኙነት ላይ ስለሚኖረው ውጤት ............

ክፍል ፫ ጋብቻ በንብረት በኩል ስለሚኖረው ውጤት ______

ምዕራፍ አምስት

ስለ ጋብቻ መፍረስ ............ 22-27

ክፍል ፩ ጠቅላላ ............

ክፍል ፪ በስምምነት ስለመፋታት ............

ክፍል ፫ ጥያቄ በመቅረቡ ምክንያት ስለሚወሰን ፍቺ ______

www.abyssinialaw.com



ስለጉዲፈቻ ............ 53–58
ምዕራፍ አሥራ ሁለት
ቀለብ የመስጠት ግዴታ ............ 58–62
ምዕራፍ አሥራ ሦስት
አካለ መጠን ስላልደረሱ ሰዎች ............ 62–88
ክፍል ፩ ጠቅላላ ድንጋጌዎች ............
ክፍል ፪ አካለመጠን ያልደረሰን ልጅ ስለሚጠብቁ ተቋሞች............
ክፍል ፫ የአሣዳሪውና የሞግዚቱ ሥልጣን ............
ንዑስ ክፍል ፩ አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ አስተዳደግና ጥበቃ ............
ንዑስ ክፍል ፪ አካለመጠን ያልደረሰን ልጅ ንብረት ስለማስተዳደር ............
ክፍል ፬ አካለመጠን ያልደረሰን ልጅ ለመጠበቅ የተመለከቱትን ደንቦች መጣስ ስለመየስከትለው ውጤት ............
ንዑስ ክፍል ፩ አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ ሥራዎች ............
ንዑስ ክፍል ፪ የሞግዚቱ ሕጋዊ ድርጅቶች ............
ንሁስ ክፍል ፫ በኃላፊነት ሊያስጠይቁ ስለሚችሉ ድርጅቶች ............
ክፍል ፭ አካለመጠን ያልደረሰ ልጅ ችሎታ ማጣት ስለመቅረቱ ............
ንሁስ ክፍል ፩ ከሞግዚቱ አስተዳደር ነፃ ስለመውጣት ............
ንሁስ ክፍል ፪ የሞግዚትነት ሥራ ሂሣቦችን ስለማስታወቅ ............
ምዕራፍ አሥራ አራት
ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች ............ 88–92